Hans-Jörg Ronsdorf

የምሥራቹ ምን እንደ ሆነና ለእኛ ምን ማለት እንደ ሆነ

ቀላል።
ግልጽ።

የእግዚአብሔር መልካም ዉንጌል

የእግዚአብሔር መልካም ወንጌል

የምሥራቹ ምን እንደ ሆነና ለእኛ ምን ማለት እንደ ሆነ

Hans-Jörg Ronsdorf

የኅትመት መረጃ

የእግዚአብሔር መልካም ወንጌል። የምሥራቹ ምን እንደ ሆነና ለእኛ ምን ማለት እንደ ሆነ

የተሻሻለ አዲስ እትም፣ 2026 (እ.ኤ.አ.)። በነጻ ለማውረድ፦ www.hans-joerg-ronsdorf.de

የታተመው 5ኛ እትም (ኖቬምበር 2021) በISBN 978-3-9820715-0-3 ወጥቷል (የጀርመንኛው እትም ISBN)።

© Hans-Jörg Ronsdorf – መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው። ጽሑፉ ሳይለወጥ እስከ ቀረ ድረስ ለሌሎች ማካፈል በጣም ይበረታታል።

Hans-Jörg Ronsdorf, Albis 6 1/2, 87477 Sulzberg

ኢሜይል፦ hj-ronsdorf@t-online.de

ድረ ገጽ፦ www.hans-joerg-ronsdorf.de

ማውጫ

ሦስት ቃላትና አንድ ታሪክ 7
ወንጌል 7
የእግዚአብሔር ወንጌል 10
ወንጌል የሚያሰፈልገው ማን ነው? 11
ኃጢአት? 12
ነጻነት – ግዳጅ አይደለም 14
እዚህ ደረጃ እንዴት ተደረሰ 15
እንዲህ ሆኖ መቅረት የለበትም 17
የመንግሥቱ ወንጌል 18
ይህ መልእክት ወደ እኛ እንዴት መጣ? 18
የእግዚአብሔር ንግሥና ምንድር ነው? 19
የእግዚአብሔር አገዛዝ – ለሁሉም የሚበጀው 20
የእግዚአብሔር ልጅ ወንጌል 22
ንጉሡና መሰቀሉ 24
የንጉሡ መገደል 24
ከተጠበቀው በተለየ 26
መሰቀሉ በእግዚአብሔር ዓይን 27
ስለ እኛ የተሠዋ 28
እግዚአብሔር መሥዋዕት ያሰፈልገዋል? 30
ክፉው በመልካም ተሸነፈ 33
ወሰን የሌለው የእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል 34
መሰቀሉ የሚሰጠን 35
መሰቀሉ – ሞኝነት 36
ወደ ቤት መመለስ 38
የእግዚአብሔር ጸጋ ወንጌል 38
ጸጋ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ 41
እግዚአብሔር ፍቅር ነው 43
የማይታየው ዓለም – የጨለማ ኃይላት 46
ኃይላቱና ሰዎች 47
ወንጌልና ኃይላቱ 48

ኃይላቱና የእግዚአብሔር የመዳን ዕቅድ 48
የመሰቀሉ ድል 50
ነጻነት ይቻላል 51
የሰላም ወንጌል 51
ወንጌል – የተፈጸመ የተሰፋ ቃል 52
የወንጌል ተሰፋ 54
የእግዚአብሔር አዲስ ዓለም ሕልም 56
ወንጌል – ለማዳን የሆነ ኃይል 58
ለወንጌል መታዘዝ 59
የኢየሱስ ደቀ መዝሙር መሆን 60
የደቀ መዝሙርነት ጅማሬ 60
ኢየሱስን መከተል ምን ይመስላል? 61
ወንጌልን ቸል ማለት 64
ሁሉም ወደ ብርሃን ይወጣል 65
የእግዚአብሔር ቁጣ 67
የዘላለም ሕይወትና ገሃነም 68
ሌላው ወንጌል 70
ወንጌል ያልሆነው 71
በመጨረሻም 72
ከዚህስ በኋላ? 73

እንኳን ደስ አለዎት! ይህ መጽሐፍ ትኩረትዎን መሳብ ችሏል። ያስቀምጡት። ያንብቡት። እግዚአብሔር ሊገናኝዎ ይፈልግ ይሆናል። ወንጌልን አስቀድመው የሚያውቁት ቢሆንም እንኳ – ወይም የሚያውቁት ቢመስልዎትም። እግዚአብሔር የንባብ ጊዜዎን ይባርክ። ዋጋ አለው።

አንድ ጊዜ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያንብቡት። በሁለተኛው ንባብ በግርጌ ማስታወሻዎቹ ውስጥ ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አውጥተው ማንበብ ይችላሉ።

ወንጌል ምን እንደ ሆነ የሚያሳየው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። ይህንን በተቻለኝ መጠን በአጭሩ አውጥቼ አቅርቤዋለሁ።

ሦስት ቃላትና አንድ ታሪክ

ወንጌል ታሪክ ነው። የእኛ አይደለም። የናዝሬቱ ኢየሱስ ታሪክ ነው። በቤተ ልሔም የሚጀምርና በኢየሩሳሌም የሚያበቃ። የማይታመን ታሪክ ነው። ቢሆንም ብዙዎች ያምኑታል። ምክንያቱም ይህ ጥንታዊ ታሪክ ቁጥር ሰፍር የሌላቸው አዳዲስ ታሪኮችን ጽፏል። ብዙ ሰዎች ይህ የኢየሱስ ታሪክ በእነርሱ ላይ ያደረገውን ይመስክራሉ። ተሰፋና የወደፊት ሕይወት ያላቸው አዲስ ሰዎች ሆነዋል።

ወንጌል በእርግጥም የኢየሱስ ታሪክ ነው። በሦስት ቃላት ሲጠቃለል ወደዚህ ያደርሳል፦

ኢየሱስ ጌታ ነው።[1]

እርሱ ንጉሥ ነው።[2]

በጽንፈ ዓለም ላይ። በሁሉም ሰውና በሁሉም ነገር ላይ። በጽድቅና በፍቅር የሚገዛ፣ ይቅር የሚል፣ ሁሉንም አዲስ የሚያደርግ ንጉሥ። ይህ ነው የምሥራቹ! ይህንን ሐዋርያት – ከመጀመሪያው ጀምሮ ከእርሱ ጋር የነበሩት ደቀ መዛሙርት – ሰበኩ። ለእስራኤልና ለዓለም ሁሉ።

ስለዚህ ገና ብዙ የሚባል አለ። በሚቀጥሉት ገጾች ያገኙታል። እነዚህን ሦስት ቃላት ይያዙ። ዋናው መልእክት ይህ ነው። የምሥራቹ ልብ ይህ ነው። እርሱም ሁላችንንም ይመለከታል። በግል። ሌሎችን አይደለም። እኛን። እኔን። ደግሞም መላዋን ፕላኔታችንን፣ መኖሪያችንን ይመለከታል። ያያሉ። ይህን መጽሐፍ ለእርሰዎ በግል እንደ ተላከ መልእክት አድርገው ያንብቡት።

ወንጌል

ክርስቲያኖች ስለ ወንጌል ይናገራሉ። ማንነታቸውን የሚገልጸው እርሱ ነው። ወይም ሊገልጸው ይገባል። የማንነታቸው አካል ነው። ያለ እርሱ ምንም አይደሉም። ትርጉም የላቸውም። ጣዕሙን እንዳጣ ጨው።

ወንጌል ምሥጢራቸው ነው። ሀብታቸው። መድኃኒታቸው። መንፈሳዊና ዓመፅ የሌለበት የጦር መሣሪያቸው። እንደ እርሱ ያለ መልእክት ያለው ማንም የለም።

«ወንጌል» የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ ይገኛል። ነገር ግን መጀመሪያ የተጠቀሰው እዚያ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ቤተ ክርስቲያን የፈጠሩት ሃይማኖታዊ ቃል አይደለም። በኢየሱስ ዘመንና ከዚያም በፊት የዕለት ተዕለት ቋንቋ አካል

1. የሐዋርያት ሥራ 2፥36፤ 4፥24፤ 11፥20፤ 15፥17
2. የሐዋርያት ሥራ 17፥7፤ 1 ጢሞቴዎስ 6፥15፤ ራእይ 17፥14፤ 19፥16

ነበር። እንደ መልካም ዜና። ደስታንና እፎይታን እንደሚያመጣ የምሥራች። መልካም ነገርን እንደሚያበሥር።[3] በልዩ ልዩ የደስታ አጋጣሚዎች ሰዎች «ወንጌል» ያደርሱ ነበር። ከክርስቶስ ልደት 63 ዓመት በፊት አውግስጦስ ቄሳር ተወለደ። ልደቱ በኋላ በመላው የሮም ግዛት እንደ የምሥራች ይከበር ነበር። ራሱን የመለኮታዊው ልጅ ብሎ ጠራ – ይህም ማዕረግ ለብዙ ቄሳሮች የሚሰጥ ሆነ። ስለ አውግስጦስ ቄሳር ከዚህ ወንጌል ጥቂት ዓረፍተ ነገሮች እነሆ፦

> «ይህ ቀን ለዓለም ሌላ ገጽታ ሰጥቷል። በእርሱ መወለድ ለሰዎች ሁሉ መዳን ባያበራ ኖሮ ዓለም በጠፋች ነበር። ለዓለም መዳን ይህ ሰው በእንደዚህ ያሉ ሰጦታዎች ተሞልቷል፤ ስለዚህም ለእኛና ለሚመጡት ትውልዶች አዳኝ ሆኖ ተልኳል። ጠብ ሁሉ እሁን አብቅቷል፤ እርሱ ሁሉን ክቡር ያደርጋል። የአባቶች ተሰፋ ተፈጽሟል። ከእርሱ የሚበልጥ ፈጽሞ ሊመጣ አይችልም። በእርሱ መወለድ አዲስ የዘመን አቆጣጠር ይጀምራል።»[4]

ከዚያ 700 ዓመት በፊት ጥንታዊው ነቢይ ኢሳይያስ እንዲህ ብሎ ነበር፦ እንዴት ያለ ደስታ ነው! የድል አብሣሪው በተራሮች ላይ እየፈጠነ ይመጣል! የምሥራች ያመጣል፣ ስላምንና መዳንን ያውጃል፣ ጽዮንንም፦ አምላክሽ የዓለም ሁሉ ንጉሥ ነው! ይላታል።[5]

3. ሉቃስ 1፥19
4. በትንሹ እስያ የምትገኘው የፕሪየኔ የቀን መቁጠሪያ ጽሑፍ፣ ከክርስቶስ ልደት 9 ዓመት በፊት፤ ተቆርጦና በነጻ ተተርጉሞ።
5. ኢሳይያስ 52፥7



ኢሳይያስ የሚናገረው ስለ ሕያው እግዚአብሔር ነው። ስለ ዘላለማዊው። ሁሉን ስለ ፈጠረው። ስለ ታሪክ ጌታ። ስለ ሰው አይደለም። ወይም ራሱን የአምላክ ልጅ ብሎ ስለ ሰየመ አይደለም። የቄሳሩ ዐዋጅ የደስታ ወሬ ነበር። ታዲያ ዓለም በእውነት የሚያስፈልጋትን የሚያመጣላት የትኛው ገዢ ነው? ሁሉም በውስጣቸው በጥልቅ የሚናፍቁትን?

ወንጌል ከጦር ግንባርም የሚመጣ ዜና ነበር። ድል ሲገኝና ጠላት ሲሸነፍ። ይህ ከክርስቲያናዊው ወንጌል ጋር ፍጹም ይሰማማል። ይህ የድል የምሥራች ነው። እግዚአብሔር በልጁ – በተሰቀለውና ከሙታን በተነሣው በኢየሱስ ክርስቶስ – ያገኘው ድል። እግዚአብሔር እጅ አልሰጠም። ስለ ዓለሙ ይዋጋል!

> በመስቀል ላይ መሞቱ፣ ከሙታን መነሣቱና በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ከፍ መደረጉ ኢየሱስን የዓለም ጌታና አዳኝ አድርገውታል። ሥልጣን ሁሉ ተሰጥቶታል፦ እርሱ የጽንፈ ዓለም ገዢ ነው።[6] ጽንፈ ዓለሙ የእርሱ ነው። ለሁሉ ይቅርታንና የዘላለም ሕይወትን የሚያቀርብ የነገሥታት ሁሉ ንጉሥ ነው![7] ስለ እኛ ሁሉን የሰጠ ንጉሥ። የሚወደን። የራሱን ጥቅም ስለማይፈልግና የተደበቀ ሐሳብ ስለሌለው ያለ ምንም ስጋት ራስን አሳልፎ ሊሰጠው የሚቻል ንጉሥ። ክብር ሁሉ ይገባዋል። ዳግመኛ ይመጣል፤ ስለዚህ ግን በኋላ ብዙ እንላለን።

6. ማቴዎስ 28፥18፤ የሐዋርያት ሥራ 2፥36፤ ኤፌሶን 1፥20-23
7. ሉቃስ 24፥47፤ የሐዋርያት ሥራ 2፥38፤ 5፥31፤ 10፥43፤ 13፥38፤ 26፥18

ወንጌል በአጭሩ ይህ ነው። ዋናው ነገር። ያስቡበት። ይያዙት። በፍጹም አይርሱት።

ኢየሱስን ንጉሥ ብሎ መመስከር ለክርስቲያኖች እስከ ዛሬ አደገኛ ሊሆን ይችላል፤ በአንዳንድ አገሮችም አደገኛ ነው። ይህን ንጉሥ[8] ማክበር ገዢዎችን፣ ቄሳሮችንና ነገሥታትን እንደ መገዳደር ተደርጎ ሊታይ ይችላል። ያለ ፖለቲካዊ ዓላማ። ከመታዘዝ የተነሣ። ለኢየሱስ ታማኝ መሆን ብዙ ጊዜ ስደትንና ሞትን አምጥቶባቸዋል። ምክንያቱም የእነርሱና የእኛ ኢየሱስ የምድር ነገሥታት ገዢ ነውና።[9] እርሱ ከእነርሱ በላይ ነው!

ነገር ግን የምሥራቹ ሊገደል አልቻለም። ከሙታን የተነሣው ጌታና ክርስቶስ በእርሱ ውስጥ ይኖር ነበርና። የሮምን ግዛት እንዲንበረከክ የሚያደርግ ፈንጂ ኃይል ነበረው። በስይፍ ሳይሆን በሚለውጠው የወንጌል ጸጋና ኃይል።

የእግዚአብሔር ወንጌል

ወንጌል ከየት ይመጣል? ሁሉም የሚጀምረው ከእግዚአብሔር ነው። በሦስት አካላት ካለው ከእንዱ አምላክ፦ ከአብ፣ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ። የፈጠረው እርሱ ነው። በልቡ ውስጥ ተወለደ። ከዘላለማዊ ፍቅሩ። ምድርና ሰዎች ገና ሳይኖሩ።[10] በውስጡ ያለው ሁሉ ከእርሱ ይመጣል።[11] ከእርሱ ብቻ። ወንጌሉ የእርሱ ነው። ስለዚህ እውነት ነው። የሚታመን። የሚያስተማምን። ሰው ሕይወቱን በእርሱ ላይ ሊገነባ ይችላል።[12] እግዚአብሔር ታማኝ ነውና።[13] አይዋሽም።[14] በወንጌል የሚሰጠው የተሰፋ ቃልና ማረጋገጫ ሁሉ የጸና ነው፤ ይፈጸማልም። ያለ ምንም ጥርጣሬ ልንታመንበት የምንችለው የተሰፋ ቃሉ ነው። በፈቃዱ የተሰጠ ነው። ወሰን ከሌለው ፍቅር የመነጨ። እርሱ ፈለገው። ራሱን መስጠት ደስ ያሰኘዋል። ደስታው ነው። በእርሱም ይከበራል።[15] ክብር ሁሉ ለእርሱ ይገባል።[16]

የምሥራቹን የሚያደርሰው እግዚአብሔር ራሱ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ተልእኮ ነው። እርሱ ይሠራል፣ ያደርጋል፣ ይናገራልም። የምሥራቹ ይህንኑ ወደምትፈልግ ዓለም ይመጣል። እግዚአብሔር ራሱ ምንም አያስፈልገውም። ምንም አይጎድለውም። ፍጹም ነው። ቢሆንም

8. የሐዋርያት ሥራ 17፥7
9. ራእይ 1፥5
10. ሮሜ 16፥25፤ 2 ጢሞቴዎስ 1፥9
11. 2 ቆሮንቶስ 5፥18
12. ማቴዎስ 7፥24
13. 1 ተሰሎንቄ 5፥24፤ ዕብራውያን 10፥23፤ 1 ጴጥሮስ 4፥19
14. ቲቶ 1፥2፤ ዕብራውያን 6፥18
15. ኤፌሶን 1፥6፣ 9፣ 12፣ 14
16. ራእይ 5፥11-14

ልቡ ሞልቶ ይፈሰሳል። ፍቅር ሰለ ሆነ ይወዳል። በዘመናት ሁሉ ታላቁን የመመለሰ ዘመቻ ይጀምራል። እኛን ሰዎችን መልሶ ይፈልገናል! ቤተሰብ እንዲኖረው ይፈልጋል![17]በተወለድንበት ሁኔታ ልጆቹ አይደለንምና። ሁላችንም ልጆቹ እንድንሆን ይፈልጋል። ስለዚህ ፍቅሩንና ቸርነቱን ሊሰጠን ይፈልጋል። ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንድንኖር።

ወንጌል የሚያስፈልገው ማን ነው?

የእግዚአብሔር መልእክት እርሱ በመጀመሪያ እንደ ፈጠራት ወዳልሆነች ዓለም ይመጣል። እርሱ እንዳሰባትም ወዳልሆነች። ምን ይመሰልዎታል፦ እግዚአብሔር በዓለማችን ጣልቃ መግባቱ አሰፈላጊ ነው? ወይስ ያለ እግዚአብሔር እንችለዋለን?

ዓለማችንን በቅንነትና በጥንቃቄ እንመልከት።

የእግዚአብሔር መልእክት በውሰጣቸው ወደ ተሰበሩና ተሰፋ ወደ ቆረጡ ሰዎች ይመጣል። ብዙ ጊዜ መውጫ መንገድ ወደማያዩ። ኅሊናቸው በበደል ወደሚሠቃይ። ምን ሁሉ መለወጥ እንዳለበት ወይም ሊለወጥ እንደሚችል ወደሚያውቁ። ፍርሃት ወዳለባቸው፣ ዕረፍት ወደሌላቸው፣ ባዶነት ወደሚሰማቸው፣ ወደ ታመሙና ወደ ታሰሩ። ሁሉም ወደሚሞቱ ሰዎች ይመጣል።[18] የወደፊቱን ወደሚፈሩ ሰዎች።

አብዛኛው የሰው ልጅ በድህነት ውሰጥ ይኖራል። በዕለት ተዕለት የሕልውና ትግል ውሰጥ። ብዙዎች መንገድ ላይ ይቀራሉ።

የእግዚአብሔር መልእክት በትዳር፣ በቤተሰብ፣ በሥራና በማኅበረሰብ ወደ ወደቁ ሰዎች ይመጣል። ራሰን ማጥፋት የመጨረሻ አማራጭ ወደሚመሰላቸው ሰዎች።

እንዲሁም ጥቂት ወይም ምንም ችግር ወደሌላቸው ሰዎች ይመጣል። በሀብታም አገር ወይም በሀብታም ቤተሰብ ውሰጥ የማደግ ዕድል ወዳገኙ። በገንዘብ ራሳቸውን የቻሉ። ነገር ግን ጤናና ብልጽግና ቢኖራቸውም ትርጉም አልባነትና የውሰጥ ባዶነት ወደሚያሠቃያቸው።

ገና ያልተሸነፉ በሽታዎችና ቫይረሶች ሕይወታችንን ያሰጋሉ። ተፈጥሮም ሕይወትን የሚያሰጋ ገጽታዋን ታሳያለች።

እያንዳንዱ ሰው ፍቅርን፣ ትርጉምን፣ ይቅርታንና መደገፊያን የሚጮኽ የጥያቄዎች፣ የጭንቀቶችና የችግሮች ትንሽ ዓለም ነው። ይህ በሥራ መጨናነቅና በልዩ ልዩ መዘናጊያዎች

17. መዝሙር 103፥13፤ ኢሳይያስ 64፥8፤ ሚልክያስ 2፥10፤ ዮሐንስ 14፥2፤ ዕብራውያን 2፥10፤ 1 ዮሐንስ 3፥1-3
18. ሮሜ 5፥12-14፤ 6፥23

ተደብቆ ወይም ታፍኖ ቢሆንም እንኳ።

ወንጌል እርስ በርሳቸው ወደሚዋጉ ሕዝቦች ይመጣል። እርስ በርሳቸው በጠብና በሰላም ማጣት ወደሚኖሩ ሰዎች። ግፍ ቤቱ ወደ ሆነባት ዓለም ይመጣል። እስከ ዛሬ ሰዎች ሰዎችን በባርነት ወደሚገዙበትና ወደሚበዘብዙበት። እርስ በርስ ወደሚያገልሉበት። ደካሞቹ ተጠቂዎች ወደሚሆኑበት። ልጆች እንዲሠሩ ወደሚገደዱበትና ሴቶች ወደሚበዘበዙበት። ሰብዓዊ መብቶች በመለ መንግሥታት በዘዴ ወደሚጣሱበት።

ዓለም ለብዙዎች በሥቃይ የተሞላች ሰፍራ ሆና ትቀራለች። ይህን ዝርዝር ሲያነቡ ሁሉም ነገር እንዲህ መጥፎ እንዳልሆነና ብዙ መልካም ነገርም እንዳለ አሰቀድመው አስበው ይሆናል። ብዙ ነገርም እየተሻሻለ ነው። ትክክል ነዎት። ጉዳዩ ያደላ ወይም ተሰፋ የቆረጠ የዓለም አመለካከት አይደለም። ጉዳዩ እግዚአብሔርና ወንጌሉ ያሰፈልጉናል ወይ የሚለው ጥያቄ ነው።

ይህ የምሥራች ያሰፈልገናል! ሰው በማንኛውም ጊዜ ወደዚህ ግንዛቤ ሊደርስ ይችላል። ይህንንም ወንጌል ለራሱ ሊቀበል ይችላል። ብዙ ሰዎች ይህንን ተገንዝበዋል። እንዳንድ ጊዜ በከባድ መንገድ። ወደዚህ ግንዛቤ ያደረሳቸው ውድቀት፣ መሰበር፣ በሽታና ሥቃይ ነበሩ። እግዚአብሔር ዝም አይልም። እነዚህ አሰቸጋሪና ብዙ ጊዜ ሕይወትን የሚያሰጉ ገጠመኞች እኛን ለማግኘት የሚጠቀምባቸው የእግዚአብሔር ድምፅ ማጉያ ናቸው።[19]

ኃጢአት?

ዘመናዊ ቃል አይደለም። የማይማርክና በተሳሳተ መንገድ የሚረዱት። ቢሆንም የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከትና ለነገሮች መንሥኤ የሚሰጠው ማብራሪያ አካል ነው። የማንፈልገውን ሁሉ፣ ውድቀትን፣ መሰበርን፣ ጠላትነትንና ትርምስን መንሥኤ እንዴት እናብራራለን?

መጽሐፍ ቅዱስ ሰውን ሲገልጽ ግልጽ ነው። እንዴት እንደሚወለድ፣ እንዴት እንደሚያድግና እንደሚኖር። ለባልንጀሮቹ እንዴት እንደሚሆን። ለእግዚአብሔርም። በግልጽ ይናገራል። አያለሳልስም። ያለ ርኅራኄ ሐቀኛ ነው። ኃጢአተኞች እንደ ሆንን ይናገራል።[20] ሁላችንም። ያለ ልዩነት። ኃጢአተኞች ስለ ሆንን ሁላችንም ኃጢአት እንሠራለን። ይህ ሁሉን የሚያጠቃልልና ልዩነት የማያደርግ ድምዳሜ የሚገኘው በመጽሐፍ ቅዱሳዊው የዓለም አመለካከት ብቻ ነው! ሁሉም ያለ ልዩነት ኃጢአተኞች ናቸው የሚል ሃይማኖት የለም።

---

19. የድምፅ ማጉያው ምሳሌ የሲ. ኤስ. ሉዊስ (C. S. Lewis) ነው፤ «Über den Schmerz» (The Problem of Pain)።
20. ኤፌሶን 2፥1

ኃጢአት የምናደርገውን ብቻ አይገልጽም። ማንነታችንንም ጭምር ነው። እንደሚያሳዝን ሆኖ እንደ ዕጢ በውስጣችን ተለይቶ ሊወጣ አይችልም። ከዚህ የከፋ ሊሆን አይችልም፦ በኃይሉ ተይዘናል። ይህ ከስሕተት ባሕርይ እጅግ የከበደ መዘዝ አለው። ኃጢአት የግለሰብ በደሎች ክምችት ብቻ አይደለም። ማንነታችንን ስርጎ የያዘና የተቆጣጠረ ንቁና ክፉ ኃይል ነው። ጥፋት ነው። ምክንያቱም በኃጢአታችን ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅር ተለይተናል። ያ ፍቅር ለእኛ የማይደረስበት ነው። ኃጢአትና እግዚአብሔር በፍጹም አብረው አይሄዱም።

ከኃጢአት ጋር ሞት መጣ። እንደማይቀር መዘዝ። እንደሚገባን ደመወዝ። የዘራነውን እናጭዳለን። ኃጢአትና ሞት ማንም የማያመልጣቸው ዓለም አቀፍ ኃይላት ናቸው።

ኃጢአት እንደ ገዢ ኃይል ባሕርያችንን በጎጂ መንገድ ይቀርጻል። ስለ ሌሎች ደኅንነት ሲሆን – የጎረቤታችንም ሆነ በአፍሪካ በሞት አፋፍ ላይ ያለው ሰው – ፍጹምነት ፈላጊዎች፣ ፈሪዎችና ወላዋዮች ያደርገናል። ስለ ራሳችን ጥቅም ሲሆን ደግሞ ራስ ወዳዶች ያደርገናል። ኃጢአት ራሳቸውን የሚያመልኩ፣ አታላዮች፣ ሱሰኞች፣ ሴረኞች፣ አክራሪዎች፣ አመንዝሮች፣ ደፋሪዎች ያደርገናል። ዝርዝሩ ማብቂያ የሌለው ሊሆን ይችላል።

ነገር ግን እኛ እስረኞች ወይም ሕሙማን ብቻ አይደለንም። ዝም ብለው የሚጎዱ ተጠቂዎች ብቻ አይደለንም። ይልቁንም በግድ የተመለመልን ንቁ የኃጢአት ወኪሎች ሆነናል። ራሳችንን እንደ ተወካዮቹ፣ እንደ መሣሪያዎቹ አሳልፈን ሰጥተናል። ምርኮ ብቻ አይደለም፤ ንቁ ተባባሪነት ነው።

ኃጢአትና እግዚአብሔር ያላቸውን ግንኙነት ቸል እስካልን ድረስ የኃጢአት ባሕርይ ተሰውሮብናል። ሰው ሊያፍነው ወይም ሊገታው የሚችል ወይም የሚገባው በሰው ሕይወት ውስጥ ያለ ክስተት ብቻ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአትን ሥርዓት አልበኝነት፣ ጠላትነት፣ ዓመፅ፣ ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ብሎ ይገልጸዋል። ያለ እግዚአብሔር ያለ ሰው መሻሻል የሚያሰፈልገው ያልተሟላ ፍጡር ብቻ አይደለም። መሣሪያውን መጣል ያለበት ዐመፀኛ ነው። እጅ መስጠት ብቸኛው መውጫ ነው።

እባክዎ፣ ይህ ሁሉ ከባድ ክስ ቢሆንም ማንበብዎን ይቀጥሉ!

የሰው ሕይወት መሠረታዊ ግንኙነት – ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት – ተሰብሯል። ይህ መስበር እርስ በርሳችን ባሉን ሌሎች ግንኙነቶች ሁሉ ይታያል። ኃጢአተኞች የሆንነው በግል ወይም ለብቻችን ብቻ አይደለም። ከኃጢአት ማምለጥ የማይችለው የመላው የሰው ልጅ አካል ነን።

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ የሕክምና ምርመራ መደናችን ነው! ኩነኔ አይደለም!

ሐኪምዎ ገዳይ በሽታዎን በተመለከተ ሐቀኛውን የምርመራ ውጤት ቢደብቅዎ ደስ ይልዎታል? በተለይ ደግሞ በዚያው ቅጽበት በሽታውን የሚያሸንፍ መድኃኒት ወይም ቀዶ ሕክምና ሊሰጥዎ ቃል መግባት ሲችል?

የእግዚአብሔርን ምርመራ መረዳትና መቀበል ከሞላ ጎደል የማይቻል ነው። ራሳችንን እንደ ልዩ ማየት እንወዳለን። ወይም የሁኔታውን ክብደት እናቃልላለን።

ስለዚህ ወንጌል ችግሮች ቢኖሩባትም በሚገርም ሁኔታ የእግዚአብሔርን የመዳን መልእክት ብዙም ወደማትፈልግ ዓለም ይመጣል። ተቃርኖ ነው። ቢሆንም በዚህች ፕላኔት – በእርሱ ፕላኔት – የሚሆነው ነገር ለእግዚአብሔር ግድ የማይሰጠው አይደለም። ወንጌል እግዚአብሔር ስለዚህ ዓለም እንደሚዋጋ ማስረጃ ነው። ሥቃይ፣ ክፋትና ሞት የመጨረሻውን ቃል ሊይዙ አይገባም። እግዚአብሔር ፍቅር ነውና![21]

ለመጀመሪያው ጥያቄ መልሱ ይህ ነው፦ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ወንጌል ያስፈልገናል።

እግዚአብሔር ኃጢአትን፣ ሰዎች የሚያስቡትንና የሚያደርጉትን ክፋት – በትልቁም በትንሹም – የሚጸየፍበት መጠን ታላቅ ነው። ምክንያቱም ኃጢአት ያጠፋናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ሊያድነንም ይፈልጋል። ይህ የእግዚአብሔር መጸየፍና በኃጢአት ላይ የሚሰጠው ፍርድ በተጨባጭ የሚገለጸው «በእግዚአብሔር ቁጣ» ነው።[22]

ክፉውን – እኛ ፈጸሚዎቹ መሆናችን የታወቀበትን – ምንም ያህል ቢኮንነው፣ እያንዳንዱን ሰው ከእርሱ ነጻ ሊያወጣ የዚያኑ ያህል ይፈልጋል።

ነጻነት – ግዳጅ አይደለም

ይህ ድንቅ ወንጌል ቢኖርም[23] እግዚአብሔር ሰዎች «አዎን» እንዲሉ አያስገድድም። እውነተኛ ፍቅር የሚኖረው በነጻነት ላይ ብቻ ነው! የመምረጥ ነጻነትና ኃላፊነት የሰው ባሕርይ ሆነው ይቀራሉ። ሰው የተፈጠረው እንዲህ ነው፤ በሌላ መንገድ አይደለም።

ነገር ግን ሰው ኃጢአተኛ ሆኖ ከእንግዲህ ገለልተኛ አይደለም። ኃጢአት ረዳት የሌለው ያደርገዋል፤ እንዲያውም በራሱ ወንጌልን መቀበል የማይችል ያደርገዋል። ኃጢአተኛ መሆኑን ራሱ መገንዘብ በሰው ዓይን የማይቻል ነው። ወንጌል ግን ኃይል አለው። ስለ ራሱና ስለ እግዚአብሔር ዓይንን ይከፍታል። ለልብና ለኅሊና ብርሃን ይሰጣል። እግዚአብሔር


21. ሮሜ 5፥8፤ 1 ዮሐንስ 3፥1፤ 4፥7-11
22. ዮሐንስ 3፥36፤ ሮሜ 1፥18፤ 5፥9፤ ኤፌሶን 2፥3፤ 5፥6፤ ቆላስይስ 3፥6፤ 1 ተሰሎንቄ 1፥9-10
23. 2 ቆሮንቶስ 4፥4

በዚህ ውሳኔ ሰውን ብቻውን አይተወውም። የሰው ልብ ከባድ ውጊያ የሚካሄድበት የጦር ሜዳ ነው። እግዚአብሔር ልቦችን ለማሸነፍ ይፈልጋል። ሊያስታርቅ ባለው ፈቃደኝነትም ለማሳመንና ብርሃን ለመስጠት።

እግዚአብሔር ለማዳን ያለው ብልሃት ልክ የለውም። እግዚአብሔር በቅዱስ መገኘቱ የኃጢአትንና የጠፋነትን ግንዛቤ ለመቀስቀስና በዚያው ጊዜ መዳንንና ማዳንን ለመስጠት ማንኛውንም ሁኔታ፣ ማንኛውንም ጊዜና ማንኛውንም ሰፍራ ሊጠቀም ይችላል።

ለእነዚህ ታላላቅ ስዓቶች ደንብም ቅጥም የለም። እንዲህ ሆኗል። እንዲህ ይሆናል። አሁንም በእርሰዎ ላይ እንዲህ ሊሆን ይችላል። ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር በምን ያህል ድንቅ፣ ያልተጠበቀ፣ ምሥጢራዊ፣ ፍቅር የተሞላ ወይም ሥር ነቀል መንገድ ወደ ሕይወታቸው እንደ መጣ ይመስክራሉ።

> የእግዚአብሔር መልእክት ወደ እርሱ እንድንመለስ የሚሰጥ አስቸኳይ ትእዛዝ ነው።[24] ለእኛው መልካም። ይሁን እንጂ ሰዎች ለዚህ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ ኃላፊነቱ የራሳቸው ነው።



እዚህ ደረጃ እንዴት ተደረሰ

ሰዎች የተፈጠሩት በምድር ላይ የእግዚአብሔር ወኪሎች ሆነው ነበር። በመልኩ። ምድርን ከፈጣሪያቸው ጋር በእንክብካቤ እንዲያስተዳድሩና እንዲገዙ። የእትክልቱ ገነት – ውስን

24. የሐዋርያት ሥራ 17፥30

ሰፍራ – በመላው ምድር ላይ እንዲሰፋፋ ታሰቦ ነበር። እርሱ – አባት፤ እነርሱ – ሰዎች ሁሉ – ቤተሰቡ።[25] ከመጀመሪያው የታሰበው እንዲህ ነበር።

ሰዎች – እውነተኛ የፈቃድ ነጻነት ይዘው የተፈጠሩ። የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዲቀበሉ፣ እንዲመልሱና ለሌሎች እንዲያሰተላልፉ። ከፈጣሪ ጋር እንዲህ መኖርና መሥራት – ሕልም ነው። በቅርብ። በጥበቃውና በበረከቱ ሥር።

ነገር ግን ያን ጊዜ፣ በመጀመሪያ፣ ሰዎቹ ሌላ መረጡ። ልዩ መብት ያገኙበትን መኖሪያቸውን – የእትክልቱን ገነት – አልጠበቁም። አሳሳቹ ገባ። ተንኮለኛው እባብ። ከእባቡ በሰተጀርባ በአንድ ወቅት ያበራ የነበረ የእግዚአብሔር መልአክ ተደብቆ ነበር። እርሱ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ነበር። ዐምፆ በኃጢአት ወድቆ ነበር። ሰይጣን – ዲያብሎስ – ይህን ሐሳብ ለሰዎች ሊሸጥ ፈለገ፦ ወደ ተሻለና ነጻ ወደ ሆነ ሕይወት የሚያደርስ ብርሃንና እድገት አድርጎ።

የፈጣሪያቸውን መልካም መመሪያ አልተከተሉም። እንደ እግዚአብሔር መሆን የዲያብሎስ ፈተናና ማባበያ ነው። ስለዚህ የመልካሙን አምላካቸውን ቀላል ትእዛዝ ናቁ። ምናልባት እግዚአብሔር አንድ መልካም ነገር ከልክሏቸዋል ብለው ፈርተው ይሆን?[26]

ለዚህ እርምጃ ከፍተኛ ዋጋ ከፈሉ። ነገሮች መሆን እንደሚገባቸው መሆናቸው ቀረ። ገነትን አጡ። ሞትና ጠፊነት – በመንፈስም በሥጋም – ወደ ሕይወታቸው ገባ።[27] ተሰፋፉ። እንደ ዘር የሚወረሰ በሽታ ወደ ዘሮቻቸው ሁሉ ተላለፈ። እኛም ከእነርሱ ውስጥ ነን።

ይህ ከረጅም ጊዜ በፊት ነበር። በሆነ መንገድ እንዲሁ ሆኖ ቀረ። እስከ ዛሬ። ከብዙ ሺህ ዓመታት በኋላ እኛ ሰዎች ሕይወትን ያለ ፈጣሪ እንቀርጻለን። በራሳችን ፈቃድ። እግዚአብሔር እንደሌለ። የተሻለ እንደምናውቅ እናስባለን። ፈጣሪያችንን ረስተናል። ይበልጥ የሚማርኩ የሚመስሉ አማልክትንም አግኝተናል። ምክንያቱም እንደ ሰው ተፈጥሮአችን ሃይማኖተኛ መሆን፣ በአንድ ነገር መደገፍ ወይም በአንድ ነገር ማመን ነው። ይህን የዓለም ሃይማኖቶች ያሳያሉ፤ የዘመናዊ ሰዎች ጠባይና እንደ ገንዘብ፣ ሥልጣንና ወሲብ ያሉ በእግዚአብሔር ቦታ ያስቀመጧቸው አማልክትም ያሳያሉ። አሁን ያለ እግዚአብሔር ፍላጎቶቻችንን ማርካት አለብን። በትልቅም በትንሽም ደረጃ የማይጠግብ ስግብግብነት በራሳቸው ውስጥ የጠፉ ልቦች መግለጫ ነው። በራሳችን ውስጥ ታስረናል፤ አንድ ዋና ነገር፣ ለሕይወት ትርጉም የሚሰጥ ነገር እንደ ጠፋብን እናውቃለን። የሕይወትን

25. ኢሳይያስ 63፥16፤ 64፥8፤ ሉቃስ 3፥38፤ የሐዋርያት ሥራ 17፥28-29
26. ዘፍጥረት 3
27. ሮሜ 5፥12-21

ምንጭ፣[28] ፈጣሪያችንን ትተናል። ከእርሱ ጋር ግንኙነት ሳይኖር ከፍጥረት ጋር ያለው ጤናማ ግንኙነት ተዛብቷል። ሰዎች በብዙ ቦታ የሚኖሩበትን ቤት ያጠፋሉ። ከእግዚአብሔር ጋር፣ እርስ በርሳችንና ከፍጥረት ጋር ለተሳካና ለተባረከ ሕይወት የተሰጡንን የእግዚአብሔርን መልካም ትእዛዛት እንቃወማለን።

ሕጎችና ትእዛዛት ከእምባገነን የሚመጡ ናቸው ተብሎ ብዙ ጊዜ ይደመደማል። ሊቆጣጠረን፣ ሊገዛንና ሊያጠብበን ከሚፈልግ አምላክ። ነገር ግን ብዙዎች እግዚአብሔር በእውነት ማን እንደ ሆነ አያውቁም።

የሚበጀንን የሚፈልግ መልካም አባት።

እንዲህ ሆኖ መቅረት የለበትም

እግዚአብሔር የወደቀችውን ዓለም ይከተላል። ከችግሮቿና ከእሰጨናቂ ቦታዎቿ ሁሉ ጋር። አይተዋትም።[29] ክፋት በልዩ ልዩ ጥንካሬው፣ በትልቁም በትንሹም፣ ችግር ብቻ አይደለም። ከመጀመሪያው ጀምሮ የሕልውና ቀውስ ነው። መኖር ወይም አለመኖር። ከዔደን ውጭ መትረፍ – ይህ የሕልውናችን እድማስ ነው። ከዚያ ወዲህ በዚህ ቀውስና በሥራችን መዘዞች ሁሉ ውስጥ እንኖራለን። ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ በየዕለቱ በዓይናችን እናያለን። ያለ እግዚአብሔር መልካም ፍጻሜ ሊኖረው አይችልም። ያለ እግዚአብሔር መንገዱ ወደ ጨለማ ነው። በመንፈሳዊና በሥነ ምግባራዊ ጨለማ ውስጥ እየተደናቀፍን እንዞራለን። መንገዱንም መድረሻውንም አናውቅም።

ወንጌል – ፍርድና መኮነን ሳይሆን – በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ የእግዚአብሔር መልስ ነው። ወንጌል ክፋትን ለማሸነፍ ያወጣው ዋና ዕቅዱ ነው። የቁልቁለቱን ሽክርክሪት ለማስቆምና ብርሃንን፣ ሕይወትንና ተስፋን ወደ ጨለማው ለማምጣት።[30] ነጻነት፣ ሰላምና ደስታ እንዲመለሱ።[31] ለሁሉ። ከመጥፎው ሁሉ ደግሞ መልካም ነገር እንዲወጣ።[32] እግዚአብሔር እንደገና ቤተሰብ እንዲኖረው። እኛም ልጆቹ እንድንሆን። በእኛ ላይ ሊደርስ ከሚችለው ሁሉ የሚበልጠው ይህ ነው።

ወንጌል ነገሮች ዛሬ እንዳሉ እንደማይቀሩ እግዚአብሔር የሰጠው ማረጋገጫ ነው። ይህ የተሰፋ ቃል እስከ ዛሬ ጸንቶ ይኖራል። ፈጽሞ አልተሻረም። የእርሱ ለሆኑ ሰዎች ሁሉ

28. መዝሙር 36፥9፤ ምሳሌ 14፥27፤ ኤርምያስ 2፥13፤ 17፥13
29. ዮሐንስ 3፥16
30. መዝሙር 27፥1፤ 43፥3፤ ኢሳይያስ 9፥2፤ 60፥1፤ ማቴዎስ 4፥16፤ ዮሐንስ 1፥4-9፤ 3፥19-21
31. ሉቃስ 2፥10
32. ዘፍጥረት 50፥20

ይሠራል። በዓለም በየትኛውም ሰፍራ።

የመንግሥቱ ወንጌል

ወንጌል በእርግጥም ቀላል ነው። ሁሉም ሊረዳው ይገባል። ቢሆንም ልዩ ልዩ ገጽታዎችና ጎኖች አሉት። ሰው በመጀመሪያ ከሚያስተውለው በላይ ይይዛል። አንድ አልማዝ ያሰቡ። ካሉት ሁሉ የሚበልጠውን። የተቀረጸ። ብርሃንን በአንድ ገጽ ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ በተቀረጸ ገጽ ይሰብራል። ወንጌል በብዙ መንገድ በሚያስደንቅ የብርሃን ድምቀት ያበራል። ይህ የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነው የክርስቶስ ክብር ነው።[33]

ይህ መልእክት ወደ እኛ እንዴት መጣ?

መልእክቱ የመጣው በአንድ ግለሰብ ነው። አዎን፣ መልእክቱ ግለሰብ ነው። ሕግ አይደለም። የእምነት መግለጫ አይደለም። የሃይማኖት ትምህርት መጽሐፍ አይደለም። ሰው ነው። ጥያቄው ምን ሊያድነን ይችላል የሚለው አይደለም። ማን ሊያድነን ይችላል የሚለው ነው።

ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ። ቢሆንም ፍጹም የተለየ ነበር፦ በአንድ ጊዜ አምላክም ሰውም የሆነ። ነገር ግን አምላክነቱን ወደ ኋላ የሚያስቀምጥና በትሕትና፣ እንዲያውም በድካም ወደ እኛ የሚመጣ።

እግዚአብሔር ወደ እኛ ዝቅ ይላል። ራሱን እጅግ ትንሽ አደረገ።[34] ልናስበው የማንችለው ወሰን የሌለው። እንደ እኛ መጀመሪያ ያለው ያልሆነ። እርሱ ሰው ሆነ። ወደ እኛ እጅግ ቀረበ።[35] ከቀድሞው ሁሉ ይበልጥ። ወደ ዓይናችን ደረጃ ዝቅ ብሎ። ፈጣሪ ከፍጡራኑ ጋር። በሰው መልክ።[36] ታየ፣ ተሰማ፣ ተዳሰሰ፣ ታቀፈ።[37] አየ፣ ተናገረ፣ በልቡ ተነካ፣ አለቀሰ፣ ሰዎችን ወደደ፤ በርኅራኄም ዳሰሳቸው።

በመጨረሻ እንድንረዳ። በገዢ ግርማ አልመጣም። የመጣው የናዝሬት እናጢ ነበር። ከገሊላ ዝቅተኛ ማኅበረሰብ። እግዚአብሔር በኢየሱስ ወደ እኛ ይመጣል። የሰጠውን የተሰፋ ቃል እውን ያደርጋል። ኢሳይያስ አስቀድሞ እንዲህ ይላል፦

33. 2 ቆሮንቶስ 4፥4
34. ፊልጵስዩስ 2፥6-8
35. ዮሐንስ 1፥14
36. ፊልጵስዩስ 2፥5-11
37. 1 ዮሐንስ 1፥1-3

> የጌታ መንፈስ ያዘኝ። ጌታ ቀብቶኛልና፤ በዚህም ለድሆች የምሥራች እንዳመጣ ሥልጣን ሰጥቶኛል። ተሰፋ የቆረጡትን አዲስ ብርታት እንድሰጣቸው፣ ለታሰሩትም፦ «ነጻ ናችሁ! እስራታችሁ ይፈታል!» ብዬ እንዳውጅ ልኮኛል።[38]

ኢየሱስ ይህን በናዝሬት ምኩራብ ውስጥ ስለ ራሱ ይናገራል፦ ይህ የነቢዩ ቃል ዛሬ በዓይናችሁ ፊት ተፈጸመ።[39] መላ ሕይወቱ – ቃሉና ሥራው – የእነዚህ የነቢይ ቃላት ፍጻሜና የዚህ የምሥራች ፍጹም መግለጫ ነው።

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ምሳሌ ነው።[40] እርሱን ያየ የሰማዩን አባት አየ።[41] እርሱ የእግዚአብሔር ተልእኮ ነው። ኢየሱስ እግዚአብሔር ሊነግረን ያለው ነው።[42] እግዚአብሔር ማን እንደ ሆነና ምን ዓይነት እንደ ሆነ ለመረዳት ከፈለግን ከኢየሱስ በመነሣት ልንረዳው ይገባናል። ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር ያለን ሥዕል ነው። በወንጌል ታሪኮች እንደ ተገለጸው። እግዚአብሔር እንዲህ ነው።

ስለዚህ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ የጻፏቸው አራቱ የኢየሱስ የሕይወት ታሪኮች ወንጌሎች ይባላሉ። ማርቆስ እንዲህ ይጀምራል፦ በዚህ መጽሐፍ ስለ እግዚአብሔር ልጅ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገረው የምሥራች እንዴት እንደ ጀመረ ተጽፏል።[43]

የምሥራቹ የሚጀምረው በኢየሱስ ነው። ስለ እርሱ እንዲህ ተብሏል፦ ኢየሱስ ወደ ገሊላ ተመለሰ፤ በእግዚአብሔርም ተልእኮ እንዲህ ብሎ አወጀ፦ ጊዜው ደርሷል፤ አሁን እግዚአብሔር አገዛዙን ይመሠርታል፤ ሥራውንም ይፈጽማል። ንስሐ ግቡ፤ በዚህ የምሥራችም እመኑ![44]

የእግዚአብሔር ንግሥና ምንድር ነው?

የእግዚአብሔር አገዛዝ የፍቅርና የጽድቅ አስተዳደሩ ነው። ለዓለማችን ወደፊት የሚያዋጣው ብቸኛው አማራጭ። ብቸኛው የወደፊት ዕድሏ።

ብዙ አይሁድ ይህን የተረዱት የሮም ወራሪዎች እንደሚሸነፉና አምባገነንነታቸው እንደሚያበቃ አድርገው ነበር። ነገር ግን በኢየሱስ የመጣው ተራ ሰው ነው እንጂ ፖለቲካዊ

38. ኢሳይያስ 61፥1-2
39. ሉቃስ 4፥16-22
40. ቆላስይስ 1፥15፤ ዕብራውያን 1፥1-3
41. ዮሐንስ 14፥9
42. ዕብራውያን 1፥2
43. ማርቆስ 1፥1
44. ማርቆስ 1፥14-15

ሥልጣን ያለው ንጉሥ አይደለም። የጦር ጀግና አይደለም። መንግሥቱ – የእግዚአብሔር መንግሥት – እንደ ተጠበቀው በኢየሩሳሌም በዳዊት ዙፋን ላይ አይጀምርም፤ በመሰቀል ላይ በሚያበቃ ተጓዥ ሰባኪ እንጂ። ኃጢአታቸውን በሚናዘዙና ሕይወታቸውን በሚለውጡ ሰዎች ልብ ውስጥ ይጀምራል። መንግሥቱ ከዚህ ዓለም አይደለም።[45] ከእግዚአብሔር ይመጣል። የተለየ ነው። ያለ ዓመፅ፣ ያለ ጭቆና፣ ያለ ወታደራዊ ወረራ። በእስራኤል ይጀምራል፤ ትኩረቱ ግን መላው ዓለም ነው። ለሰዎች ሁሉ የታቀደ።

በኢየሱስ የእግዚአብሔር ንግሥና በነበረው ፖለቲካዊ መዋቅር ላይ አይነሣም። ሌላ ግብ አለ። ኢየሱስ በአገሩ እየዞረ ይሰብካል፦ ንሰሐና ወደ እግዚአብሔር መመለስ። የእግዚአብሔር አገዛዝ እውን የሚሆነው በኢየሱስ መገለጥና እርሱን በሚከተሉ ሰዎች ነው። ቁጥር ሰፍር የሌላቸውን ሕሙማን ይፈውሳል። አጋንንትን ያወጣል። የእግዚአብሔር ንግሥና ሰዎችን በሚያሠቃዩ ክፉና የማይታዩ ኃይላት ላይ ይነሣል። እንደ ነገሥታት ወይም ወታደሮች ያሉ የሚታዩ ባለ ሥልጣናት ብቻ አይደሉም ያሉት። ሰዎች የሚሠቃዩባቸው የማይታዩ ኃይላት አሉ። በመጀመሪያ በአትክልቱ ገነት የነበረውን አሳሳች ያሰታውሱ። ሰለዚህ በኋላ ብዙ እነላለን።

ኢየሱስ ክፋት ከየት እንደሚመጣና ለምን እንዳለ ለሚለው ጥያቄ መልስ አይሰጥም። ይሠራል። በአባቱ ተልእኮና ሥልጣን በክፋት ላይ ውጊያ ይጀምራል። የእግዚአብሔር ንግሥና ወደዚህ ዓለም ሰብሮ ይገባል፤ ያን ጊዜ ከነበሩት ሮማውያን ይልቅ እጅግ በጥልቀት የእግዚአብሔርን አገዛዝ የሚቃወመውን ነገር ይለውጣል። የእግዚአብሔር መንግሥት ሰዎች ይበልጥ በሚሠቃዩበት ደረጃ ያገኛቸዋል። ታላቁ ጠላት ክፋት፣ ግፍ፣ ግብዝነትና ፍቅር ማጣት ነው። በአንድ ቃል፦ ኃጢአት። ሰውን በመንፈስ ታማሚ አድርጎታል። በሰው ላይ ሥልጣን አግኝቷል። ያን ጊዜም ዛሬም።

እግዚአብሔር ራሱ ወደ ኃጢአት፣ ወደ ሥቃይና ወደ ፍርሃት፣ ወደ መከራና ወደ ሞት መድረክ ይመጣል። ይህን ሁሉ በራሱ ላይ ሊጭንና በዚህም አዲሱን መንግሥት ሊመሠርት ይመጣል።

የእግዚአብሔር አገዛዝ – ለሁሉም የሚበጀው

ኢየሱስ በሰውር 30 ዓመት ከኖረ በኋላ ለሦስት ዓመት ተኩል በይፋ ይሠራል። ይፈውሳል፣ ነጻ ያወጣል፣ በእውነት አስፈላጊ የሆነውንም ያስተምራል። ግብዝነትን ይገልጣል፤ የተራቡትን ያጠግባል። በዚህ እግዚአብሔር ማን እንደ ሆነና ምን እንደሚፈልግ ያሳያል።

45. ዮሐንስ 18፥36

በዚህም የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት ወደፊት ምን እንደሚመስል ለእኛ ለሰዎች ይታያል። የኢየሱስ ሥራ ጅማሬ ብቻ ነው። የተሰፋ ቃልም ነው። የእግዚአብሔር ዋና ዕቅድ በኢየሱስ ዘንድ አስቀድሞ የሚያበራውን ታላቅ ግብ ይይዛልና፦ ኢየሱስ የተዋጋው ነገር ሁሉ ከእንግዲህ የማይገኝበት አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር። እግዚአብሔር ከቤተሰቡ ጋር የሚኖርባት አዲስ ምድር።[46] በተለወጡና በታደሱ ሰዎች በእንክብካቤ የምትተዳደር አዲስ ምድር። በአምባገነኖችና በጨቋኞች አይደለም። የምሥራቹ ይህ ነው፦ ቄሳሮቻቸውና ፕሬዚዳንቶቻቸው ያሉባቸው የዓለም መንግሥታት ያልፋሉ። የእግዚአብሔር መንግሥት ይመጣል፤ ለዘላለምም ይኖራል።[47]

ከኢየሱስ ጋር ተጀምሯል። ዛሬ አለ። ከውጭ ሲታይ የተሰወረ ነው። የሚታይ ንጉሥ የለውም። በምሳሌው ውስጥ ወደ ሌላ አገር እንደሚሄደው ጌታ ንጉሡ ለጊዜው ሄዷል። መንግሥቱ መመለሱን ይጠብቃል።[48] ዛሬ «በሰውር የሚኖር» መንግሥት ነው። ያለ ድንበር። ያለ ዋና ከተማ። ከዓለም መንግሥታትና ከፖለቲካ መዋቅሮች ጎን ለጎን ይኖራል። ሰዎች በዚህ ለሌለው፣ ለማይታየው ነገር ግን እውነተኛ ንጉሥ ለሆነው ለኢየሱስ ታማኝነታቸውን በማሌበት ቦታ ሁሉ። እነርሱ ይህን መንግሥት ያለ ምንም ዓመፅ ይመሠርታሉ።[49] መሣሪያቸው ፍቅር ነው። ከሙታን የተነሣውና ወደ ሰማይ የተመለሰው ኢየሱሳቸው ዳግመኛ እስኪመጣ ይጠብቃሉ። እንዲህ ብሎ ቃል ገብቷልና።[50] የንጉሡ መመለስ – በይፋ፣ በሚታይ፣ በታላቅ ኃይል። ያን ጊዜ የዓለም መንግሥታት ሁሉ ያበቃሉ። በዓለም ሁኔታ ላይ በክፋት የሚሠሩ የማይታዩ ኃይላትም።

የምሥራቹ የፍቅርና የጽድቅ አገዛዙን በሚቃወም ነገር ሁሉ ላይ የእግዚአብሔርን ድል ያውጃል። በኢየሱስ ሕይወት ተጀምሯል። የእግዚአብሔር የመጨረሻ ድል ገና ይመጣል። ማንም ሊያስቆመው በማይችል ሁኔታ እየቀረበ ነው። መንግሥቱ አሁን አለ፤ ግን ገና ሙሉ በሙሉ አይደለም። ገና አይታይም። ኢየሱስ ዳግመኛ እስኪመጣ ድረስ ጊዜያዊና ምሥጢራዊ በሆነ መልክ ይኖራል። ቢሆንም የሚመጣው ነገር ቅምሻ አሁኑኑ አለ። በመንፈስ ቅዱስ ሰላምና ደስታ።[51] የወንጌል በመላው ምድር መስፋፋትና በየዕለቱ ራሳቸውን ለንጉሡ በምስጋና አሳልፈው የሚሰጡ ሰዎች የዚህን መንግሥት የማይታይ ሕልውና ይመሰክራሉ። እስከ ዛሬ ድረስ ያሉ ምልክቶች፣ ተአምራትና ፈውሶችም እንዲሁ።

---

46. ራእይ 21፥3-5
47. ዳንኤል 2፥44-45፤ 7፥26-27
48. ማቴዎስ 25፥14-30
49. ማቴዎስ 5፥43-48
50. የሐዋርያት ሥራ 1፥10-11
51. ሮሜ 14፥17

ወንጌል የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሆነና በሁሉ ላይ ጌታ እንደ ተደረገ የሚያውጅ ዐዋጅ ነው።[52] ወልድ በአብ ተላከ። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሊነበቡ የሚችሉትን የጥንት ትንቢቶች ሁሉ ፈጸመ። የዳዊት ዘር ሆኖ ሰው ሆነ። ስለ እኛና ስለ ኃጢአታችን ሞተ። ተቀበረ፣ ከሙታን ተነሣ፣ በእግዚአብሔርም ዙፋን ላይ ዘውድ ተቀዳጀ። ከዚያ ይገዛል። ሥልጣን ሁሉ ተሰጥቶታል። ኢየሱስ ክርስቶስ ነው!

የእግዚአብሔር ልጅ ወንጌል

ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ነው። አዲስ ኪዳን የክርስቶስ ወንጌል ብሎ ይጠራዋል።[53] ሐዋርያትና የኢየሱስ ደቀ መዛሙርትና ተከታዮች የሆኑት ሁሉ ይህን ሰበኩ።[54] የሰበኩት እርሱን ነው።[55] ይህ የመንግሥቱ ወንጌል ነው። እርሱ ንጉሥ ነው። ግን ከዚያም በላይ ነው። ንጉሥ ብቻ አይደለም የሚያሰፈልገን። አዳኝም ያሰፈልገናል።

አራቱ የሕይወት ታሪኮች ወንጌሎች የሚባሉት የምሥራቹ ሰለ ሆኑ ነው። በእነርሱ ውስጥ የሚያሰገርመው ነገር ኢየሱስ ራሱ ለመታወቅ ምንም ጥረት አለማድረጉ ነው። ንጉሥ እንዲያደርጉት እንኳ አይፈልግም።[56] የተፈወሱት ለማንም እንዳይናገሩ ይታዘዛሉ። ቢሆንም ይናገራሉ፤ ደስታቸው እጅግ ታላቅ ነውና።[57] ማንነቱን በእውነት የሚያውቁትን አጋንንት የያዟቸውን ሰዎች – በትክክል ለመናገር በውስጣቸው ያሉትን ርኩሳን መናፍስት – እንዳይናገሩ ይከለክላቸዋል።

በጥንቃቄ ሲታይ እርሱ ማን እንደ ነበረ በእውነት የተረዳ ማንም አልነበረም። በጣም የቀረቡት እንኳ። ጴጥሮስ፦ አንተ ክርስቶስ ነህ ቢልም፣[58] የተነገረውን የሚፈጽመው የሞተና ከሙታን የተነሣ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን አያውቅም።

ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሁለት ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ እንደሚገደል ይነግራቸዋል፤ እነርሱም ይደነቃሉ። ይህም በኢየሩሳሌም፣ በታላቁ ንጉሥ ከተማ።[59] በፈሪሳውያን፣ በሊቃነ ካህናትና በጸሐፍት ጥላቻ ምክንያት። በዚያው ጊዜ ከሦስት ቀን

52. የሐዋርያት ሥራ 2፥36፤ 3፥20-23፤ 10፥36
53. ሮሜ 15፥19፤ 1 ቆሮንቶስ 9፥12፤ 2 ቆሮንቶስ 2፥12፤ ፊልጵስዩስ 1፥27፤ 1 ተሰሎንቄ 3፥2
54. የሐዋርያት ሥራ 8፥4፣ 12፣ 25፣ 35፣ 40፤ 10፥36፤ 11፥20፤ 13፥38፤ 14፥7፣ 15፣ 21
55. የሐዋርያት ሥራ 5፥42፤ ኤፌሶን 3፥8፤ ፊልጵስዩስ 1፥17-18፤ ቆላስይስ 1፥28
56. ዮሐንስ 6፥15
57. ማርቆስ 1፥34፣ 43-45፤ 5፥43፤ 8፥26
58. ማቴዎስ 16፥13-20፤ ሉቃስ 9፥18-21
59. መዝሙር 48፥2፤ ማቴዎስ 5፥35፤ 21፥5

በኋላ ከሙታን እንደሚነሣ ይናገራል።[60]

ሁሉ ነገር ሊታሰብ በማይችል አሳዛኝ ፍጻሜ ሊያበቃ ነበር? ይህ የምሥራች ሊሆን ይችል ነበር? የሚገደል ንጉሥ?

ነገር ግን ኢየሱስ ሕይወቱን ቤዛ አድርጎ[61] ስለ ብዙዎች ሊሰጥ እንደሚገባ ይናገራል። ሕይወቱ እንደ መግዣ ዋጋ ተለውጦ። ብዙዎችን ለመቤዠት። ከባርነት ገዝቶ ነጻ ለማውጣት። ከኃጢአትና ከሞት እሰር ቤት። ከራስ ወዳድነት፣ ራስን ከመውደድ፣ ከሱሶች። ከማይታዩ ኃይላት ሥልጣን። ይህ ሞት ሁሉን የሚያጠቃልል፣ ዓለምን የሚለውጥ የመዳን ድርጊት ሊሆን ነበር። እደጋ አይደለም፤ ሽንፈትም አይደለም።

ሕይወቱ ያተኮረው አንድ ነገርን በመፈጸም ላይ ነበር፤[62] ይህም እንዲህ እርስ በርሱ የሚጋጭ የሚመስለው ነገር ነበር።[63] አስቀድሞ ያውቀው ነበር።[64] ለሰዎች ቤዛነት ዋጋውን ለመክፈል ዝግጁ ነበር። በገዛ ሕይወቱ። ስለ እነርሱ መሞት እንዲችል ሰው ሆነ።[65] መልካም ብቻ ያደረገና የተናገረ። ምንም ኃጢአት ያልነበረበት።[66] ከሁላችንም ፍጹም የተለየ። ራስን በመሰጠትና ባልንጀራን በማገልገል የተሞላ ሕይወት። ትንሽ እንኳ ራስ ወዳድነት የሌለበት። ፈጽሞ ሊያበቃ የማይገባው እጅግ ውድ፣ ንጹሕና ቅዱስ ሕይወት። ወንጌል የኢየሱስ ሕይወትና ሥራ ነው። የሥነ ምግባር ፍጽምናው ብቻ አይደለም። በኃጢአት፣ በበሽታ፣ በአጋንንት መያዝና በሞት ላይ ያደረገው ተቃውሞ፣ ውጊያና ድልም ጭምር ነው።

በሞቱ ጫፉን፣ ፍጻሜውን፣ እንዲያውም የመጨረሻ ድሉን ሊደርስ ነበር። ሁሉን የለወጠ ሞት። በጽንፈ ዓለም ውስጥ የሥልጣን ሽግግር።

ፍቅሩ ያሳምናል። ሰዎችን የሚያገኝበት መንገድ፣ እንደሚከተላቸው፣ እንደሚያነሣቸው፣ እንደሚፈውሳቸው፣ እንደሚያከብራቸው። ያለ ልዩነት – ትንንሾቹንና ታላላቆቹን፣ ሕሙማንንና ኃጢአተኞችን። የሚሰበከው ይህ ኢየሱስ ነው። የሞተው፣ ከሙታን የተነሣውና ሕያው የሆነው። ዛሬም በወንጌል ውስጥ ሳይታይ በብርቱ የሚሰማና የሚገኘው። ሰዎችን የሚያገኘው።

---

60. ማቴዎስ 16፥13-21፤ ማርቆስ 8፥27-32፤ ሉቃስ 9፥18-22፣ 44-45፤ 18፥31-34
61. መዝሙር 49፥7፤ ማቴዎስ 20፥28፤ ማርቆስ 10፥45፤ 1 ጢሞቴዎስ 2፥6
62. ሉቃስ 9፥51
63. ሉቃስ 12፥50፤ ዮሐንስ 17፥4፤ 19፥28-30
64. ዮሐንስ 18፥4
65. ዕብራውያን 2፥14
66. 2 ቆሮንቶስ 5፥21፤ 1 ጴጥሮስ 2፥22፤ ዕብራውያን 4፥15፤ 1 ዮሐንስ 3፥3፣ 5

ወንጌልን ያገኘ ኢየሱሰን ያገኛል። ያን ጊዜ በእሰራኤል ሲዘዋወር እንደ ነበረው ዛሬም በእውነት ሕያው ነው። አሁን በእግዚአብሔር ሰማያዊ ክብር የሚኖር ከሙታን የተነሣው ሆኖ። በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ። ነገር ግን የምሥራቹ በሚሰበክበት ቦታ ሁሉ በመንፈሱ በኩል ይገኛል። ማሰረጃውም ሰዎች በየዕለቱ በእምነት መታዘዝ ወደ ኢየሱስ መመለሳቸውና እርሱን መከተላቸው ነው።

አብ ወልድን ለኃጢአታችን ሰርየት – ማለትም ይቅርታ – አድርጎ ላከው። ዓለምን እንደሚወድ ማሰረጃው ይህ ነው። አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ዓለምን በማዳን አንድ ናቸው።[67]

ንጉሡና መስቀሉ

ኢየሱስ ትኩረቱን በፍጻሜው ላይ አደረገ። ጊዜው ያልደረሰ ፍጻሜ።[68] ነገር ግን በዚያው ጊዜ የአዲሰ ነገር ጅማሬ። እጅግ የሚበልጥ ነገር ጅማሬ። የመጣው ሕይወቱን ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ ነበር። ለብዙዎች ቤዛነት! ይህ የአባቱ የልብ ምኞትና ፈቃድ ነበር።[69] ኢየሱስም ይህን ፈቃድ ለመፈጸም ሁሉን አደረገ። ወደ ኢየሱስ ሕይወት የመጨረሻ ክፍል እንቅረብ። እጅግ ሊብራራ የማይችል ሰለ ሆነ በጥንቃቄና በትሕትና እናድርገው።

የንጉሡ መገደል

ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይጓዛል። ወደ ከተማዋ በሚወሰደው መንገድና ወደ ከተማዋ ሲገባ እንደ ንጉሥ፣ እንዲያውም ንጉሥ ሆኖ ይቀበሉታል። የእግዚአብሔር ንግሥና በመጨረሻ ይጀምራል?

ከተማዋ ተጨናንቃለች። ቁጥር ሰፍር የሌላቸው ተሳላሚዎች በመንገድ ላይ ናቸው። ሙሉ ሳምንት በዚያ ይቆያል።[70] ዛሬ የሕማማት ሳምንት ብለን እንጠራዋለን። ያሰተምራል፤ ከጸሐፍትም ጋር ዘወትር ይከራከራል። ሊያጠምዱትና ወደ ወጥመድ ሊያሰገቡት ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን በጥበቡ ደጋግመው ይረታሉ። የሃይማኖት መሪዎችን ግብዝነትና ፍቅር ማጣት ይገልጣል። በሕዝቡ ዘንድ ያለው ተጽእኖ ታላቅ ነው። በቤተ መቅደሱ ያደረገው ድርጊት – በቤተ መቅደሱ እደባባይ የገንዘብ ለዋጮችን ገበታዎች ለጥቂት ጊዜ በእጁ

67. ዮሐንስ 3፥16፤ 1 ዮሐንስ 4፥9-14
68. መዝሙር 102፥24
69. ሉቃስ 22፥42
70. ማቴዎስ 21-27

የገለበጠበት – ለሕዝቡ አለቆች ከአቅም በላይ ነው። የሚያስናክለውን የናዝሬት ሰው ከዓለም ለማስወገድ ዕቅድ ያወጣሉ።

ሐሙስ ማታ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የአይሁድን ቋሲካ ያከብራል። በዚህ የቋሲካ እራት ጊዜ አዲስ ነገር ይመሠርታል። እንጀራን ይወስዳል፣ ይቆርሰዋል፤ እንዲህ እያለም ለደቀ መዛሙርቱ ያካፍላቸዋል፦ ይህ ስለ እናንተ የሚሰጥ ሥጋዬ ነው። ከዚያም የወይን ጽዋ ወስዶ እንዲህ ይላል፦ ይህ ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈሰስ ደሜ፣ የአዲሱ ኪዳን ደም ነው።[71] በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ እነዚህ ቃላት ምን ያህል ሰፊና ጥልቅ እንደ ነበሩ አላስተዋሉም።

ከዚያ ሁሉ ነገር መንገዱን ይይዛል። ኢየሱስ በገዛ ደቀ መዝሙሩ አልፎ ይሰጣል።[72] ይያዛል።[73] በሊቃነ ካህናት ፊት ይቀርባል።[74] ለሮማዊው ገዢ ለጲላጦስ ተላልፎ ይሰጣል፤ ያለ በደልም ይፈረድበታል።[75] ያሠቃዩታል። ሁሉ ነገር ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ይመስላል። ኢየሱስ የኃይላት መጫወቻ ይሆናል። በጥልቅ ትርጉም እንዲህ ብሎ ነበር፦ ይህ የእናንተ ሰዓትና የጨለማ ሥልጣን ነው።[76] በመስቀሉ ድርጊት ውስጥ የታወቁት የሃይማኖትና የፖለቲካ መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የማይታዩ ኃይላትም ይሠሩ ነበር። ሁሉ ነገር በእግዚአብሔር ልጅና በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ተባበረ።

ሰውን የሚንቀው ትዕይንት በሰቅላት አበቃ። ኢየሱስ እጅግ ጨካኝ ከሆኑ የአገዳደል መንገዶች በአንዱ ተገደለ። በዚያ በማይረሳው ዓርብ።[77] በግራና በቀኝ ከሁለት ወንጀለኞች ጋር ይሰቀላል። ፀሐይ እጅግ ከፍ ባለችበት ከቀትር 6 ሰዓት እሰከ ከሰዓት በኋላ 9 ሰዓት ድረስ ጨለማ ይሆናል።[78] የተሰቀለው ኢየሱስ ይጮኻል፦ አምላኬ፣ አምላኬ፣ ለምን ተውኸኝ?[79] በዚያ ያልተለመደ ነገር ይሆናል። በመጨረሻ ኢየሱስ ከተሰሙት ቃላት ሁሉ የሚበልጡትን ቃላት ይጮኻል፦ ተፈጸመ![80] የግሪኩ ቃል tetelestai – ኢየሱስ ምናልባት በአራማይስጥ ጮኾ ተናግሮት ይሆናል – ትርጉሙ፦ ተልእኮው ተፈጽሟል ማለት ነው።

---

71. ማቴዎስ 26፥26-30፤ ማርቆስ 14፥22-26፤ ሉቃስ 22፥14-20
72. ማቴዎስ 26፥14፤ ማርቆስ 14፥10
73. ዮሐንስ 18፥1-11
74. ዮሐንስ 18፥12-24
75. ዮሐንስ 18፥28-19፥16
76. ሉቃስ 22፥53
77. ዮሐንስ 19፥17-24
78. ሉቃስ 23፥44
79. ማቴዎስ 27፥46
80. ዮሐንስ 19፥30

የመጣበት ነገር ሁሉ ተከናውኗል። ቤዛው ተሰጥቷል። ከእነዚህ ቃላት በኋላ ወዲያውኑ ሞተ። መንፈሱን በአባቱ እጅ ሰጠ።[81]

ሰቅላቱን የፈጸመውና ሁሉን በቅርብ ያየው ሮማዊው የመቶ አለቃ በጥልቅ ተነካ። እንዲህም አለ፦ ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበር![82]

ብዙዎች ለረጅም ጊዜ የፈለጉት ነገር በመጨረሻ ተፈጸመ። ሰዎች በልባቸው ያለውን ገለጡ። ከዚህ የከፋ፣ የሚያሰጠላና የጨከነ ሊሆን አይችልም ነበር። ዓመፅ፣ ጥላቻና የጨለማ ኃይላት ድል አድርገው ነበር።

በኢየሱስ ላይ ምንም በደል ሊገኝበት አልተቻለም። ንጹሑ የወንጀለኛ ሞት ይሞታል። በመከራው ሁሉ ኢየሱስ ራሱን አልተከላከለም።[83] ልመናው እቻ የሌለው ነው፦ አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው።[84] አብ የመከራውን መንገድ ከእርሱ ጋር ይሄዳል። ይህ ግን ከሞት አያድነውም። አብ ለገዛ ልጁ አልራራም።[85]

ኢየሱስ ቶሎ ይሞታል፤ ከእርሱ ጋር ከተሰቀሉት ቀድሞ። የአይሁድ ሸንጎ አባል የሆነው የአርማትያሱ ዮሴፍ አስከሬኑን ማንም ባልተቀበረበት በራሱ መቃብር ያኖረዋል።[86] በእርሱ ተሰፋ ላደረጉት ሁሉ ዓለማቸው ይፈርሳል። ተሰፋ የምትሞተው በመጨረሻ ነው ይባላል። አሁን ግን ሞታለች።

እሑድ ማለዳ የኢየሱስን አስከሬን ሸቱ ለመቀባት ወደ መቃብሩ የሚመጡት ሴቶች ናቸው። ግራ ይጋባሉ፦ ብዙ ቶን የሚመዝነው የመቃብሩ ድንጋይ ከመቃብሩ አጠገብ ተንከባሎ ተቀምጧል። በተከፈተው መቃብር ውስጥ የኢየሱስን ሥጋ አያገኙም። ባዶ ነው። አስከሬኑ ከእንግዲህ በዚያ የለም። በዚያ ፋንታ መላእክት አሉ፤ እንዲህም ይላሉ፦

እዚህ የለም። እንደ ተናገረው ከሙታን ተነሥቷል![87]

ከተጠበቀው በተለየ

ደቀ መዛሙርቱ መምህራቸው ከሙታን እንደ ተነሣ የሚገነዘቡት ቀስ በቀስ ብቻ ነው። ኢየሱስ ራሱን እስኪገልጥላቸውና እስኪያዩትና እስኪዳስሱት ድረስ። እርሱ ነው። ያው ነው፤ ቢሆንም በሆነ መንገድ የተለየ ነው። ከሙታን የተነሣ። አዲስ አካል። ቢሆንም በእጆቹና

81. ሉቃስ 23፥46፤ ዮሐንስ 19፥30
82. ማርቆስ 15፥39
83. ኢሳይያስ 53፥7፤ 1 ጴጥሮስ 2፥23
84. ሉቃስ 23፥34
85. ዮሐንስ 3፥16፤ ሮሜ 8፥32
86. ኢሳይያስ 53፥9፤ ሉቃስ 23፥50-56
87. ሉቃስ 24፥1-12፤ ዮሐንስ 20፥1-10

በእግሮቹ ላይ የችንካሮቹ ምልክቶች፣ በጎኑም ያለው ቁስል በግልጽ ይታያሉ። ከእነርሱ ጋር ይበላል፤ ነገር ግን በተዘጉ በሮች ያልፋል። አንድ ጊዜ እዚህ፣ አንድ ጊዜ እዚያ ይገኛል።[88] ለብዙ ደቀ መዛሙርት ይገለጣል። ለወንድሙ ለያዕቆብም።[89] ከሙታን ተነሥቶ በአዲስ ሕልውና የሚኖር እንደ መሆኑ ሌላ ነው፤ በዚያው ጊዜ ግን የእነርሱው ኢየሱስ ነው።

ሁሉን አስቀድሞ እንደ ነገራቸው መረዳት ይጀምራሉ። አሁን ከሙታን ከተነሣው ከኢየሱስ ጋር 40 ቀን አብረው ይሆናሉ። ብዙ ጥያቄዎችን ይመልሳል። ጥርጣሬያቸውን ያስወግዳል። እንደገና አቅጣጫ ይሰጣቸዋል። ለአዲሱ ተልእኮአቸው። ስለ መንግሥቱ ያስተምራቸዋል።[90] ስለ ሞቱ። ለምን መሞት እንደ ነበረበት። ይህን አስቀድሞ ተናግሮ ነበር፤ አሁን ግን ይበልጥ እየጠራ መጣ። ትርጉም የሌለው አሳዛኝ ክስተት አልነበረም። የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ማዕከሉ የሆኑበት የእግዚአብሔር ዋና ዕቅድ ነበር። ዓለምን ያናወጠ የመንፈሳዊ የመሬት መንቀጥቀጥ ማዕከል። የአዲስ ዘመን መዞሪያ ምሰሶ። በጽንፈ ዓለም ውስጥ የጦር ግንባርና የሥልጣን ለውጥ።

መስቀል ለምን ይህን የጽንፈ ዓለም ትርጉም ሊኖረው እንደሚገባ ይጠይቁ ይሆናል። መስቀል የሚያመለክተው ከዚህ በቀር ሌላውን ሁሉ ነው። በመስቀል ላይ የሚደረግ ሞት ዓለማው ሰውን ስብዓዊነቱን ማሳጣት፣ እጅግ ማዋረድና ከመታሰቢያ መደምሰስ ነው።

መስቀሉ በእግዚአብሔር ዓይን

መስቀሉን የምናየው ከሩቅ ነው። ከብዙ ዘመን በፊት የሆነ ድርጊት። በብዙ መንገድ ለእኛ እንግዳ በሚመስሉ ዓለምና ባህል ውስጥ። ነገር ግን ይህን መስቀል በትክክል ከተረዳነው በዚህ ሩቅ መስቀል ውስጥ እግዚአብሔር ለእኛ ቅርብ መሆኑን እናገኛለን።

ደቀ መዛሙርቱ የመሲሑ ሞት አደጋ እንዳልነበረ መረዳት ጀመሩ። የቤዛነታችን ዋጋ ነበር። ልክ እንዲህ ሊሆን እንደሚገባው ተገነዘቡ፤ ሰበኩም።[91] አስፈላጊ ነበር። ክርስቶስ የሞተው ስለ እኛ ነውና።[92] ሊገባ ለማይችለው ነገር ከጊዜ በኋላ ትርጉም ለመፍጠር አልሞከሩም። ራሳቸውንና ሌሎችን ለማጽናናት ብለው። ኢየሱስ ከሞቱ በፊትና በኋላ በተናገረው ነገር ተረድተው ነበርና። እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሙታን አስነሣው፤ ከፍም አደረገው። አሁን የዓለም የወደፊት ዕድል በእርሱ ላይ የተመሠረተ ነው። በመስቀሉ

88. ሉቃስ 24፥13-49፤ ዮሐንስ 20፥11-31፤ 21፥1-14
89. 1 ቆሮንቶስ 15፥5-7
90. የሐዋርያት ሥራ 1፥3
91. የሐዋርያት ሥራ 2፥22-24፤ 3፥18፣ 24፤ 8፥35፤ 9፥22፤ 13፥32፣ 38፤ 18፥28፤ 26፥23
92. 1 ቆሮንቶስ 15፥3፤ ገላትያ 1፥4፤ 3፥13፤ 1 ተሰሎንቄ 5፥10፤ ቲቶ 2፥14፤ 1 ጴጥሮስ 2፥24፤ 1 ዮሐንስ 3፥16፤ ራእይ 1፥5

ድርጊት፣ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረቡ፣ እግዚአብሔር ዓለምን ከራሱ ጋር እንዳስታረቀ ተገነዘቡ።[93]ኢየሱስ እንደ መሥዋዕት የዓለምን ኃጢአት እንደ ተሸከመና እንዳስወገደ።[94]

ኢየሱስ ራሱን ሳይከላከል አሳልፎ ስለ ሰጠ የእግዚአብሔር ፍቅር ምን ያህል ታላቅ እንደ ነበረ ግልጽ ሆነ። በመስቀል ላይ መልኩ በተበላሸውና በተሠቃየው ኢየሱስ ውስጥ የእግዚአብሔር እጅ ለዕርቅ ተዘርግቷል።

ስለ እኛ የተሠዋ

እስራኤል የእንስሳት መሥዋዕት ሥርዓት ነበራት። ሌሎች ብዙ ሕዝቦችም እንዲሁ። በከፊል እስከ ዛሬ ይገኛሉ። አዲስ ኪዳን የኢየሱስን ሞት እንደ መሥዋዕት ይገልጸዋል፤ የእስራኤል የእንስሳት መሥዋዕቶች ሁሉ ፍጻሜ እንደ ሆነ አድርጎ።[95] ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፤ ኢየሱስ የፈጸመውን እንድንረዳ ለእኛ የተሰጠ እገዛ። የመሥዋዕት ሐሳብ ከአምልኮ ሥርዓት ውጭም የማይታወቅ አይደለም። አንድ ሰው ሌሎችን ለማዳን ራሱን አሳልፎ ሲሰጥ።

የመሥዋዕት እንስሳት በመሠዊያው ላይ በጸጥታ ይታረዱ ነበር። ኢየሱስን ግን ሰዎች ገደሉት። በቀላሉ ወይም በፍጥነት አልሞተም። በግፍ ተገደለ። የመሥዋዕት ባሕርይ ደም ማፍሰስንና ሞትን ይጨምራል፤ መከራንና ጭካኔን ግን አይጨምርም። የኢየሱስ ሞት ሆን ተብሎ የተፈጸመ የዓመፅና የክፋት ድርጊት ነበር። በመስቀል መሞት ሌሎችን ለማስፈራራት የታሰበ ነበር። ሰዎቹ ቢገነዘቡትም ባይገነዘቡትም በኢየሱስ ላይ ያደረጉት ዓመፅ በእግዚአብሔር ላይ የተደረገ ዓመፅ ነበር።

እግዚአብሔር ራሱ ለዓለም ዓመፅ የሰጠው ምላሽ የክፋት ኃይላት እንዲሻሩ ማድረግ ነበር። በመታገሥና በመዋጥ። ስለዚህ ኢየሱስ ጥቃት ሲደርስበት ራሱን አለመከላከሉ እጅግ ታላቅ ትርጉም አለው። ይቅርታ የውስጥ ሕመምን መታገሥንና መዋጥን ይጨምራል። መራርነት፣ ቂም፣ ጥላቻና በቀል እንዳይነሡም እምቢ ማለትን። እግዚአብሔር ንጹሕ ተጠቂ ሆኖ ወደ ዓለም ይመጣል። በመጨረሻ የመሥዋዕቱ ሞት ልዩ መሆን ነበረበት። የእምልኮ ሥርዓት የእንስሳት መሥዋዕት ብቻ አይደለም። በመጨረሻ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች በእርግጥም የእውነተኛው መሥዋዕት ጥላዎች ብቻ ነበሩ።

---

93. 2 ቆሮንቶስ 5፥19-21
94. ዮሐንስ 1፥29፣ 36
95. ኤፌሶን 5፥2፤ ዕብራውያን 7፥27፤ 9፥14፣ 26፤ 10፥12፣ 14

ኢየሱስ በኃጢአታችን ምክንያት ሞተ፤ ከሁሉም በላይ ግን ስለ ኃጢአታችን ሞተ።[96] የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር የመሥዋዕት በግ ነበር።[97] እንደ መሥዋዕት ከኃጢአታችን፣ ከርኩሰታችን እንድንነጻ ብቸኛው መንገድ እርሱ ነው። ወደ ቅዱሱ አምላክ ፊት ለመቅረብ።

መሥዋዕት የሚያቀርበው ሰው እጆቹን በመሥዋዕቱ ላይ በመጫን ወይም በማሳረፍ ራሱን ከመሥዋዕቱ ጋር ያንድ ያደርጋል። እንድ ነገር ወደ መሥዋዕቱ ይተላለፋል። እድፉ፣ ርኩሰቱ ወደ መሥዋዕቱ ተላለፈ፤ በዚህም ተደመሰሰ። መሥዋዕቱ እንድ ዓይነት ምትክ ይሆናል። መሥዋዕት – በትክክል ለመናገር የመሥዋዕቱ ደም – ኃጢአትን ሊያስተሰርይ ይችል ነበር። ስርየት ማለት ኃጢአታችን ይደመሰሳል ማለት ነው። ያደረሰው ጉዳትም ይሻራል። ኃጢአት ይሸፈናል፤ ኃይሉ ይሰበራል። የተሰበረው ይፈወሳል።

ኢየሱስ የእነሰሳት መሥዋዕቶች ሁሉ የሚያመለክቱትን ፈጸመ። በዚያው ጊዜም አስቀራቸው።[98] አላስፈላጊ አደረጋቸው። አሁን ኃጢአት የሌለበት ሰው ስለ ኃጢአታችን ሞተ። ፍጹም የሆነው ስለ ኃጢአተኞች። ኃጢአታችንን፣ መተላለፋችንንና ክፋታችንን፣ በእግዚአብሔርና በሰዎች ላይ የፈጸምናቸውን ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ጥፋቶች፣ አለመታዘዛችንን – ይህን በራሱ ላይ ወሰደ። እርሱ ራሱ እንዳደረገው ሆኖ። ይህንንም ለዘላለም አስወገደው።[99] ወደ ሞቱ ውስጥ። በመስቀሉ ላይ የኃጢአታችንንና የኃጢአቶቻችንን ሸክም ተሸከመ። በዚያ በመስቀሉ ላይ እግዚአብሔር በልጁ አካል ኃጢአትን ኮነነ፤ እንዲያውም ፈረደበት።[100] ስለዚህ ሞቱ እንደ ሌሎቹ የተሰቀሉ ሰዎች ሞት አልነበረም። እዚህ ኃጢአተኛ ሳይሆን አንድ ሰው የኃጢአተኛን ሞት ሞተ። በኃጢአታችንና በዓመፃችን የተጫነ መሥዋዕት ሆኖ። ከመላው ዓለም ኃጢአት ጋር አንድ መደረግ ሊቋቋሙት የማይቻል ድርጊት ነው። ስለ ሌሎች የኃጢአትን ኩነኔ በራሰ ውስጥ መሸከም በዓለም ካለ ከማንኛውም ሕመምና ከማንኛውም ገጠመኝ ጋር ሊወዳደር አይችልም።[101] አንድ ጊዜ ብቻ የሆነ ድርጊት ነው። ሰውን እጅግ በሚጠላ፣ በአሰቃቂ የሰቅላት አካባቢ ውስጥ። ዋጋው ይህ ነበር። በሁለት ሌሎች መሰቀሎች መካከል በቆመው በዚህ መሰቀል ላይ በዘመናት ሁሉ ታላቁ መከራ ተፈጸመ።

---

96. 1 ቆሮንቶስ 15፥3
97. ዮሐንስ 1፥29፣ 36፤ 1 ጴጥሮስ 1፥18-21
98. ዕብራውያን 7፥27፤ 9፥26፣ 28፤ 10፥10፣ 14
99. ዕብራውያን 8፥12፤ 10፥17፣ ሚክያስ 7፥19
100. ሮሜ 8፥3
101. ሮሜ 8፥3፤ 2 ቆሮንቶስ 5፥21

ይህ መከራ የወደፊቱ ጊዜ በሰው ልጅ እጅ እንዳለ ዋስትና ነው። እግዚአብሔር ራሱ በራሱ ላይ የወሰደው የመከራ ጥልቀት ምሥጢር ሆኖ ይቀራል። እግዚአብሔር ራሱ ብቸኛውን የሚቻል መፍትሔ ያዘጋጀል፦ የልጁን ልዩ መሥዋዕት። እኛ ፈጽሞ መመለስ ወይም ማከናወን ያልቻልነውን ይፈጽማል።

ኢየሱስ ስለ እኛና ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሆኖ ራሱን መስጠቱ ለእኛ ያለው ወሰን የሌለው ፍቅር፣ ልግስናና ሞገስ ማሰረጃና መሠረት፣ መነሻም ነው።

የሞተ፣ በሞት የቀረ ክርስቶስ አይረዳንም።[102] ሁሉን የሚወስነው ጥያቄ ቀረ፦ እግዚአብሔር የልጁን መሥዋዕት በእርግጥ ተቀበለው?

አዎን! ከሙታን አስነሣው። የኢየሱስ ከሙታን መነሣት ከተአምር በላይ ነው። ከቃለ አጋኖ ምልክት በላይ ነው። እግዚአብሔር ይህን ልዩ መሥዋዕት በደስታ እንደሚቀበልና አሁን ኃጢአተኞችን ጻድቃን ብሎ ሊያውጅ እንደሚችል ያውጃል።[103] ያለ ቅድመ ሁኔታ ጸጋን እንደሚያሳይና ይቅር እንደሚል ማለት ነው። ኃጢአተኞችንም ጻድቃን እንደሚያደርግ።[104] ፈጽሞ ኃጢአት እንዳልሠሩ ሆነው።

እግዚአብሔር መሥዋዕት ያስፈልገዋል?

ስለ ክርስቶስ መስቀል ማለቂያ በሌለው ሁኔታ ማሰብ ይቻላል። እርስዎስ እንዲህ ብለው ጠይቀው ያውቃሉ፦ እግዚአብሔር መሥዋዕት ያስፈልገዋል? ወይም የፍቅር አምላክ ቁጣውን ለማብረድ መሥዋዕት የሚጠይቀው እንዴት ሊሆን ይችላል?

በመጀመሪያ ይህ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል፦ መሥዋዕት ያስፈለገን እኛ ነን። እግዚአብሔር አይደለም። ችግር የነበረብን እኛ ነን። እግዚአብሔር አይደለም። ኃጢአት ሠርተናል፤ ለሰርየት፣ ለካሳ መሥዋዕት ማቅረብ በተገባን ነበር። ሰርየት ተላላፊው ኃላፊነት የሚወሰድበት ነገር ነውና። ነገር ግን ሁኔታውን ሊያስተካክል የሚችለው ብቸኛው እግዚአብሔር ራሱ ነው። እርሱ ዋጋውን ይከፍላል። ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ለማደስ። ይቅር ለማለት ዝግጁና ፈቃደኛ በመሆን። እግዚአብሔር በኢየሱስ የሚያደርገው ይህንኑ ነው።

እኔም ያለ ደም መሥዋዕት አይቻልም ወይ ብዬ ጠይቄ ነበር። በተለይ ያለ ኢየሱስ አስቃቂ የመስቀል ሞት። ኢየሱስ ከመስቀሉ ጥቂት ቀደም ብሎ በጌቴሴማኒ የአትክልት ሰፍራ

102. 1 ቆሮንቶስ 15፥17
103. ሮሜ 4፥24-25፤ 1 ቆሮንቶስ 15፥3
104. ሮሜ 3፥21-26፤ 5፥1፣ 9

ይጸልያል፤ ይማልዳልም። ደንግጦና ተጨንቆ። ሁሉ የሚቻለውን አባቱን መሰቀሉ ይቅርለት እንደ ሆነ ይለምነዋል። የመከራው ጽዋ ከእርሱ እንዲያልፍ። ኢየሱስ ግን የአባቱን ፈቃድ ይፈጽማል። ያለ ተቃውሞ ወደ ሐሰተኛው ፍርድና ወደ መሰቀሉ ድርጊት ይሄዳል።[105]

በእትክልቱ ሰፍራ የተነገሩት ቃላት ለጥያቄያችን መልስ ይሰጣሉ፦ ያለ መሰቀሉና ያለ ኢየሱስ ሞት የእግዚአብሔርን የማዳን ፈቃድ መፈጸም አይቻልም ነበር። በእርግጥም ለእግዚአብሔር ሁሉ ይቻላል – እርሱ ግን ወደ መዳን የሚያደርሰ የራሱ መንገድ አለው። ጽንፈ ዓለሙ የእርሱ ነው፤ ዓለሙም የእርሱ ነው። የሕይወትን ሕጎችና ሁኔታዎች የሚወስነው እርሱ ነው። ምትክ ያሰፈልገን ነበር። ከሙታን የሚነሣና ከእርሱ ጋር ወደ ሕይወት የሚጎትተን ነጻ አውጪ ያሰፈልገን ነበር። የሞትን ኃይል የሚያሸንፍ ነጻ አውጪ ያሰፈልገን ነበር – በሞቱ። ወደ ሞት ጠላት ምሽግ ሰብሮ የሚገባና እሰራቱንና በሮቹን የሚሰባብር።

የእግዚአብሔር ፍቅርና የኢየሱስ ፍቅር ከመከራው ይበረታሉ። ኢየሱስን ከልክ በላይ ያሰፈራው ምን ነበር? ሮማውያን በመሰቀል ላይ የሚፈጽሙበት ግድያ? በእርግጥ። ግን ደግሞ ከኃጢአታችን ጋር አንድ መደረጉ ጭምር። ኃጢአታችንን መሸከሙ። ራሱ ምንጩና አድራጊው እንደ ሆነ። ታላቁና ለእኛ የማይታሰበው ነገር በዚህ ውሰጥ ነው። በዚያ ቀን በጎልጎታ ከነበሩት ማንም ያልተረዳው፣ ያልጠረጠረውም እንኳ ነገር። በመሰቀሉ ላይ ወሰን የሌለው የእግዚአብሔር ፍቅርና ቅድሰና፣ ቁጥር ሰፍር የሌላቸው የዓለም ኃጢአቶች፣ የሰዎች ጥላቻና የጨለማ ኃይላት ይገናኛሉ። ኢየሱስ ይህን መቋቋም አለበት። መሸከምና መታገሥ። ከእርሱም ጋር ወደ ሞቱ መውሰድ።

የእግዚአብሔር የማዳን ፈቃድ ያለ መሰቀሉ ቢቻል ኖሮ ይህ በጎልጎታ የሆነው ፍጻሜ ባልኖረ ነበር! መሰቀሉ የታሪክ መዞሪያ እንደ መሆኑ እርሰ በርሱ የሚጋጭ ምሥጢር ሆኖ ይቀራል። ለእኛ ግን የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ መሆኑን ያሳያል። እንደገና፦ የእርሱ መንገድ ይህ ነው።

የሰዎች ፈጠራ አይደለም። የኢየሱስ ክርሰቶስ መሰቀል ለተሰበረች ዓለም የእግዚአብሔር መልስ ነው። ክርስቲያኖች፣ የኢየሱስ ተከታዮች ሰለ መሰቀሉ ይቅርታ መጠየቅ አያሰፈልጋቸውም። ማሰናከያ ሆኖ ይቀራል። ለማያምኑት ተቀባይነት ባለው መልክ ወይም አመክንዮ ሊቀርብ አይችልም።

እግዚአብሔር እንዲረጋጋ ወይም ቁጣውን ለማብረድ መሥዋዕት ያስፈልገዋል ወይ ለሚለው ጥያቄ እንዲህ ብሎ መመለስ ይቻላል፦ ሁላችንም ከእግዚአብሔር ቁጣ በታች

105. ማቴዎስ 26፥36-46፤ ማርቆስ 14፥32፤ ሉቃስ 22፥39

ነን።[106] የእግዚአብሔር ቁጣ ተገልጧል፤[107] በሚመጣውም ፍርድ ይታያል።[108]

ነገር ግን እግዚአብሔር ለቁጣ የዘገየ ነው።[109] ቁጣውን ይገታል። ክፋትን በራሱ ላይ ይወሰዳል፤ ቅጣትንም ይተዋል። ይቅርታ ከመሸከምና ከመታገሥ ጋር የተያያዘ ነው። እግዚአብሔር ራሱ የሕዝቡን የእስራኤልን ዓመፅ ብዙ ጊዜ ታግሿል። ጎልጎታ ጫፉ ነው። በዚያ እግዚአብሔር የሕዝቡን ኃጢአት ይታገሣል፤ እኛ ሰዎች ሁሉን ብንችል ኖሮ የምንሰጠውን ምላሽም ይተዋል። እግዚአብሔር ግን ዝም ይላል። በጌቴሴማኒ የቀረበውን ጸሎት አይመልሰም፤ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያቀረበውን ጸሎት እንጂ፦ አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው።[110]

በመስቀሉ ላይ እግዚአብሔር ቁጣውን ያሰቆማል። ይገታዋል! መስቀሉ የእግዚአብሔር ቁጣ ፍጻሜውን የሚያገኝበት ሰፍራ ነው። ተገቢው ቁጣው የሚነድበት ሰፍራ አይደለም፤ የሚጠፋበት እንጂ። ማሰረጃው ያለ መከላከል ራሱን አሳልፎ መሰጠቱ ነው። እንደ ተሰቀለ አምላክ።

ማስናከያ ነው። ለእኛ ግን ቁጣና ዓመፅ የሚጠፉበት የኒውክሌር ማዕከል መቅለጥ ነው። የኃጢአትና የሞት ኃይል ደሙ ፈሰሶ ማለቁ።

በ1986 (እ.ኤ.አ.) በቼርኖቤል የኒውክሌር ማብላያ በፈነዳ ጊዜ ከዚያ የሚበልጥ አደጋ ተጋርጦ ነበር። ከጋለው ማብላያ ሥር በውኃ የተሞላ ገንዳ ነበር። የቀለጠው ነገር ወደዚያ ቢፈሰስ ኖሮ ኃይለኛ የእንፋሎት ፍንዳታ እጅግ የበዛ ጨረር ይለቅ ነበር። ሦስት ሰዎች በፈቃዳቸው ቀረቡ። በጨረር ወደ ተበከለውና በውኃ ወደ ተጥለቀለቀው ምድር ቤት ወረዱ። በዚያም ውኃው እንዲፈስስ ቫልቮቹን በእጃቸው ከፈቱ። በሕይወት እንመለሳለን ብለው አላሰቡም። ቢሆንም ሄዱ። ለዩክሬን፣ ለአውሮፓ። ያደረጉት ጥረት አደጋውን አስቀረ። ሦስቱም በሕይወት ተረፉ።

እንዲሁ ኢየሱስ በማይታሰብ መንገድ ስለ እኛ አደጋውን ያመጣው ነገር ሆነ፦ ኃጢአት።[111]

106. ዮሐንስ 3፥36፤ ሮሜ 3፥5፤ ኤፌሶን 2፥3
107. ሮሜ 1፥18
108. ሮሜ 2፥5፣ 8፤ 5፥9፤ ቆላስይስ 3፥6፤ 1 ተሰሎንቄ 1፥10
109. ዘጸአት 34፥6፤ ዘኁልቁ 14፥18
110. ሉቃስ 23፥34
111. 2 ቆሮንቶስ 5፥21

ክፉው በመልካም ተሸነፈ

በክርስቶስ ክፋት ፍጻሜውን ያገኛል፤ በራሱ ላይ ይወሰደዋልና። የሰዎችን ክፋት ይታገሣል። በድካም ይሰቀላል።[112] ነገር ግን የእግዚአብሔር ድካም ይበረታል።[113] ፍቅሩ በክፋት ሊጠፋ አልቻለም። ክፉውን በመልካም አሸነፈ። ጠላትን በመውደድ። ፍቅሩ ይበልጥ ብርቱ ነበር፤ አሸነፈም! ክፋት የቻለውን ያህል ተቆጣ፤ ቢሆንም ተሸነፈ። ከሙታን በተነሣው ውስጥ የእግዚአብሔር እጅ ለዕርቅ ተዘርግቶ ይቀራል።

እግዚአብሔር በክርስቶስ፣ ራሱን መሥዋዕት በሚያደርግ ፍቅሩ፣ ዓመፃችንን በራሱ ላይ ወሰደ። ከተበላሸውና ኃጢአተኛ ከሆነው ተፈጥሮአችን፣ በሥልጣን፣ በበቀልና በብድራት ከተቀረጸ ልብም ሊቤዠን።

በመስቀሉ ላይ እግዚአብሔር እያዳነና እያሰታረቀ ይገኛል።[114] በተሰቀለው ውስጥ። በሦስት አካላት ያለ አንዱ አምላክ – አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ – በመስቀሉ በኩል የዘላለም መዳንን አዘጋጀ።[115] በኢየሱስ ደም ሰርየት ሆነ። ኃጢአታችንን ይሸፍናል።[116] በመስቀሉ ላይ ኃጢአት እንደ ኃይል ሞት ተፈረደበት፤[117] እኛ አዲስ ሕይወት እንድንኖር። ኃጢአታችን ይቅር መባሉ ብቻ ሳይሆን የኃጢአት ኃይልም እንዲሰበር። ከእንግዲህ ሕይወታችንን በበላይነት እንዳይቆጣጠር።

የመስቀሉ የምሥራች ይህ ነው። በሦስት አካላት ያለ አንዱ አምላክ በመስቀሉ ላይ በራሱ ውስጥ አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ ያደርጋል – ሰለ እኛ!

112. 2 ቆሮንቶስ 13፥4
113. 1 ቆሮንቶስ 1፥25
114. 2 ቆሮንቶስ 5፥19
115. ዕብራውያን 9፥14
116. 1 ዮሐንስ 2፥2
117. ሮሜ 8፥3



ወሰን የሌለው የእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል

የእግዚአብሔር ታላቅነት በትሕትናው ይታያል። በሚያገለግልና ራሱን አሳልፎ በሚሰጥ ፍቅር። እግዚአብሔር በክርስቶስ ወደ መሰቀል ሲሄድ ከባሕርዩ ውጭ አይሠራም። እንደ ማንነቱ ይሠራል። ከጎልጎታ ወዲህ ፍቅሩ መልክ አለው፦ የመሰቀል መልክ። መልካሙን የሚፈልግና ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ፍቅር። መሰቀሉ የፍቅሩ ታላቅ መገለጥ ከሆነ እግዚአብሔር ሁልጊዜም እንዲህ ነበር። ሁልጊዜም እንዲህ ይሆናል።

በመሰቀሉ ላይ እግዚአብሔር ጥበቡን ያሳያል። ሞኝም ይመስላል። በመሰቀሉ ላይ እግዚአብሔር ኃይሉን ያሳያል። ራሱንም ኃይል የሌለው ያደርጋል። በመሰቀሉ ላይ እግዚአብሔር ውበቱን ያሳያል። መልኩም እንዲበላሽ ይፈቅዳል። በመሰቀሉ ላይ እግዚአብሔር ፍቅሩን ያሳያል። ከኃጢአታችን መዘዞች ጋር ራሱን አንድ ያደርጋል። ከዚህ ይበልጥ ከእግዚአብሔር መራቅ አይቻልም። ዝቅ ብሎ የሚጎነበሰው ወደዚያው ነው።


መሰቀሉ የእግዚአብሔር ኃይል ነው።[118] ይህ የሚያስደንቅ ነው። ጳውሎስ እንደሚለው እግዚአብሔር ኃይሉን ሲያሳይ እንዲህ ይመስላል፦ ኢየሱስ አምላክ በመሆኑ ያሉትን መብቶች ይተዋል።[119] ሊቆሰል የሚችል ሰው ይሆናል። የሚሰቅሉትን ሰዎች በደልና ኀፍረት

118. 1 ቆሮንቶስ 1፥18
119. ፊልጵስዩስ 2፥6-8

በራሱ ላይ ይወሰዳል። ስለ ኃይል እንዲህ አናስብም። ብዙ ክርስቲያኖችም ይህን በቁም ነገር አልወሰዱትም።

ስለ ኃይል ስናስብ ግዳጅንና ዓመፅን እናስባለን። ስዎች አማልክቶቻቸውን እንዲህ አድርገው ያስባሉ። መስቀሉ ተቃራኒውን ያሳያል። በመስቀሉ ላይ ያለው የእግዚአብሔር ኃይል ልባችንን ለማግኘት የሚደረግ ልመና ነው። ፍጹም በተለየው ባሕርዩ። ራሱን አሳልፎ በሚሰጥ ፍቅር።

በድካም ተሰቀለ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ድካም ከስዎች ብርታት ይበረታል።[120] በሥልጣን ሕጎች ሳይሆን በፍቅር ሕግ! ጠላትን በመውደድ ሕግ።



መስቀሉ የሚሰጠን

መስቀሉ እኛ ስዎች ምን ማድረግ እንደምንችል ያሳያል። በእግዚአብሔር ላይ ባለን ዓመፅ፣ እያወቅንም ሳናውቅም በሕይወታችን ባለ ሥርዓት አልበኝነት።[121] እግዚአብሔር ቦታ በሌለው ቦታ። ወይም ትንሽ ሚና ብቻ በሚጫወትበት ቦታ። ነገር ግን እንደ ጠላቶች

120. 1 ቆሮንቶስ 1፥25፤ 2 ቆሮንቶስ 13፥4
121. 1 ዮሐንስ 2፥15-17፤ 3፥4

ለሚቃወሙትም እነኳ እግዚአብሔር ልጁን ለሞት እስከ መሰጠት ድረስ ለመሄድ ከልቡ ጥልቀት ዝግጁ ነው።[122] ጠላትነትን ወደ ዕርቅና ሰላም ለመለወጥ።

ከሞትና ከኃጢአት ነጻ ሊያወጣን ብቸኛው ኃጢአት የሌለበት ሞተ፤ እንደገናም ሕያው ሆነ። እግዚአብሔር ክርስቶስ ያደረገውን ለእኛ ያስተላልፋል። ሞቱ ሞታችን ነው፤ ትንሣኤውም የእኛ ነው። ከእርሱ ጋር ሞተናል፤ ከሙታንም ተነሥተናል![123] በመስቀሉ ላይ ራሱን ከእኛ ጋር አንድ አደረገ። ከክርስቶስ ጋር ተዋሕደናል። ሞቱ ሞታችን ነው። የእርጌው ኃጢአተኛና የወደቀው ሕይወታችን ፍጻሜ። ትንሣኤውም ትንሣኤያችን ነው። ከመንፈሳዊ ሞት[124] ወደ አዲስና ዘላለማዊ ሕይወት ተነሥተናል። አዲስ ጅማሪ የሚቻለው በመስቀሉ፣ በክርስቶስ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ኃጢአትንና ክፋትን ከዓለም ሊያስወግድ ቢፈልግ ኖሮ ሰዎችን ከዓለም ማስወገድ በተገባው ነበር። ምክንያቱም ኃጢአት ለይተን በቀዶ ሕክምና ልናወጣው የምንችለው የእኛ አንድ ክፍል አይደለም። ከራስ እስከ እግር ኃጢአተኞች ነን። ነገር ግን እግዚአብሔር የኃጢአተኛውን ሞት አይፈልግም![125] በሞቱ ውስጥ ያለ እግዚአብሔር የነበረው አርጌው ሕይወታችን ሞተ። በሞቱ ውስጥ ተቀበረ። ወደ አዲስ ሕይወት ተነሥተናል።

መስቀሉ – ሞኝነት

በመስቀሉ ላይ ሰዎች ይለያያሉ። ለእንዳንዶች ሞኝነት ነው። በመስቀል ላይ በሥቃይ የሚሞት የዓለም አዳኝ የእግዚአብሔርን መንግሥትም ሆነ መዳንን ሊያመጣ አይችልም። በዓለም ያለ ማንም ሃይማኖት መሥራቹን በውርደት ከሕይወት ስለ ተለየ አያከብረውም።

ለሚያምኑት ግን ከሁሉ የሚበልጥ ነው፦ የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ። መስቀሉ ለእነርሱ መዳን፣ ዕርቅ፣ ይቅርታ፣ ነጻነት ማለት ነው።[126] ይህን የመስቀል እውቀት በሰው ውስጥ ሊሠራ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ያለ አስናካዩ መስቀል ወንጌል የምሥራች አይደለም። ከመስቀሉ ጋር ብቻ ለመዳን የሆነ የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ለማዳን። የተሰቀለው ብቻ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብ፣

122. ሮሜ 5፥6-10
123. ሮሜ 6፥1-14፤ ኤፌሶን 2፥1-10፤ ቆላስይስ 2፥11-14፤ 3፥1-4
124. ሉቃስ 15፥32
125. ሕዝቅኤል 18፥23፣ 32
126. 1 ቆሮንቶስ 1፥18፣ 23-24

ጽድቅ፣ ቅድሰናና ቤዛነት ይሆንልናል![127] በአንድ ሞት፣ በሕዝብ ፊት በተፈጸመ ግድያ፣ ታላቅ መዳንን ማዘጋጀት የእግዚአብሔር ጥበብ ነው፦

- ድልና ነጻነት፣ የሥልጣን ለውጥ[128]
- ሰርየት[129]
- ዕርቅ[130]
- ይቅርታ[131]
- የዘላለም ሕይወት[132]
- ቤዛ[133]
- ቤዛነት[134]
- ፈውስ[135]
- ከሁሉ የሚበልጠው የፍቅር ማሰረጃ[136]
- ምሳሌ[137]
- አንድነት[138]

ለክርስቲያኖችም አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ጥበብ ከአቅማቸው በላይ ነው። ወሳኙ ነገር ሰለ መስቀሉ የሚረዱትና የሚያምኑት አይደለም። እጅግ የሚበልጠው በመስቀሉ በኩል ለዓለም መዳንን በሚሰጥ አምላክ መታመናቸው ነው። የሚያድነው እውቀት አይደለም፤ በዚያ አንዱ ሰለ እኛ ሁሉን እንዳስተካከለ ማመን አንጂ።

በመስቀሉ በኩል በሚያገኘን አምላክ ይታመናሉ?

---

127. 1 ቆሮንቶስ 1፥30
128. የሐዋርያት ሥራ 26፥18፤ ቆላስይስ 1፥12-13፤ 2፥15፤ ዕብራውያን 2፥14-15
129. ሮሜ 3፥24-26፤ 8፥3፣ 32-34፤ ገላትያ 3፥13፤ ኤፌሶን 5፥2፤ ዕብራውያን 2፥17፤ 1 ዮሐንስ 2፥2፤ 4፥10
130. ሮሜ 5፥10፤ 2 ቆሮንቶስ 5፥18-20፤ ቆላስይስ 1፥20-22
131. የሐዋርያት ሥራ 2፥38፤ ኤፌሶን 1፥7፤ ዕብራውያን 10፥18
132. ዮሐንስ 3፥14-16፤ 6፥51-56
133. ማቴዎስ 20፥28፤ ማርቆስ 10፥45፤ የሐዋርያት ሥራ 20፥28፤ 1 ቆሮንቶስ 6፥20፤ 1 ጢሞቴዎስ 2፥5-6
134. ኤፌሶን 1፥7፤ 5፥25፤ ቲቶ 2፥14፤ ዕብራውያን 9፥12፤ 1 ጴጥሮስ 1፥18-19፤ ራእይ 1፥5-6፤ 5፥9
135. ኢሳይያስ 53፥5፤ 61፥1፤ ሉቃስ 4፥18-19፣ 23
136. ዮሐንስ 3፥14-16፤ 10፥11፤ 15፥13፤ ገላትያ 2፥20፤ 1 ዮሐንስ 3፥16፤ 4፥10
137. ኤፌሶን 5፥2፤ ፊልጵስዩስ 2፥5-11፤ 3፥10-11፤ 1 ጴጥሮስ 2፥21-24፤ 1 ዮሐንስ 3፥16
138. ዮሐንስ 11፥52፤ 12፥24፤ ኤፌሶን 2፥16

ወደ ቤት መመለስ

በተሰቀለው ክርስቶስ የሚታመን ይድናል። ለእርሱ ሁሉ ነገር ይለወጣል። እንደ ጠፋ ልጅና እንደ ጠፋች ልጅ በሰማያዊው አባት እቅፍ ውስጥ ይገባል። የእግዚአብሔር ወንድ ልጅና ሴት ልጅ ይሆናል።[139] ከመሰቀሉ በስተኋላ የአባቱ ታላቅ የበረከት ብዛት ይጠብቃል።[140] ከልጁ ጋር ሁሉን ይሰጠናል።[141] በመሰቀሉ በኩል ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መልሶ ይመራናል።[142] ወደ አባታዊ ልቡ።[143] ወደ ኅብረቱ።[144]

በፈቃዱ ቦታችንን ያዘ። ከመዘዘቹ ሁሉ ጋር። የኃጢአታችን ደመወዝ፣ የሥራችን ውጤት ሞት ነውና።[145] ስለዚህ ጻድቁ ስለ ዓመፀኞች ሞተ። ምትካችን ሆኖ።

ወደ ቤት ተመልሰዋል? ገና እያመነቱ ነው? አባት በየቀኑ እርሰዎን በጉጉት ይጠባበቃል። እርሰዎን ይጠብቃል!

የእግዚአብሔር ጸጋ ወንጌል

ሁላችንም ኃጢአተኞች እንደ ሆንን ደጋግመው ማንበብን ገና ይችሉታል? ሰው በዚህ ቢቆጣ ትክክል አይደለም? ይመኑኝ፦ ጉዳዩ እኛን ማዋረድ አይደለም። ይህን ምርመራ የሚሰጠው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። እውነትን ይናገራል። እውነትም ነጻ ያወጣናል።

ኃጢአተኛ መሆንን ማወቅና መቀበል ማለት ይህ ነው፦ ሙሉ በሙሉ አበላሽተነዋል። ሊጠገን አይችልም። መውጫ መንገድ የለም። ሁኔታችን አሰቢ ነው። ከሞት አናመልጥም። ከሁኔታችን ነጻ ሊያወጣን የጎልጎታ መሰቀልና የኢየሱስ አስቃቂ ሞት አስፈላጊ ከነበሩ ሁኔታችን ምን ያህል አደገኛ መሆን እንዳለበት በጥቂቱ ልናስብ እንችላለን። አረጋግጥልዎታለሁ፦ ይህን የሚረዱት አዳኙን ካወቁ በኋላ ብቻ ነው። በአስተማማኝ ወገን ላይ ሲሆኑ።

በረዶ በሸፈነው የቦደን ሐይቅ (Bodensee) ላይ ፈረሱን እየጋለበ ያለፈውን ሰው ታሪክ ምናልባት ያውቁ ይሆናል። ሳያውቅ።[146] በሐይቁ ማዶ ሲደርስ ከየት እንደ መጣ ነገሩት።


---

139. ሮሜ 8፥14፣ 19፣ 29፤ ገላትያ 4፥6
140. 2 ቆሮንቶስ 8፥9
141. ሮሜ 8፥32
142. ዕብራውያን 10፥19-22፤ 1 ጴጥሮስ 3፥18
143. ሉቃስ 15፥11-24፤ ኤፌሶን 2፥13፣ 18
144. 1 ዮሐንስ 1፥3-4፣ 7
145. ሮሜ 6፥23
146. በጉስታፍ ሽዋብ (Gustav Schwab) «Der Reiter und der Bodensee» በሚለው ግጥም መሠረት (1826)።

ደንግጦ ወደቀ። በቀዘቀዘው ሐይቅ ላይ የነበረውን የሞት አደጋ ተገነዘበ። ስማይ ለአንድ ሰው ሲከፈትና የእግዚአብሔር ጸጋ ወደ ልቡ ሲያበራ ሁኔታው ልክ ይህን ይመስላል። እነዚህን ቃላት ሲሰማ፦ በጸጋ ድናችኋል![147] ሰው ወደ ኋላ ይመለከትና ራሱን ይጠይቃል፦ የት ነበርሁ? በገደል ላይ! በሞት አደጋ ውስጥ። ላደርገው የምችለው ከሁሉ የከፋው ሞኝነት። ለጥፋት የተወሰንሁ ነበርሁ፤ አሁን ግን በሰላም ነኝ። እርሰዎም ይጠይቁ ይሆናል፦ በእርግጥ በእንደዚህ ያለ ታላቅ አደጋ ውስጥ እንኖራለን? አዎን፣ ለጥፋት ተወስነን በሞት ደጃፍ ላይ እንኖራለን።

መዳን አለ፦ ወደ አዳኛችን ይመልከቱ! በመስቀሉ ላይ! በኃጢአትዎ ተጭኖ። የጠፋውና የተበላሸው ሕይወታችን በክርስቶስ በመስቀል ላይ ተቸነከረ። እንድንገላገለው። ይህን ዜና ስሞቶ የማይናወጥ የእግዚአብሔርን ቃል ገና አልተረዳም። ኃጢአተኛ መሆኑን ሊረዳ የሚችለው የጠፋው ሳይሆን የዳነው ነው። የእግዚአብሔር ጸጋ ሳይጠበቅ ወደ ሰው ልብ ሲገባ ኃጢአተኛ መሆንን ማወቅ ወደ መዳን ደስታ ይለወጣል።

147. ኤፌሶን 2፥1-10



ስለ ራሳችን ያለው እውነትና የእግዚአብሔር ጸጋ ነጻ ያወጡናል![148] ምናልባት መዝሙሩን ያውቁት ይሆናል፤ ዜማውንም ይወዱት ይሆናል። ነገር ግን ርዕሳችንን በትክክል የሚገልጸውን ቃሉን በጥንቃቄ ያስተውሉ፦

Amazing Grace how sweet the sound! That saved a wretch like me! I once was lost, but now am found; Was blind but now I see.

አስደናቂ ጸጋ፣ ድምፁ እንዴት ጣፋጭ ነው፣ እንደ እኔ ያለ ጎስቋላ ያዳነ! እንድ ጊዜ ጠፍቼ ነበር፤ አሁን ግን ተገኘሁ፤ ዕውር ነበርሁ፤ አሁን ግን አያለሁ።

ይህ የመዝሙሩ የመጀመሪያው እንጓ ነው። መዝሙሩን የጻፈው ቀድሞ የባሪያ ነጋዴ የነበረ ሰው (ጆን ኒውተን (John Newton)፣ 1779) ሲሆን ክርስቶስን አዳኙ አድርጎ አግኝቶት ነበር። ወይም ይልቁንም በክርስቶስ ተገኝቶ ነበር።

148. ዮሐንስ 8፥32

ጸጋ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ

ኢየሱስ የጸጋ ቃላትን ተናገረ።[149] የሚኮንኑና የሚያጠፉ ቃላትን አይደለም። የሚያነሡትን፣ የሚያበረታቱትንና ይቅርታን የሚሰጡትን እንጂ። ሰለዚህ ወንጌል ከጸጋ የምሥራች በቀር ሌላ ሊሆን አይችልም።[150] ጸጋ ማለት እኛ ጀርባችንን ብንሰጠውም ዘላለማዊው አምላክ ወደ እኛ ሰዎች ዝቅ ማለቱና ፊቱን ወደ እኛ ማዞሩ ነው። በግድ ሊገኝ የማይችል፣ ነገር ግን በነጻና በፈቃደኝነት የሚሰጥ ጸጋ።

ጸጋ አዳነን። ለእግዚአብሔር ምንም ልናቀርብለት አልቻልንም። ምንም ካሳ መክፈል የማንችል ነንና። ልናደርግ የቻልነው ማንነታችንን ማሰተዋልና መቀበል ብቻ ነበር። እግዚአብሔርም ማን እንደ ሆነ። የእግዚአብሔርን ጽድቅ መቀበል እኛ ጻድቃን አለመሆናችንን መቀበል ማለት ነው።

እግዚአብሔር ጻድቅ ዳኛ ነው።[151] በዛሬው የሕግ ሥርዓታችን ዳኞች የሕግ መተላለፍን ይኮንናሉ፤ በሕግ መሠረትም ቅጣትንና ማዕቀብን ይወሰናሉ። ወንጀሎቹ ግን በቀጥታ በዳኛው ላይ የተፈጸሙ አይደሉም። በእግዚአብሔር ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም፦ በደለኞች የሆንነው በእርሱ ላይ ነው – ዳኛችንም በሆነው በፈጣሪያችን ላይ።[152] ምን ይጠብቀናል?[153]

ነገር ግን ኩነኔውን ለማሰቀረት ሁሉን ያደረገው ዳኛው ራሱ ነው።[154] በፍቅሩና በሚያድነው ጽድቁ በኢየሱስ አገኘን። በሕይወቱና በሞቱ። በመስቀል ላይ ያቀረበው መሥዋዕት፣ የኢየሱስ ደም፣ ኃጢአታችንን ለዘላለም ይሸፍናል።[155] ይህ ወንጌልን ለራሳቸው ለሚቀበሉና ለሚያምኑ[156] ሁሉ ነው – እግዚአብሔር ለእነርሱ ባደረገው ለሚያምኑ ሁሉ።[157]

የእግዚአብሔር ጸጋ ይህ ነው።[158] ትክክለኛ ኩነኔ ከእኛ ሲመለስ። ሌላው በእኛ ፋንታ ሰለ ቆመ። እርሱ ኃጢአታችንንና ኃጢአተኛ ማንነታችንን ወደ ሞቱ ውሰጥ ይሸከማል።[159]

---

149. ሉቃስ 4፥22
150. የሐዋርያት ሥራ 20፥24
151. የሐዋርያት ሥራ 10፥42፤ 17፥31፤ ሮሜ 2፥3፣ 16፤ 3፥6፤ 14፥10፤ 2 ጢሞቴዎስ 4፥1፤ ዕብራውያን 10፥30፤ 1 ጴጥሮስ 1፥17፤ 4፥5፤ ራእይ 11፥18፤ 20፥12
152. ሮሜ 3፥23
153. ሉቃስ 18፥13
154. ዮሐንስ 3፥17
155. 1 ዮሐንስ 1፥7፤ ራእይ 1፥5-6፤ 5፥9-10፤ ዕብራውያን 9፥12-15
156. ሮሜ 1፥16
157. ሮሜ 5፥8-10
158. ዮሐንስ 1፥14-17፤ ሮሜ 5፥9፣ 15፤ 2 ቆሮንቶስ 8፥9፤ ኤፌሶን 1፥7፤ 2፥5፣ 13፤ ቲቶ 2፥11
159. 1 ተሰሎንቄ 5፥10፤ ቲቶ 2፥14፤ 1 ዮሐንስ 2፥2፤ 3፥16፤ 4፥10፤ 1 ጴጥሮስ 2፥24፤ 3፥18

ጸጋ ደግሞ ያልተገባንን ነገር በሰጦታ መቀበል ነው። ያልተገባንን እጅግ እጅግ የሚበልጥ ነገር የሚሰጠን ጸጋ።[160] አምላክ እንዲህ ነው፤[161] በጸጋ ወንጌል የሚሰበከውም እርሱ ነው።[162]

የጸጋ ወንጌል ከሃይማኖቶች ሁሉ ይለያል። ከክርስቲያናዊ ሃይማኖትም። ጸጋ የሃይማኖት ሁሉ ፍጻሜ ነው። ሰው መልካም እንዲያደርግ የሚገደድበት ሃይማኖት። በመዳን ወይም በዘላለም ሕይወት ለመሸለም ሥራ ማቅረብ የሚገደድበት። በኢየሱስ ይህ ሥራ ሰለ እኛ ተፈጽሟል። በኢየሱስ ሁሉ በሰጦታ ተሰጥቶናል። እኛ ራሳችን ልንፈጽመው አንችልም። ጸጋ በነጻ ነው፤ ነጻ ሰጦታ ነው፤ በሥራ ለረኀ አይችልም። እንዳንዶችን ብዙ ጊዜ ሳያውቁት ያላቸው የራሳቸው ትዕቢት ያግዳቸዋል። ይህን ታላቅ የጸጋ ሰጦታ በእምነት መቀበል ይከብዳል። በሥራ መርሕ ተሞልተናል። ሰው ጸጋን ሲቀበልና ከእንግዲህ በራሱና በሥራው ሳይታመን ሲቀር ይህ እመርታ፣ ነጻ መውጣት ነው። በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት ባደረገው መልካም ሥራ ሳይመካ ሲቀር።

> ወንጌል ከማንም ጋር አይምታታም። አስናካይ ነው። ከሃይማኖቶችና ከመዳን አቅርቦቶች ሁሉ ተቃራኒ ነው። እንዲህ ያውጃል፦ ሁሉ ኃጢአተኞች ናቸው። እንድ የተሰቀለ መዳናችን ነው። ቤዛነት የሚገኘው ያልተገባ የጸጋ ሰጦታ ሆኖ ብቻ ነው። በነጻ። ይህ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው።

ሰው ጸጋን የሚቀበለው እግዚአብሔርን ለመጀመሪያ ጊዜ በለመነበት ቅጽበት ብቻ አይደለም። ከዚያ ጀምሮ ጸጋ በሕይወቱ በየሰዓቱ ይከተለዋል። ጸጋ የክርስትና መለያ ምልክት ነው። ያለ እርሱ ምንም አይሆንም። ጸጋ ኢየሱስን መከተልን ይሞላዋል፤ ከሁሉም ወገን ይከብበዋል። ጸጋ ይሸከመናል። የሕግ ወይም የባሪያ አስገዳጅ ጥያቄዎች አይደሉም። ጸጋ አይጠይቅም፤ ራሱን ይሰጣል። ኢየሱስን መከተል የሚሠራው ከጸጋ ነው። ሰጦታ እንደ ተቀበሉና ዘወትር እንደሚቀበሉ ሰዎች። ጸጋ የመከተልን ጅማሬና የመጨረሻውን ቀን ይከብባል። ያለ እርሱ ታማኝነትና መከተል ሊታሰቡ አይችሉም።

---

160. ሉቃስ 15፥22፤ ኤፌሶን 2፥7
161. 1 ጴጥሮስ 5፥10
162. ሚክያስ 7፥18



እግዚአብሔር ፍቅር ነው

መላ ማንነቱ ፍቅር ነው ተብሎ ስለ ማን ሊነገር ይችላል? ሥር ነቀል፣ ራሰ ወዳድነት የሌለበትና ራሱን መሥዋዕት የሚያደርግ ፍቅር። እንደዚህ ያለ ሰው አግኝተው ያውቃሉ? እኔ አላገኘሁም፤ ምንም እንኳ መልካምና ምሳሌ የሚሆኑ ሰዎችን ባውቅም።

ስለ እግዚአብሔር ይህ ይነገራል። ከዓለም በላይ የሆነ፣ ከፍጥረት የላቀና ዘላለማዊ የሆነ ይህ ፍቅር በእርግጥ እንዳለ በኢየሱስ ማሰረጃ አለን። በዓለማችንም እንደ ተገለጠ። እንደዚህ ያለውን አምላክ ማወቅ ይገባናል?

አሁን ስለ እግዚአብሔር ጸጋ ተነጋገርን። እርሱ ቸር ነው። መዳናችን የሆነ የእግዚአብሔር ባሕርይ! ነገር ግን ለምን ቸር ነው? ራሱ ፍቅር ስለ ሆነ።[163] የጸጋ ምንጭ እንደ ወንዝ ወደ እኛ የሚፈሰሰው ፍቅሩ ነው፤ እጅግ ዝቅተኛው ቦታ እስኪደርስ ድረስ አይቆምም።

እርሱ ሁልጊዜ ፍቅር ነበር። ፍቅር ለመውደድ የሚወደው ሌላ አካል ያስፈልገዋል። ጽንፈ ዓለም ከመኖሩ በፊት አብ ወልድን ወደደ።[164] አብ፣ ወልድና መንፈስ – በሦስት አካላት ያለ አንዱ አምላክ – እርስ በርስ በሚተያይ ዘላለማዊ ፍቅር ነበሩ። ያለ መጀመሪያ። ብቸኛ

163. 1 ዮሐንስ 4፥7-11
164. ዮሐንስ 17፥24

ወይም ለብቻው አልነበረም። ልናስበው ከምንችለው በላይ ነው፤ ይበልጥም ታላቅ ነው። ፍቅሩም እንዲሁ።

የሰው ፍቅር ጥልቀት ለሚወደው ምን ያህል መሥዋዕት ለማድረግ ዝግጁ እንደ ሆነ ሊለካ ይችላል ብለን ብንነሣ በወንጌል ታሪክ የሚገለጸው ፍቅር ተወዳዳሪ የለውም። ሊመረመር ከማይችል ፍቅር የተነሣ እስከ መጨረሻው ጥግ ለመሄድ ዝግጁ የነበረ የአምላክ ታሪክ ነው። ራሳቸውን የእግዚአብሔር ጠላቶች ያደረጉ ሰዎችን ለማዳንና ለማደስ።

ቅዱሱ አምላክ ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ እስከ መጨረሻው ጥግ ሄደ። ወልድ ኃጢአታችንን ተሸከመ።[165] በኃጢአት ውስጥ ያለውን በእግዚአብሔር መተው ቀመሰ። ስለዚህ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ጮኸ፦ አምላኬ፣ አምላኬ፣ ለምን ተውኸኝ?[166] እግዚአብሔር ከዚህ በላይ ሊሄድ አይችልም። በጎልጎታ ከሰጠው በላይ ሊሰጥ አይችልም። ስለዚህ መስቀሉ የእግዚአብሔር ታላቅ መገለጥ ነው። ከዚህ የሚበልጥ የሚወድ፣ አብልጦ የሚሰጥ ሰው የሚተርክ ታሪክ የለም። ይህንም ላልተገባቸው ሰዎች።[167]

ይህን ፍቅር እንዴት ልንረዳው ወይም ልናብራራው እንችላለን? ኅብረተሰባችን ይህን ቃል ብዙ ጊዜ ይጠቀማል። ከልክ በላይ። ነገር ግን በትክክል ምን ማለቱ ነው? እያንዳንዱን ሰው እንዳለ የሚቀበል ፍቅር። ያለ ቅድመ ሁኔታ። የማይፈርድና የማይኮንን ፍቅር። ሁሉን የሚታገሥ፣ ሰምምነትን የሚፈልግ። ምንም የማይጠብቅ። የፍቅር ስሜትና ልብ የሚነካ ስሜት ብቻ የሆነ።

ይህ መግለጫ ከመጽሐፍ ቅዱስ የፍቅር ትርጉም ጋር አንድ ነው?

እንዲህ ቢሆን ብለን እናስብ። እግዚአብሔር ሰዎች የሚያደርጉትን ሁሉ ቢታገሥ። ባይነቅፍና ባይፈርድ። ይህ የት ያበቃ ነበር? እንደዚህ ያለው ፍቅር በእውነት ምን ያህል ፍቅር ያለበት ነው?

ሰው የእግዚአብሔር ፍቅር እንዳለን ይቀበለናል ብሎ ካመነ ኃጢአተኞች መሆናችንን ይረሳል። ዛሬ እግዚአብሔር እንደሚፈልገውና ለእኛ እንደሚበጀው እንደማንኖር ይረሳል። ራሰዎን በወላጆች ቦታ ያስቀምጡ። ምናልባት እናት ወይም አባት ይሆኑ ይሆናል። ያደገ ልጅዎን ያስቡ። መልካም ያልሆኑ ነገሮችን ያደርጋል። ራሱንና ሌሎችን የሚጎዱ ነገሮችን። ከዚህም በላይ ከእርስዎ ጋር ያለውን ግንኙነት አቋርጧል። ይጠላዎታል፤ ያለ ምክንያትም ይወቅሰዎታል።

---

165. 2 ቆሮንቶስ 5፥21
166. ማርቆስ 15፥34
167. ሮሜ 5፥8

ልጅዎ ሆኖ ይቀራል። እርሱን መውደድዎን አያቆሙም። ነገር ግን በሕይወቱ ያለውን ክፉ ነገር አይቀበሉም። ነገሩ እንዲህ በመሆኑ ይቆጣሉ፤ ያዝናሉም። መጥፎውን ነገር ፈጽሞ አይፈቅዱም። በእኛ በሰዎች ተሞክሮ እንኳ ፍቅርና አለመቀበል በሆነ መንገድ አብረው የሚሄዱ ነገሮች ናቸው። ክፉውን የሚቃወመውና የሚኮንነው ፍቅር ነው።

እንዳለን እንድንቀር እግዚአብሔር እንዳለን ሊቀበለን ይገባል ማለት እንችላለን? ሌሎች ቢሠቃዩበት ወይም ቢጎዱበትም እግዚአብሔር በእርግጥ የአኗኗራችንን ዘይቤ ሊቀበል ይገባዋል?

ውስን የሆንን፣ በብዙ መንገድ ነጻ ያልሆንን ሰዎች እንደ መሆናችን ስላምና ፍትሕ የተለመዱ የሆኑባትን ዓለም እንናፍቃለን። ምድርንና ሰዎችን የፈጠረው እርሱ ይህን ምን ያህል የሚናፍቅ ይመስልዎታል? እግዚአብሔር በጥላቻ፣ በግፍ፣ በዓመፅና በእርሱ መልክ በተፈጠሩት ሰዎች ላይ ኃጢአት በሚያመጣው መከራ ባይቆጣ ኖሮ የሚወድ አምላክ ባልሆነ ነበር። ጉዳዩ የማይመለከተው ተመልካች ብቻ ይሆን ነበር። እግዚአብሔር ኃጢአትን፣ የሰዎችን ክፋት ባይኮንንና ባይፈርድበት ኖሮ ይቀበለው፣ ያመካኘውና ይፈቅደው ነበር። ለኃጢአት አጥፊ ኃይል የሚሰጠው ምላሽ ሁልጊዜ ቁጣና ፍርድ ይሆናል።

የእግዚአብሔር ፍቅር ቅዱስ ፍቅር ነው። ብዙ ጊዜ ከምንረዳው የተለየ ነው። መለኮታዊ፣ ወሰን የሌለው፣ ያለ ቅድመ ሁኔታ የሆነ ነው። ንጹሕ ነው። ሥራ ፈት፣ የፍቅር ስሜት ብቻ ወይም ልብ የሚነካ ስሜት ብቻ ሳይሆን ጠንካራ ፈቃድ ያለው የእዳኝ ፍቅር ነው።

የእግዚአብሔር ፍቅር ቁጣውንና ፍርዱን አያሰቀርም። እግዚአብሔር ይመሰገን። ደስተኛ ለመሆን ስለሚያስፈልገው እንዳለን የሚቀበለን ደግ አምላክ አይደለም የምናገኘው። የመጽሐፍ ቅዱስ አምላክ ሊለውጠን፣ በፍቅሩ ሊያወጣን፣ ወደ ራሱ ሊሰበን ይፈልጋል። ኃጢአተኛውን ከመለወጡ በፊት ይወደዋል። በኃጢአቱ መካከል ይወደዋል።[168] ነገር ግን ሊለውጠው፣ ሊቀድሰው፣ ኢየሱስን እንዲመስል ሊያደርገው ይፈልጋል።

168. ዮሐንስ 3፥16፤ ሮሜ 5፥8፤ 2 ቆሮንቶስ 5፥14፤ ኤፌሶን 2፥4-5፤ ቲቶ 3፥4-5፤ 1 ዮሐንስ 4፥7-10



የማይታየው ዓለም – የጨለማ ኃይላት

እንደገና ወደ ሰቅላቱ እንመለስ። በእርሱ ውስጥ የማይታዩ ክፉ ኃይላትም ዋና ተሳታፊዎች ነበሩ። ኢየሱስ በሕይወት ሳለ አግኝቷቸው ነበር። እንደ ብርቱ ነጻ አውጪ![169] አጋንንትን – ርኩሳን መናፍስትን – ያወጣና ያባርር ነበር። በዚህም ሥልጣናቸው ወደ ፍጻሜው እንደ ደረሰ አወጀ። ወንጌል ከእነዚህ ኃይላት ጋር በተጨባጭ የተያያዘ ነው። ብዙዎች ከሚያስቡት በላይ።

እነዚህ ኃይላት እነማን ናቸው? የኢየሱስንስ ሞት ለምን ፈለጉ? እግዚአብሔር ምድርንና ሰዎችን ከመፍጠሩ በፊት መላእክትን ፈጠረ።[170] አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ።[171] ይህ ሰማያዊ ቤተሰቡ ነው። ልዩ ልዩ መላእክት በልዩ ልዩ ተዋረድ፣ የተለያየ ሥራ ያላቸው። እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ጽንፈ ዓለምን እንዲገዛ ለራሱ ፈጠራቸው። አገልጋዮቹ ናቸው።[172]

እንደ እኛ እንደ ሰዎች እነርሱም ለፈጣሪያቸው ታማኝ የመሆን ነጻነት ነበራቸው። ከመላእክት አንድ ክፍል ሌላ መረጠ። ያለ እግዚአብሔር መኖርን።[173] መሪያቸው ዲያብሎስ – ሰይጣን – ነበር።[174] በማይታየው ዓለም ይህ ዐመፅ በተነሣ ጊዜ እግዚአብሔር አላጠፋቸውም። ከዚያ ወዲህ እነዚህ መላእክትና የእግዚአብሔር ልጆች

169. ማርቆስ 3፥27
170. ኢዮብ 38፥4-7፤ መዝሙር 148፥2፣ 5፤ ቆላስይስ 1፥16
171. ኢዮብ 1፥6፤ 38፥7፤ መዝሙር 82
172. መዝሙር 104፥4፤ ዳንኤል 6፥22፤ ማቴዎስ 1፥20፣ 24፤ 16፥27፤ ሉቃስ 2፥13፤ የሐዋርያት ሥራ 8፥26፤ 10፥7፤ 12፥8፤ ዕብራውያን 1፥7፤ 13፥2
173. 2 ጴጥሮስ 2፥4፤ ይሁዳ 1፥6
174. ማቴዎስ 25፥41፤ ኤፌሶን 2፥2፤ 1 ዮሐንስ 3፥8፤ ራእይ 12፥7-9

በሰይጣን መሪነት እግዚአብሔር በሚያደርገው ነገር ሁሉ ላይ ይሠራሉ።[175] ከእነርሱ በተቃራኒ ታማኝ ሆነው የቀሩት መላእክት ይቆማሉ።[176]

ኃይላቱና ሰዎች

ሰው ከተፈጠረ በኋላ ወዲያውኑ አሳሳቹና ነፍሰ ገዳዩ[177] ወደ መድረኩ ይመጣል።[178] ሰይጣን – የቀደመው እባብ –[179] የመጀመሪያዎቹን ሰዎች ከእንግዲህ በእግዚአብሔር እንዳይታመኑና በቸርነቱ እንዲጠራጠሩ ያሳስታቸዋል።

ሰይጣን በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠሩትን ሰዎች ቀና። ማጥፋት ብቻ ፈለገ። እግዚአብሔር በምድር ላይ የሰዎች ቤተሰብ እንዳይኖረው ለማገድ። ሰዎችን ለራሱ ፈለጋቸው። እንደ መልካም አባት ሳይሆን እንደ ባሪያ አሳዳሪና አምባገነን። ይህ ዝርፊያ ተሳካለት። በእትክልቱ ገነት ከሆነው ድርጊት ወዲህ ሰው ከእንግዲህ በእግዚአብሔር አጠገብ አይደለም።[180]

በሰው ልጅ ታሪክ እድገት ውስጥ የእነዚህ የማይታዩ ኃይላት ተጽእኖ ይታያል። በሕዝቦች ሁሉ መካከል በነበሩና በከፊል እስከ ዛሬ ባሉ ቁጥር ሰፍር የሌላቸው የጣዖት አምልኮዎች ውስጥ ይህ በግልጽ ይታያል።[181] አዲሰ ኪዳን ያለ እግዚአብሔርና ከእግዚአብሔር ተለይተው የሚኖሩ ሰዎች በዲያብሎስ መንፈሳዊ ምርኮና እስራት ውስጥ እንዳሉ ግልጽ ያደርጋል።[182] ይህ ከውጭ አይታይም። ሰዎች ራሳቸው አያስተውሉትም። ነጻ እንደ ሆኑ ይሰማቸዋል። የሚከብበንንና በመካከላችን ያለውን የማይታየውን ዓለም ለማየት ዕድል ቢያገኙ ኖሮ ዓይኖቻቸው በተከፈቱ ነበር። ሰለ እግዚአብሔር፣ ሰለ ራሳቸውና ሰለ ወንጌል ያላቸው አስተሳሰብ ጨልሟል።[183] ዓለም በእርግጥ ገና የሰይጣን መንግሥት ነው።[184] ኢየሱስ የዚህ ዓለም ገዢ ብሎ ይጠራዋል።[185] ጳውሎስ እንዲያውም የዚህ ዓለም አምላክ ብሎ ይጠራዋል።[186] በዓለም ሁኔታ ላይ ታላቅ ሥልጣንና አጥፊ ተጽእኖ አለው። ያለዚህ

175. ሮሜ 8፥38፤ 2 ቆሮንቶስ 11፥14፤ 12፥7፤ ኤፌሶን 6፥10-17፤ ራእይ 12፥13፤ ራእይ 13
176. 1 ጢሞቴዎስ 5፥21፤ ራእይ 5፥11፤ 7፥11፤ 12፥7
177. ዮሐንስ 8፥44፤ 1 ዮሐንስ 3፥8፣ 12
178. ዘፍጥረት 3፥1-7፤ 2 ቆሮንቶስ 11፥3-4
179. ራእይ 12፥9
180. ዘፍጥረት 3፥23-24
181. 1 ቆሮንቶስ 10፥20-22
182. የሐዋርያት ሥራ 26፥18፤ ኤፌሶን 2፥1-3፤ ቆላስይስ 1፥13
183. 2 ቆሮንቶስ 4፥3-5
184. ማቴዎስ 4፥8-10
185. ዮሐንስ 12፥31፤ 14፥30፤ 16፥11
186. 2 ቆሮንቶስ 4፥4

የዓለምን ሁኔታ ማብራራት አይቻልም ማለት ይቻላል። ሰው ራሱ ክፉ መሆኑ ሁኔታውን ይበልጥ የከፋና መውጫ የሌለው ያደርገዋል።[187]

የማይታየው ዓለም ይህን ያህል እውነተኛ እንደ ሆነ አስበው ነበር? ከእኛም ጋር ይህን ያህል ግንኙነት እንዳለው?

ወንጌልና ኃይላቱ

ኢየሱስ በመጣ ጊዜ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ዓለም፣ ወደ ክፉ ኃይላት ግዛት ሰብሮ ገባ። ይህ የዲያብሎስና የመላእክቱ ፍጻሜ ጅማሬ ነበር። የእግዚአብሔር ዋና ዕቅድ ሥራ ላይ ዋለ። ኢየሱስ በገሊላ ሲዘዋወር አጋንንት ከማን ጋር እንደሚገጥሙ ያውቁ ነበር።[188] እንደ ሰዎቹ አልነበሩም። ከማይታየው ዓለም ያውቁት ነበር። ፈጣሪያቸው ነበር።

ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ሰይጣን ሊፈትነው በምድረ በዳ ገጠመው። ቢሰግድለት የዓለምን መንግሥታት ሊሰጠው አቀረበለት። ሰይጣን ክብሩን፣ ስግደትን ይፈልጋል። ባሕርዩ ይህ ነው።[189] ኢየሱስ ግን ተቃወመው። በዔደን እንደ ነበረው እንደ አዳም አልሆነም።[190]

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱንም በአጋንንት ላይ ሥልጣን እንዲኖራቸውና እንዲያወጧቸው ሥልጣን ሰጣቸው።[191]

አይደለም፣ እነዚህ የሚያስፈሩ ተረቶች አይደሉም፤ የአእምሮ ክሰተቶች ብቻም አይደሉም፤ የዕለት ተዕለት ሕይወት እውነታ ናቸው። እንደዚህ ያሉ ኃይላት በዚያ ይገለጣሉ። በተለይ ደግሞ ሰዎች ራሳቸውን ለእነርሱ በንቃት በሚከፍቱበትና አሳልፈው በሚሰጡበት ቦታ።

ኃይላቱና የእግዚአብሔር የመዳን ዕቅድ

የእግዚአብሔር የመዳን ዕቅድ ለዲያብሎስም ለሰዎችም የማይታወቅ ነበር። ብዙ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ቢኖሩም ለመገንዘብ አስቸጋሪ ነበር።[192] ደቀ መዛሙርቱም አልተረዱትም። የእግዚአብሔር ልጅ ያለ ሥልጣንና ያለ ዙፋን ሰው ሆኖ መገለጡ ኃይላቱን ግራ አጋባቸው።

187. ማርቆስ 7፥20-23
188. ማርቆስ 1፥23-24፤ 3፥11፤ 5፥7
189. ማቴዎስ 4፥1-11፤ ሉቃስ 4፥1-13
190. ሮሜ 5፥12-21
191. ማርቆስ 6፥7
192. 1 ቆሮንቶስ 2፥6-9

በዚህ ሁኔታ ያላቸው ብቸኛ አማራጭ ሰዎች ኢየሱስን እንዲገድሉት ማነሣሣት ነበር።[193] ሰው እንደ መሆኑ ሊቆሰልና ሊሞት ይችል ነበርና። ሰለዚህ አንድ ግብ ብቻ ነበራቸው፦ ሞቱን። አገኙትም! ነገር ግን ተሳሳቱ። ሞቱ ድሉ ነበርና።[194] ሞቱ ለእኛ ለሰዎች የጽንፈ ዓለም የሥልጣን ለውጥ ነበር።

ሞቱ ሰዎችን ከጨለማ ሥልጣን ነጻ ለማውጣት የተከፈለ ቤዛ ነው። ሞቱ ለሰዎች ጸጋንና ይቅርታን አመጣ። ነጻነትን። የዚያን ዘመን የባሪያ ገበያ ለዚህ ምሳሌ ነው። ቤዛነት ማለት ከባርነት ተገዝቶ ወደ ነጻነት መለቀቅ ማለት ነበር። ከሙታን መነሣቱና በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ከፍ መደረጉ ከኃጢአት፣ ከሞትና ከዲያብሎስ ባርነት ወደ ነጻነት የሚያስገቡ በሮች ናቸው።

የኃጢአታችን ይቅርታና ከኃጢአት ሥልጣን ነጻ መውጣት ያስፈልገን ነበር። ሁለቱም በመስቀሉ በኩል ተሰጥተውናል።

ዲያብሎስ ጸጋን አያውቅም። እርሱ ራሱ የእግዚአብሔርን ጸጋ አይቀበልም፤[195] ለሰዎችም ምሕረት የለውም። ጸጋ ለባሕርዩ እንግዳ ነው። በእግዚአብሔር ላይ ያነሣው ዐመፅ ፈጽሞ መራራ አድርጎታል።

አሁን አንድ ሰው በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ተቀምጧል። ሰለ እኛ ሰለ ሰዎች። እኛም ከእርሱ ጋር አንድ ሆነናል።[196] በክርስቶስ ነን![197] ኃይላቱ ተሸንፈዋል። ጊዜያቸው አልቋል። ቀኖቻቸው ተቆጥረዋል። ነገር ግን ወንጌልን ለማሰቆም ገና ይቃወማሉ፤ የተሸነፈ ውጊያም ይዋጋሉ። እነዚህ ኃይላት ሰዎች ነጻ ሲወጡ በየዕለቱ ያያሉ። በወንጌል የሚያምን እያንዳንዱ ሰው የእግዚአብሔር የመዳን ዕቅድ ግቡን እንደሚመታ ያስታውሳቸዋል። እግዚአብሔር ከምድር ሕዝቦች ሁሉ ቤተሰቡን ያገኛል። በሞቱ ዋና ተሳታፊዎች በነበሩበት በኢየሱስ በኩል። ኢየሱስ በሞተበት በጎልጎታ ሳያውቁ የራሳቸውን መቃብር ቆፍረዋል ማለት ይቻላል።

እግዚአብሔርንና ሰዎችን የሚጠሉ ኃይላት የሚመኩበት የዕዳ ጽሕፈት፣ የክሱ ደብዳቤ፣ በመስቀል ላይ ተቸንክሮ ተደምስሷል።[198] በመስቀሉ በኩል ኃይላቱን ትጥቅ አስፈታ፤ በዚያም በአደባባይ አጋለጣቸው። ከሙታን የተነሣው ክርስቶስ አሁን የጽንፈ ዓለም ጌታ

193. ሉቃስ 22፥53
194. ዕብራውያን 2፥14
195. ዕብራውያን 2፥16
196. ኤፌሶን 2፥6
197. ሮሜ 8፥1፤ 1 ቆሮንቶስ 1፥30
198. ቆላስይስ 2፥14-15

ነው።[199]የምሥራቹ ይህ ነው፦ በሁሉም ስውና በሁሉም ነገር ላይ ጌታ ነው። በክርስቶስ የሚያምን ነጻ ወጥቷል።[200]ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ወደ ቤቱ ይመለሳል።

ወንጌል እግዚአብሔር ሰዎቹን መልሶ እንደሚያመጣና ቤተሰቡን ሊያገኝ እንደሚፈልግ የሚገልጽ የእግዚአብሔር የምሥራች ነው። ከሞትና ከክፉ ኃይላት ነጻ የወጡ። ኢየሱስ ይህን ሁሉ በመስቀል ሞቱ እንደ አሰቻለ የሚናገር የምሥራች ነው። ኢየሱስ የዲያብሎስን ሥራ ሊያፈርስ መጣ።[201] ከእርሱ ጋር የእግዚአብሔር የፍቅር አገዛዝ መጣ። ድነን ወደ ፍቅር መንግሥቱ እንሻገራለን።[202]

የመስቀሉ ድል

የሮም የጦር አዛዦች በክብር የድል ሰልፍ ወደ ሮም ይገቡ ነበር። የተሸነፉት መሪዎች በሰንሰለት ታሰረው አብረው ይወሰዱ ነበር። ከመገደላቸው በፊት በሕዝብ ፊት ለትዕይንት ይቀርቡ ነበር። ጳውሎስ የመስቀሉን ኃይል – የዚህ ዓለም ገዢ ግዛት በሆኑት አለቆችና ሥልጣናት ላይ ያለውን የማይቋቋሙትን ኃይል – የሚገልጸው እንዲህ ነው።[203] ትጥቅ ተፈትተውና ተጋልጠው። የሥራ ኃይላቸው ጠፍቷል።

የተሰቀለው በማይታየው መካከለኛ ዓለም ካሉ የአሰማት ኃይላት ነጻ ያወጣል። ሰይጣን ተፈርዶበታል። ሥልጣኑ ተሰብሯል። በኢየሱስ ሰዎች ላይ ከእንግዲህ ሥልጣን የለውም።

የእግዚአብሔር የመዳን ዕቅድ ለረጅም ጊዜ እንደሚቆይ የቼዝ ጨዋታ ነው። ከተጫዋቾቹ አንዱ ጨዋታውን የሚያውቅ ሰው ጨዋታው አሁን እንደ ተወሰነ የሚያውቅበትን እንቅስቃሴ እሰኪያደርግ ድረሰ ውጤቱ የማይታወቅ ነው። ጨዋታው ገና ቢቀጥልም እንኳ። በብርሃንና በጨለማ መካከል ያለው ውጊያ እንዲህ ነው። ወሳኙ እንቅስቃሴ በንጉሡ ተደርጓል። በጎልጎታ መሰቀል ላይ የእሾህ አክሊል በደፋው ንጉሥ። ድሉ ተፈጽሟል።

የተቃዋሚው እንቅስቃሴዎች ከእንግዲህ የማፈግፈግ ውጊያ ብቻ ናቸው። የቀረው ጊዜ ጥቂት ነው። ፍጻሜው ተወሰኗል።

የመስቀሉ መከራ የመስቀሉ ድል ይሆናል!

---

199. ማቴዎስ 28፥18
200. ዮሐንስ 8፥33-36፤ ሮሜ 6፥7፣ 18፣ 22
201. 1 ዮሐንስ 3፥8
202. ቆላስይስ 1፥13-14
203. ቆላስይስ 2፥15

ነጻነት ይቻላል

ስለዚህ እርግጠኛ ይሁኑ፦ የኢየሱስ ከሆኑ እጋንንት መሸሽ አለባቸው! በጥንቆላና በመናፍስት ሥራ፣ በመናፍስትና በመላእክት ነገር ውስጥ ገብተው ከሆነ ነጻነት አለ። ይቅርታም።

እነዚህ ኃይላት ሊለቁዎ አይፈልጉም፤ ነጻ ለመውጣት የሚያደርጉትንም ሙከራ ሁሉ ገና ሲጀመር ሊያፍኑት ይፈልጋሉ። ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ይጸልዩ – ስሙን ይጥሩ! ስለ እርስዎ የሚጸልዩና የሚረዱዎትን ክርስቲያኖች ይፈልጉ።

ከዚህ የመናፍስት ዓለም ጋር የሚያገናኟዎትን ነገር ሁሉ ድምፅዎን አስምተው ይካዱ።

ከእነዚህ የአስማትና የመናፍስት ነገሮች ጋር የሚያገናኟዎትን ነገር ሁሉ ያስወግዱ። ወደ እነደዚህ ያሉ ልማዶችና ግንኙነቶች ካሰገቡዎት ሰዎች ጋር ያለዎትን ግንኙነት ሁሉ ያቋርጡ።

የማይታየው ዓለም ሊናቅ የማይገባው ብርቱ እውነታ ነው። ነገር ግን ኢየሱስ ይበረታል።

የሰላም ወንጌል

ጴጥሮስ መምህሩ ስለምን እንዴት እንደ ሰበከ አይቶ ነበር።[204] ኢየሱስ ለአይሁድና ለአሕዛብ – አይሁድ ላልሆኑት – ስለምን አመጣ። በእነዚህ በሁለቱ መካከልም። ስለም የወንጌል ማዕከላዊና ዋና ገጽታ ነው።[205] ይህ የእግዚአብሔር ሻሎም ነው። በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉ እንዲህ ይባላል። የእግዚአብሔር ልብ ታላቅና ሰፊ ነው። ስለም የሚመጣው ከዚህ ልብ ነው። ትርጉሙ ሙሉ መሆን፣ ጤናማ መሆን፣ ደኅና መሆን፣ መዳን ነው። ወንጌል ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ሰላም ያመጣቸዋል።[206] ይህ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅና የጠላትነት ሁሉ ፍጻሜ ማለት ነው።[207]

ወንጌል እግዚአብሔር ልጁ አድርጎ እንደ ተቀበለን ወደ ማረጋገጫ ያመጣናል። ይህ ማረጋገጫ በእግዚአብሔር ላይ ጸንቷል። እርሱ ባለውና ባደረገው ላይ። በዚህ መሠረት ላይ እውነተኛና ጸንቶ የሚኖር ሰላም በልብ ውስጥ ይሰፋፋል። በዕረፍት ማጣት ፋንታ ዕረፍት። በስላም ማጣትና በፍርሃት ፋንታ ሰላም።

በትልቁም በትንሹም በጦርነትና በጠብ የተሞላች ዓለማችን ሰላም ያስፈልጋታል።[208] የጦርነት አለመኖር ብቻ ሳይሆን፣ የተኩስ አቁም ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎችን የሚያገናኙና አንድ

204. የሐዋርያት ሥራ 10፥36
205. ቆላስይስ 1፥20፤ ኤፌሶን 2፥17፤ 6፥15
206. ሮሜ 5፥1
207. ሮሜ 5፥10፤ 2 ቆሮንቶስ 5፥18
208. ቲቶ 3፥3

የሚያደርግ ሰላም።[209] ወንጌል በሰዎች መካከል ሰላምን ይፈጥራል። ሰላም የሚገዛበትን አዲስ የሰዎች ኅብረት ይፈጥራል።[210] እግዚአብሔር የሰውን ዓመፅ አንድ ጊዜ ለሁልጊዜ የዋጠበት የመስቀሉ ሰብከት የዓለም ሰላም ቁልፍ ሊሆን ይችላል? በመጀመሪያም በራሷ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ?

ሰዎች ሰላም ምን እንደ ሆነ ማወቅ ከፈለጉ በወንጌል በኩል የእግዚአብሔርን ሰላም ከተቀበሉት ዘንድ ሊያውቁት ይገባል። ሰላሙንም ከሚያንጸባርቁት። ለሌሎች ከሚያስተላልፉት። ሰላምን ከሚያደርጉት። በተቻላቸው መጠን[211] ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ይኖራሉ።

በኢየሱስ በኩል ሁሉ ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ታረቀ፤ ከእርሱም ጋር እንደገና ወደ ትክክለኛው ግንኙነት ተመለሰ። በደሙ ዋጋ። በጎልጎታ በሞቱ። ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ሰላምና የእግዚአብሔር ሰላም እውን እንዲሆኑ መስቀሉ አስፈላጊ ነበር።[212]

ይህን ሰላም እንዴት አጣጣሙት? በእርስዎ ውስጥ፣ በግንኙነቶችዎ ውስጥ ምን ለወጠ?

ወንጌል – የተፈጸመ የተስፋ ቃል

ወንጌል መንገዱን በሳተ የሰው ልጅ ታሪክ ላይ እግዚአብሔር በድንጋጤ ወይም በተሰፋ መቁረጥ የሰጠው ምላሽ አይደለም። ከእግዚአብሔር ልብ የሚመጣ ሲሆን ከዘላለም ዘመናት በፊት ተሰፋ የተሰጠበት ነው።[213] ስለዚህ በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ – ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ክፍል በብሉይ ኪዳን – ውስጥ በጥልቅ ሥር መሰደዱ አያስደንቅም። በዚያ ተሰፋ ተስጥቶበታል።[214] የእግዚአብሔር የመዳን ታሪክ የዘመን ፍጻሜ ብሎ ወደሚጠራው ነጥብ እንዴት እንደሚጓዝ ተገልጿል። እግዚአብሔር ልጁን የላከበት ጊዜ።[215] በእስራኤል የነበሩት አብዛኞቹ የዘመኑ ሰዎች ኢየሱስን የተሰፋው ቃል ፍጻሜ አድርገው አላወቁትም።[216] ነገር ግን አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት – ሐዋርያት – ብዙም ሳይቆዩ ይህን ተገነዘቡ። ይሁን እንጂ ከኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ በኋላ ብቻ።

209. ማቴዎስ 5፥44፤ 1 ዮሐንስ 4፥19
210. ኤፌሶን 2፥14-22
211. ሮሜ 12፥18
212. ቆላስይስ 1፥20
213. ሮሜ 16፥25-27፤ 2 ጢሞቴዎስ 1፥9፤ ቲቶ 1፥2
214. ሮሜ 1፥1-3፤ ገላትያ 3፥14-16
215. ገላትያ 4፥4
216. የሐዋርያት ሥራ 13፥27፣ 32

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍና በመልእክቶቻቸው ያለው የወንጌል ሰብከታቸው ከብሉይ ኪዳን በተወሰዱ ጥቅሶች የተሞላ ነው።[217] ብዙ ምሳሌዎች አሉ። ኢየሱስ ራሱ መጻሕፍት – ብሉይ ኪዳን – ስለ እርሱ እንደሚናገሩ ተናግሯል።[218] እዚህ ላይ ከብሉይ ኪዳን ሦስት አጫጭር ምሳሌዎችና ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች።[219]

ስዎች የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከተላለፉ በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ገጾች ላይ እነኳ የመጀመሪያው ወንጌል የሚባል የተሰፋ ቃል አለ፦ በእንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘርህና በዘሯ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ተረከዙን ትነድፋለህ።[220] ያን ጊዜ ለማስተዋል አስቸጋሪ የነበረው ነገር በኢየሱስ፣ በሕይወቱና በሞቱ ብርሃን ግልጽ ይሆናል። ኢየሱስ በመሞቱ ዲያብሎስን አሸነፈ![221]

በሰው ልጅ ታሪክ የጊዜ መሥመር ላይ ከብዙ ዓመታት በኋላ አብርሃም ከሚሰቱ ከሣራ ጋር ይገለጣል። ይህ ያረጀና ልጅ የሌለው ባልና ሚስት የወንድ ልጅ ተስፋ ቃል ይቀበላሉ። ሁለቱ ደስተኞች እንዲሆኑ ብቻ አይደለም። አይደለም፤ በዚህ ልጅ፣ በይስሐቅ፣ የምድር ሕዝቦች ሁሉ ይባረካሉ።[222] ይህ በኢየሱስ የሚፈጸም የተሰፋ ቃል ነው![223]

ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ ዳዊት የእስራኤል ንጉሥ ይሆናል። እንደ እግዚአብሔር ልብ ያለ ሰው። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ቢተላለፍም ለእግዚአብሔር ሁልጊዜ ታማኝ ሆኖ ኖረ፤ ጣዖትንም ፈጽሞ አላመለከም። እግዚአብሔር የዘላለም ዙፋን የሚኖረው ልጅ እንደሚሰጠው ቃል ገባለት።[224] ይህ ሰሎሞን ብቻ አልነበረም። ሙሉ በሙሉ የተፈጸመው በዳዊት ልጅ በኢየሱስ ነው። በእርሱ የብዙ መቶ ዓመታት ትንቢት ይፈጸማል። ንጉሥ፣ ከዳዊት የንግሥና ዘር በቀጥታ የመጣ ዘር፣ የእስራኤል መሲሕ ንጉሥ ይሆናል። ለዘላለም። እንዲህም ሆነ።[225] አሁን በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ነው፤ በቅርቡም ሁሉ እያዩት ዓለምን ይገዛል።

---

217. የሐዋርያት ሥራ 2፥25-31፤ ሮሜ 1፥17፤ 3፥21-26፤ 4፥17፤ 10፥8-13፤ 15፥9-13፤ 1 ቆሮንቶስ 2፥9፤ 2 ቆሮንቶስ 6፥2፤ ገላትያ 3፥16፤ 1 ጴጥሮስ 1፥19፤ 2፥6-9
218. ዮሐንስ 5፥39፤ 7፥42
219. መዝሙር 16፥8-10፤ 22፤ 31፥13፤ 35፥11፤ 69፥4፤ ኢሳይያስ 9፥2-7፤ 11፥1፤ 35፥4-6፤ 50፥6፤ 53፤ ሚክያስ 5፥2፤ ዘካርያስ 11፥12፤ ዳንኤል 9፥25-26
220. ዘፍጥረት 3፥15
221. ዕብራውያን 2፥14፤ ሮሜ 16፥20፤ ራእይ 12፥9-11፤ 20፥10
222. ዘፍጥረት 12፥3፤ 22፥18፤ 28፥14
223. ገላትያ 3፥16
224. 2 ሳሙኤል 7፥12-16
225. ሉቃስ 3፥23-31፤ ዘፍጥረት 49፥10፤ ኤርምያስ 23፥5-6፤ መዝሙር 132፥11፤ ሮሜ 1፥3፤ 2 ጢሞቴዎስ 2፥8፤ ራእይ 5፥5

ስለ እርሱ ይህን ያህል ብዙ ትንቢት ተነግሯል ብሎ ስለ ራሱ ሊናገር የሚችል ማንም የለም። ብዙ ትንቢቶች አሉ። ብዙዎቹም አስቀድመው በትክክል ተፈጽመዋል። መላው ብሉይ ኪዳን ወደ ኢየሱስ ያመለክታል። ብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር ልጅ ወንጌል ዋናው ምስክር ነው።



የወንጌል ተስፋ

የተስቀለ ሰው ከሙታን ሊነሣ ከቻለ ሁላችንም ተስፋ አለን! እርግጠኛ ተስፋ ነው፤ አንድ የተስቀለ ሰለ እኛ ከሙታን ተነሥቷልና፦ የእግዚአብሔር ልጅ። ተስፋን መልሶ ሰጥቶናል!

ሁላችንም ተስፋዎችና ሕልሞች አሉን። ለአንድ አፍታ ጊዜ ይውሰዱ። የሚመኙት የወደፊት ሕይወት፣ አሁን ከሚያጋጥምዎት የሚሻል ነገር ራእይ አለዎት? አንድ ቀን እውን እንዲሆን የሚመኙት ተስፋ?

ወንጌል አዲስ አድማስ ይከፍታል። በሕይወት እንኖራለን! ለዘላለም። የመጨረሻውን ቃል የሚናገረው ሞት አይደለም። ወንጌል ተስፋን ያሰራጫል።[226] ስለዚህ የአዲሱ ፍጥረት ወንጌል ብዬ መጥራት እወዳለሁ። ነገሮች እንዳሉ እንደማይቀሩ ቃል ይገባል።[227]

226. 1 ጴጥሮስ 1፥3-4
227. ሮሜ 8፥18-24

እግዚአብሔር ስለ መላው ፍጥረት ከልቡ ነው።[228] ጉዳዩ ሰዎች ብቻ አይደሉም፤ መላዋ ፕላኔት እንጂ። የእግዚአብሔር መንግሥት በአንድ በኩል ንጉሡን የሚያገለግሉ ሰዎችን ይይዛል። ነገር ግን ይህ መንግሥት የሚገኝበት ሰፍራም አለ። ይህ ሰፍራ ምድራችን ነው።[229] በጽንፈ ዓለም ውስጥ ትንሽ የአቧራ ቅንጣት ወደ ሆነችው ወደዚህች ምድር እግዚአብሔር በኢየሱስ መጣ።

እግዚአብሔር ፈጥሯት ነበር። የልቡ ሥራ ናት፦ ሁሉ እጅግ መልካም ነበር።[230] ስለዚህ እግዚአብሔር ለወደፊቱ ፍጹም የተለየ ወይም አዲስ ነገር አያስብም። አይደለም፤ ምድርን መሆን እንዳለባት አድርጎ ያድሳታል። በሌላ አነጋገር፦ አዲስ ያደርጋታል።[231] አንድ ቀን በእርሷ ላይ ሞት፣ በሽታና ረሃብ ከእንግዲህ አይኖሩም።[232] ሰው የሚያጠፋው ሁሉ፣ ሰውን የሚጎዳ ከቁጥጥር የወጣ ተፈጥሮም፣ ከእንግዲህ አይኖርም።[233]

ተስፋ በሌላት በተሰበረች ዓለም፣[234] የተስፋ ወንጌል ነው –[235] ዘላለማዊና የማይናወጥ መንግሥትን[236] ቃል የሚገባው። አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አዲሱ ቤታችን ይሆናሉ።

ተስፋው ከሙታን በተነሣው ላይ ጸንቶ ተመሥርቷል። ሞቶ በነበረውና ለዘላለም ሕያው በሆነው ላይ።[237] የሞትን ኃይል ሰብሯል።[238] በእርሱ በኩል እውነተኛ ሕይወትና አለመጥፋት ወደ ብርሃን መጥተዋል።[239] በክርስቶስ ከእንግዲህ የማይሞተውን የትንሣኤ ሕይወቱን እንደ ሕይወታችን ተቀብለናል። ከእንግዲህ ከኃጢአት ጋር ምንም ግንኙነት የሌለውን።[240] ይህ እውነተኛ ሕይወትና የአዲሱ ፍጥረት የማያልቅ ኃይል ነው። ይህ በኢየሱስ ተከታዮች ሕይወት ውስጥ አስቀድሞ ጀምሯል።[241] ለአዲስ ሕይወትና ለሕያው ተስፋ ዳግመኛ ተወልደዋል።[242] በክርስቶስ አሁንም አዲስ ፍጥረት ናቸው። አንድ ቀን በአዲሱ ፍጥረት ውስጥ ይኖራሉ።[243] የተለወጠ፣ የማይሞትና የከበረ አካል

228. ዮሐንስ 3፥16
229. ራእይ 5፥9-10
230. ዘፍጥረት 1፥31
231. ኢሳይያስ 65፥17-19፤ 66፥22
232. ራእይ 7፥9-17፤ 21፥1፣ 4-5
233. ራእይ 7፥16፤ 22፥3
234. ኤፌሶን 2፥12፤ 1 ተሰሎንቄ 4፥13
235. ኤፌሶን 1፥18፤ ቆላስይስ 1፥5፣ 23
236. 2 ጴጥሮስ 1፥11፤ ዕብራውያን 12፥27-28፤ ዳንኤል 2፥44፤ 7፥14፣ 27
237. ራእይ 1፥17-18፤ ዮሐንስ 14፥19
238. ዕብራውያን 2፥14-15
239. 2 ጢሞቴዎስ 1፥10
240. ሮሜ 6፥9-10
241. 2 ቆሮንቶስ 5፥17
242. 1 ጴጥሮስ 1፥3
243. 2 ጴጥሮስ 3፥13

ይኖራቸዋል።[244] ነገር ግን በሟች ሕይወታቸው የነበሩት፣ ከማንም ጋር የማይምታታውና እግዚአብሔር የፈቀደው ማንነት ሆነው ይቀራሉ።

ወንጌል እግዚአብሔር ስለ ወሰነው ጊዜ ይናገራል።[245] ያን ጊዜ ኢየሱስ ዳግመኛ ይመጣል፤ ሰዎች ሁሉ ያዩታል።[246] በታላቅ ክብርና ኃይል።[247] ይህ ለሚጠብቁት ሁሉ የደስታ ቀን ይሆናል። ያን ጊዜ ዘላለማዊው የእግዚአብሔር አገዛዝ ይጀምራልና። ያን ጊዜ ፈጽሞ የማያበቃው ዘመን ይጀምራል። እግዚአብሔር ራሱ ከሰዎች ጋር ሲኖር።[248] ሰዎቹ እግዚአብሔርን ያዩታል። ሊታሰብ የማይችል ደስታም ያገኛሉ።[249] ዘላለማዊው የፍቅር አምላክ፣ በሦስት አካላት ያለው አንዱ አምላክ ሁልጊዜ የፈለገው ይኸው ነው። ያን ጊዜ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ የተሻለ ይሆናል። ሰማይ – እግዚአብሔር ራሱ – ከሰዎቹ ጋር፣ ከቤተሰቡ ጋር በሚታይ ሁኔታ ለመኖር ወደ ምድር ይመጣል። ለዘላለም። ኢየሱስን በመምሰል የእግዚአብሔር መልክ እንሆናለን![250]

ያን ጊዜ ምድር አንድ ታላቅ፣ እንዲያውም ዓለም አቀፍ ገነት ትሆናለች። አዲስና የተሻለች ዔደን።[251] ፈታኙ ወደዚያ ከእንግዲህ ፈጽሞ አይመጣም። ወደ ኃጢአት የሚያደርስ ፈተና ከእንግዲህ አይኖርም።

አስልቺም አይሆንም፤ ይልቁንም የሚያጓጓ ይሆናል። ሁልጊዜ መሆን የነበረብን ሰዎች ስለምንሆንና መሆን ስለምንችል ታላቅ ጀብዱ ይጠብቀናል።

የእግዚአብሔር አዲስ ዓለም ሕልም

ስለዚህ የእግዚአብሔር አዲስ ዓለም ለጥቂት ጊዜ እናልም። ስለ እርሱ ብዙ ባናውቅም መጥፎው፣ አሉታዊውና አጥፊው ነገር ሁሉ ከእንግዲህ አይኖርም። በዚያው ጊዜ እግዚአብሔር እንደ ፈጠራት በአሁኗ ምድር ላይ የምናውቃቸው ብዙ ነገሮች ይኖራሉ።

ድህነት፣ ረሃብ፣ የሕልውና ትግል፣ የወደፊቱ ፍርሃት ከእንግዲህ የሌሉባት ዓለም።

ባርነት የለም፣ ጭቆና የለም፣ ዓመፅ የለም፣ ማታለል የለም፣ አድልዎ የለም፣ ውርደት የለም፣ ወንጀል የለም፣ ጦርነት የለም።

---

244. 1 ቆሮንቶስ 15፥35-58፤ ፊልጵስዩስ 3፥20-21
245. የሐዋርያት ሥራ 17፥30-31
246. ራእይ 1፥7
247. ማርቆስ 8፥38፤ 13፥26
248. ራእይ 21፥3
249. ራእይ 22፥4
250. 1 ቆሮንቶስ 15፥49-50፤ ፊልጵስዩስ 3፥20-21፤ 1 ዮሐንስ 3፥2
251. ራእይ 2፥7፤ 22፥1-5

በሽታ የለም፣ ሞት የለም፤ ስለዚህም ኀዘንም እንባም የለም – እንባ ካለ የደስታ እንባ ብቻ።

የአካባቢ ብክለት የለም፣ አደጋ የለም። ፖሊስ የለም፣ ጠበቆችና ፍርድ ቤቶች የሉም፣ ሆስፒታሎች የሉም፣ የአእምሮ ሐኪሞችና የሥነ ልቦና ባለሙያዎች የሉም።

መሰላቸት የለም፣ ከንቱ የትርጉም ፍለጋ የለም፣ የበታችነት ስሜት የለም፣ ኀፍረት የለም፣ ባዶነት የለም፣ አጥፊ ጥገኝነትና ሱስ የለም፣ ተስፋ መቁረጥ የለም!

በዚህ ፋንታ ይህ ይኖራል፦ ሰላም፣ በሰዎች መካከል ራስ ወዳድነት የሌለበት ፍቅር፣ ፍጹም ፍትሕ፣ ሙሉ በሙሉ እርስ በርስ መቀባበል፣ መከባበርና ትኩረት መሰጠት።

ሁሉ ነገር መሆን እንዳለበት የሆነበት ሰፍራ። የሚፈልቅ ሕይወት፣ የብዝኃነት፣ የእድገት፣ የነጻነት፣ የጀብዱ፣ የፈጠራ ችሎታ፣ ዘወትር አዲስ ነገር የማግኘት ሰፍራ፤ ሁሉ ነገር ሁልጊዜ አዲስና ትኩስ የሆነበት ሰፍራ።

በድካም፣ በፍላጎት ማጣትና በመዛል ፋንታ ብርታት፣ ሕያውነትና ተነሣሽነት ለዘላለም ይኖራሉ።

ሰው የሚያስሰውና የሚመረምረው ሊታሰብ የማይችልና ልዩ ልዩ ውበት ያለበት ሰፍራ። ሰው አዳዲስ ሰዎችን የሚያውቅበትና ከእነርሱ ጋር የሚያከብርበት ሰፍራ።

ጊዜ የሚቆምበት ወይም ፈጽሞ የማያልፍበት ሰፍራ! ውብ የሆነው ነገር ያለፈ ታሪክ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ አሁን የሚሆንበት ሰፍራ! ምንም የማያመልጠን ሰፍራ።

መኖር አለበት ብለን ያሰብነው ሰፍራ፣ ልባችን ሁልጊዜ የናፈቀው ሰፍራ።

የተትረፈረፈ በረከት፣ የምርጥ ምግብ፣ የውብ ጥበብና ሙዚቃ፣ የምርጥ ቴክኖሎጂ ሰፍራ። ዛሬ ሕይወትን ሕይወት የሚያደርገው ሁሉ በዚያ ፍጹም በሆነ መልክ ይገኛል።

ፈጣሪ ሁሉ እያዩት ከሰዎች ጋር ስለሚኖር የደስታ ሰፍራ። እነርሱም በጥበቃው፣ በበረከቱና በፍቅሩ ይኖራሉ። በእግዚአብሔር – በአብ፣ በወልድና በመንፈስ – ደስ ይላቸዋል፤ ያመልኩታል፤ ያውቁታልም። ይወዱታል።

የዘላለማዊውን ዓይን ማየት፣ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ማየት ሰዎች ሊያገኙት የሚችሉት ታላቁ ደስታ ነው። ቢያንስ ያን ጊዜ ይህ ቃል ምን ያህል እውነት እንደ ሆነ እንረዳለን። ያለ ፍርሃትና ያለ ኀፍረት፣ ነጻ ወጥቶና በእግዚአብሔር እፍቃሪ ትኩረት ሙሉ በሙሉ ተማምኖ ለዘላለም መኖር ከምንም ጋር ሊወዳደር አይችልም። ዓይኑ በእኛ ላይ ሲያርፍ ሁልጊዜ የናፈቅነው ወሰን የሌለው ፍቅር ያገኘናል፣ ይነካናል፣ ይሞላናል፣ ያቅፈናልም።

ከሕይወት ውኃ ምንጭ መጠጣትና ከሕይወት ዛፍ ዘወትር መብላት። ይህ ዛሬ ስማይ ብለን ለምንጠራው ዘላለማዊ ሕይወት ምሳሌ ነው።

በዚያ፣ በፊቱ፣ ሁልጊዜ መሆን የነበረብን እንሆናለን። ራሳችን። እግዚአብሔር እንደ ፈለገንና እንዳደረገን ልዩና አንድ ብቻ። በዚያ ያለ ጭምብል። እውነተኛ።

ስዎች ሁሉ በዚያ በተሻለው ትርጉም በፍቅርና በእነክብካቤ ምድርን ይገዛሉ፤[252] በዚህም የመጀመሪያዎቹን ስዎች ተልእኮ ይፈጽማሉ። የፍጥረት ችሎታዎች ከመቼውም ጊዜ በላይ በሚገለጡበት መንገድ። በማይታሰብ የፈጠራ ችሎታ፣ ብዝኃነት፣ ብልጽግናና ደስታ። ሁሉ በእግዚአብሔር ፍቅር የተሞላ። በአንድነት – ሁሉን ያዘጋጀላቸው አባት ከቤተሰቡ ጋር።[253] ስማይና ምድር አንድ ይሆናሉ። ደስታችንን ልንረዳው አንችልም። ከ10,000 ዓመት በኋላም እንኳ። ለዘላለም ከኢየሱስ ጋር እንሆናለን። እውነተኛ፣ ጥልቅና የእልልታ ደስታ ፍጻሜ አይኖረውም።[254]

ወንጌል በዚያ እንድንገኝና ታላቁን ዘላለማዊ በዓል አብረን እንድናከብር የቀረበ ግብዣ ነው።[255] ይህ መልእክት ለሰዎች ሁሉ ይሄዳል።[256] እያንዳንዱ ሰው ተጋብዟል።[257] የመግቢያ ክፍያ የለውም። ኢየሱስ ሁሉን አሰተካክሏል![258]

ወንጌል – ለማዳን የሆነ ኃይል

ማንም የኢየሱስ ደቀ መዝሙር በወንጌል ማፈር አያስፈልገውም። መስቀሉ ለብዙዎች ሞኝነት ቢሆንም። ይህ መልእክት ኃይል አለው። እንደ ዲናማይት ነው።[259] ወንጌል ልባቸውን የከፈተላቸው ሰዎች በእነርሱ ላይ የሚሠራውን ይህን የእግዚአብሔር ኃይል ይለማመዳሉ። መመለስ ይሆናል፤ አዲስ ሕይወት ይጀመራል። የእግዚአብሔር ኃይል ብቻ ሊያመጣው የሚችልና በሕይወት ዘርፎች ሁሉ ላይ የሚሠራ የሕይወት ለውጥ።[260] ይህ ኃይል ያድናል፤ ከመናፍስት እስራትና ከሱሶችም ነጻ ያወጣል። ብዙዎች በሥጋም በነፍስም ተፈውሰዋል። ግንኙነቶች ይታደሳሉ። በወንጌል ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ኃይል

252. ሮሜ 5፥17፤ ራእይ 5፥10፤ 22፥5
253. 1 ቆሮንቶስ 2፥9
254. መዝሙር 16፥11
255. ራእይ 19፥6-10፤ 21፥6፤ 22፥14-15፣ 17
256. ማቴዎስ 28፥19-20፤ 2 ቆሮንቶስ 5፥15
257. ማቴዎስ 22፥1-14
258. ሮሜ 3፥24፤ ራእይ 21፥6፤ ኢሳይያስ 55፥1
259. ሮሜ 1፥16-17
260. 1 ተሰሎንቄ 1፥5-10

ከምንም ጋር ሊወዳደር አይችልም። እንደ ወንጌል ያለ ውጤት ያለው ርዕዮተ ዓለም ወይም ሃይማኖት ወይም ፍልስፍና የለም።[261]

እኛ ሰዎች ኃይል ባጣንበትና ግራ በተጋባንበት፣ ራሳችንንም ሌሎችንም መርዳት በማንችልበት ቦታ[262] ይህ ወንጌል ተአምር ይሠራል። ዳግመኛ የመወለድ ተአምር።[263] ወንጌል አዲስ ሕይወት ይፈጥራል። ልጅ ከሚወለድበት ጋር ይመሳሰላል።[264]

አንድ ጊዜ አንድ አምላክ የለሽ ሰው አንድ የታወቀ ወንጌላዊን ስለ እግዚአብሔር መኖር ክርክር እንዲያደርግ ጠየቀው። ወንጌላዊውም ተሰማማ፤ ነገር ግን አምላክ የለሹ በአምላክ የለሽነት አማካይነት ሕይወታቸው ወደ መልካም የተለወጠ ሰዎችን ይዞ እንዲመጣ ቅድመ ሁኔታ አደረገ። ክርክሩ አልተካሄደም፤ በአምላክ የለሽነት አዲስ ሰው የሆነ ወይም ከሱሰና ከጥገኝነት ነጻ የወጣ ማንም አልነበረምና። ወንጌላዊው ግን በወንጌል ሰብከቱ ነጻ የወጡና አዲስ ሰዎች የሆኑ ብዙ ሰዎችን ያውቅ ነበር።

ወንጌል በማንም ሰው ፊት አይቆምም። ለሁሉ ነው። በዚህ መልእክት ውስጥ የሚኖረው ኃይልም እንዲሁ። በልጁ ከሙታን መነሣት እንደ ተገለጠው የእግዚአብሔር ኃይል ነው።

ይህ ለመዳን የሆነ እውነተኛ ኃይል ነው!

ለወንጌል መታዘዝ

ወንጌል ሰዎችን ይለውጣል። ይህን አጣጥመውታል? ወይስ በሌሎች ላይ አይተውታል? እውነተኛ ደስታ ነው። በድንገት ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ይራባሉ። የእግዚአብሔርን መገኘት ይራባሉ።[265] ስለ እግዚአብሔር ይበልጥ ማወቅ ይመኛሉ። ወንጌልን ከማወቃቸው በፊት ይህ ፍላጎት አልነበረም። በድንገት እግዚአብሔር ምን እንደሚፈልግ ይጠይቃሉ።[266]

ለወንጌል የሚሰጠው ምላሽ በአንድ በኩል ግድ የለሽነት ወይም መቃወም ነው። በሌላ በኩል እምነት ነው።[267] ወንጌልን በአእምሮ እውነት ነው ብሎ መቀበል ብቻ ሳይሆን[268] የመላው ሰው የግል ምላሽ ነው። በአንድ ቃል፦ የእምነት መታዘዝ።[269] ሰዎች ይህ መልእክት

---

261. ዮሐንስ 8፥36፤ ሮሜ 6፥18
262. ሮሜ 5፥6
263. ዮሐንስ 3፥3፤ 1 ጴጥሮስ 1፥3፤ ቲቶ 3፥4-7
264. 1 ቆሮንቶስ 4፥15፤ ያዕቆብ 1፥18፤ 1 ጴጥሮስ 1፥23-25
265. 1 ጴጥሮስ 2፥2
266. 1 ጴጥሮስ 4፥2-3
267. የሐዋርያት ሥራ 2፥37-41
268. ያዕቆብ 2፥19
269. ሮሜ 1፥5፤ 16፥26፤ 1 ዮሐንስ 2፥3-4፤ 3፥24፤ 5፥2-3

የሚያመጣላቸውን በማመን የወንጌልን ጥሪ ይታዘዛሉ። ምንም እንኳ ራሳቸው እንደ መታዘዝ እርምጃ ሳይሆን ሰጦታን እንደ መቀበል ቢያዩትም።

ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ። ያለ እግዚአብሔር ያለውን ሕይወት ከሚገልጸው ነገር ሁሉ ይርቃሉ። ከሚታዩም ከማይታዩም ጣዖታት።[270] በሕይወታቸው ያለውን ኃጢአት ይገነዘባሉ፤ ለሰማያዊ አባታቸውም ይናዘዛሉ።[271] በእግዚአብሔር ጸጋ የሚገኘውን ይቅርታ ይይዛሉ። መዳንንና ፈውስን ያገኛሉ። ወንጌል በኃይልና በታላቅ እርግጠኝነትና ግልጽነት ሲሰበክ ሰዎችን ወደ ብርሃን ያመጣል።[272] ማንነታቸውንና እግዚአብሔር ማን እንደ ሆነ ይገነዘባሉ። ለሕይወት እውነታ ፍጹም የተለየ አመለካከት ያገኛሉ። በእግዚአብሔር ራሱ የሚመጣ ለውጥ ይሆናል – ከሞት ወደ ሕይወት እንደ መሸጋገር።[273]

የኢየሱስ ደቀ መዝሙር መሆን

ወደ ኢየሱስ መመለስ ብዙ ጊዜ ሂደት ነው። በወንጌል በኩል ከኢየሱስ ጋር የሚገናኝ ሰው በእምነት ትንንሽ እርምጃዎችን መውሰድ ይጀምራል። ኢየሱስን መሰማትና በእርሱ መታመን ይጀምራል። ጉዞ፣ እድገትና ትምህርት ይጀመራል። ደቀ መዝሙር መሆን ማለት ተማሪ፣ የሚማር ሰው መሆን ማለት ነው። ይህ በዚህ ሕይወት ፈጽሞ የማያቆም ሂደት ነው።

ያን ጊዜ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ወደሄደበት ሁሉ ይከተሉት ነበር። ከእሥራ ሁለቱ የሚበዙ ደቀ መዛሙርት ነበሩ። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ የሚማሩበት መምህር ነበር። ደቀ መዛሙርቱ እርሱ የሚለውን በማድረግ እርሱን ለመምሰል ፈለጉ።[274]

ኢየሱስ ከእንግዲህ በዚያ በሌለበት ጊዜም በኢየሱስ የሚያምኑትን ሁሉ ደቀ መዛሙርት ብለው ይጠሯቸው ነበር። ክርስቲያኖች ብለው የጠሯቸው በኋላ ነው።[275]

የደቀ መዝሙርነት ጅማሬ

ደቀ መዝሙርነት እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ግብ ነው! ንጉሠነ ኢየሱስን የሚታዘዙና ለእርሱ ታማኝ የሆኑ ሰዎች። ይህ አንዳንድ ጊዜ በግልጽ ይጀምራል፤ ብዙ ጊዜ ግን በፍርሃትና ሳይታወቅ ይጀምራል። የእግዚአብሔር መንፈስ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ

270. የሐዋርያት ሥራ 11፥21፤ 14፥15፤ 1 ተሰሎንቄ 1፥9-10፤ 1 ጴጥሮስ 4፥3
271. የሐዋርያት ሥራ 19፥18-20፤ 1 ዮሐንስ 1፥9፤ ምሳሌ 28፥13፤ መዝሙር 51
272. 1 ተሰሎንቄ 1፥5
273. ቆላስይስ 2፥13፤ 1 ዮሐንስ 3፥14
274. ዮሐንስ 8፥31
275. የሐዋርያት ሥራ 11፥26

የሚለውን እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል። በእምነትም እንዲያድጉ። በእነርሱ ውስጥ ወንጌል በልብ ለም መሬት ላይ እንደሚወድቅና አድጎ ፍሬ እንደሚያፈራ ዘር ይሠራል።[276] በእንዱ ፈጥኖ፣ በሌላው ይዘገያል። መውደቅና እንደገና መነሣት። በዚህ አዲሱ መንፈሳዊ ሕይወት ይታያል።[277] ወንጌልን ይበልጥ እየተረዱ መሄድ የመማር ሂደት ሆኖ ይቀራል። ይህ የሚሆነው የአእምሮ ጉዳይ ብቻ ሆኖ ሳይሆን በማድረግና በመኖር ነው።

በጣም አስፈላጊ ስለ ሆነ እንደገና፦ ኢየሱስን መከተልና ደቀ መዝሙር መሆን የወንጌል ግብ ነው። ወንጌል ወደ መንግሥተ ሰማያት መግቢያ ትኬት አይደለም፤ ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት በማሰብ ብቻ የሚያጽናና አይደለም። ይህን ሕይወት እዚህና አሁን የሚለውጥ ነገር ነው፤ እንድ ቀን በዘላለምና በክብር የሚቀጥልና የሚፈጸም። የዘላለምን ሕይወት መኖር አሁኑ ይጀመራል!

ሰው አሁን የክርስቶስ መሆኑን የሚመስክርበት የውጭ ምልክት አለ፦ ጥምቀት።[278] ከአሁን ጀምሮ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወቱ አዳኝና ጌታ መሆኑን በሰዎችና በማይታየው ዓለም ኃይላት ፊት በይፋ ያረጋግጣል፤ ያትማልም። የውኃ ጥምቀት ታላቅ ልዩነት ያመጣል። ወገን መቀየር ነው፤ ለንጉሡ ለኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጥ ምስክርነት ነው። ከኢየሱስ ጋር ያለው ሕይወት ገና ሲጀመር ይሆናል። ሰዎች የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ምን ያህል ከልባቸው እንደ ሆኑ እንዲያዩ በይፋ ሊደረግ ይገባል።

ኢየሱስን መከተል ምን ይመስላል?

የደቀ መዝሙር ሕይወት ምን ይመስላል? ሕይወትን ሕይወት የሚያደርጉትን ነገሮች ሁሉ ማድረጉን ይቀጥላል፦ መተኛት፣ መብላት፣ መሥራት፣ ወደ ትምህርት ቤት መሄድ ወዘተ። ነገር ግን የውስጥ ዝንባሌውና ተነሣሽነቱ፣ ለሕይወትና ለባልንጀራው ያለው አመለካከት ይለወጣል።

ከእግዚአብሔር የሆነው የአዲሱ ሕይወት ፍሬዎች እንደ መሆናቸው የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ጥቂት መለያዎች እነሆ። የምጠቅሰው ሁሉ አሁን ይፈተናል፤ ወደፊትም ይፈተናል። በክርስቶስ ያለው አዲሱ ማንነትም ውጊያ ይገጥመዋል። ተቃውሞ ከውጭ ብቻ ሳይሆን ከውስጥም ይመጣል። አሮጌው ማንነታችን፣ የቀድሞ ልማዶቻችን፣ በውስጣችን ያለው ኃጢአት እንደገና ብቅ ይላሉ። አዲሱ ነገር ሁሉ ምናብ ብቻ እንደ ሆነ

276. ማርቆስ 4፥20፤ ዮሐንስ 15፥8
277. ሮሜ 6፥21-22፤ 7፥4፤ ኤፌሶን 5፥9፤ ቆላስይስ 1፥10፤ ቲቶ 3፥14፤ ዕብራውያን 13፥15፤ 2 ጴጥሮስ 1፥8
278. ማቴዎስ 28፥19፤ ማርቆስ 16፥16፤ የሐዋርያት ሥራ 2፥38-41፤ 8፥12፣ 36-38፤ 9፥18፤ 10፥47-48፤ 16፥15፣ 33፤ 18፥8፤ ሮሜ 6፥3፤ ገላትያ 3፥27፤ ኤፌሶን 4፥5፤ ቆላስይስ 2፥12

አድርጎ በዚህ መደንገጥ አያስፈልግም። እግዚአብሔር ይረዳል፤ በውስጣችንም ይሠራል። መንፈሱ አጽናኝ፣ ኃይልና ረዳት ሆኖ ተስጥቶናል።

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት እግዚአብሔርን፣ ባልንጀራቸውንና እርስ በርሳቸው ይዋደዳሉ![279] መለኮታዊው ፍቅር ለዘላለም ከሁሉ የሚበልጥ ሆኖ ይኖራል![280] ወስን የለውም። የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት እርስ በርሳቸው ባላቸው ፍቅር ይታወቃሉ![281]

ደቀ መዛሙርት እርስ በርሳቸው ይተሳሰባሉ፤ ይጠባበቃሉም![282] ቤተሰብ ናቸው። ኅብረት ናቸው። ይህ የሚታየው በአምልኮ ጊዜ አዘውትሮ በመገኘት ብቻ ሳይሆን በመላ ሕይወት፣ በዕለት ተዕለት ኑሮ ነው።

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በጌታ እራት፣ እንጀራን በመቁረስ፣ ኢየሱስ ለእነርሱ ያደረገውን በአንድነት ያስታውሳሉ። ይህን አዘውትረው ወይም በቻሉት መጠን ያደርጋሉ።[283] ለአምልኮአቸው በቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች ላይ አይመሠረቱም። እንደ መንፈሳዊ ቤተሰብ በቤቶች ይሰበሰባሉ።

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ይጸልያሉ – ወደ ሰማያዊው አባት፣ ለብቻም በአንድነትም![284] እንደሚያዩት ሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገራሉ። ለብቻም በአንድነትም ማምለክና ማመስገን ለእነርሱ ታላቅ ደስታ ነው።[285]

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መጽሐፍ ቅዱስን ያነባሉ![286] በዚህም እግዚአብሔርንና ፈቃዱን ያውቃሉ። የሰጣቸውንም።

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የእግዚአብሔርን ድምፅ ይሰማሉ፤ በዕለት ተዕለት ኑሮ በትንሹም በትልቁም ነገር የእርሱን መሪነትና መመሪያ ያጣጥማሉ።

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መከራ ይቀበላሉ።[287] ኢየሱስ እንደ ተሰደደ በእነርሱም ላይ ሊደርስ ይችላል። ይህ በመሳለቅ፣ በማሰፈራራትና በማግለል ይጀምራል፤ በአንዳንድ የዓለም አገሮች እንዳለውም ዛሬም ሞትን ሊያስከትል ይችላል።[288]

---

279. ማቴዎስ 22፥36-40፤ ዮሐንስ 13፥34-35፤ 15፥13-17፤ 1 ቆሮንቶስ 13፥4-7
280. 1 ቆሮንቶስ 13፥13
281. ዮሐንስ 13፥35
282. የሐዋርያት ሥራ 11፥29
283. 1 ቆሮንቶስ 11፥23-27
284. ማቴዎስ 6፥5-15፤ ዮሐንስ 16፥26-27፤ 1 ተሰሎንቄ 5፥17
285. ዮሐንስ 4፥23
286. ቆላስይስ 3፥16፤ 2 ጢሞቴዎስ 3፥16፤ 1 ጴጥሮስ 2፥2
287. የሐዋርያት ሥራ 14፥22
288. ዮሐንስ 15፥18-20

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሌሎችን ሰዎች ደቀ መዛሙርት ያደርጋሉ![289] ወንጌል ሰዎችን አንድ የተወሰነ ነገር የሚያምኑ ክርስቲያኖች ሳይሆን በዕለት ተዕለት ኑሮ ኢየሱስን የሚከተሉ ደቀ መዛሙርት ያደርጋቸዋል። ሁሉን ለመተው፣ በየቀኑ መስቀላቸውን ለመሸከም ዝግጁ የሆኑና ሌሎችን ሰዎች ደቀ መዛሙርት ማድረግን የሕይወታቸው ግብ ያደረጉ። ኢየሱስ የፈለገው ይህንና ይህን ብቻ ነው![290] የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ወደ ሰዎች ይወጣሉ። ራሳቸውን አያገልሉም።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እድገትና ስለ እውቀት ሂደት ይናገራል።[291] ክርስቲያኖች ፍጹማን አይደሉም። ክርስቲያኖች ገና ኃጢአት ይሠራሉ፤ ነገር ግን ኃጢአት ከእንግዲህ አይገዛቸውም።[292] ከእንግዲህ ኃጢአት መሥራት አይፈልጉም። እግዚአብሔር በሰጣቸው ሁሉን አቀፍ ይቅርታ ውስጥ ይኖራሉ። ወደፊት ለሚሠሯቸው ኃጢአቶችም።[293] ኃጢአታቸውን ይገነዘባሉ፤ ለሰማያዊ አባታቸውም ይናዘዛሉ። እርስ በርሳቸው በበደሉ ጊዜም እርስ በርሳቸው።[294] የሚኖሩት ከጸጋ በታች ነው፤[295] ከሕግ በታች አይደለም።[296] ግባቸው አሥርቱን ትእዛዛት መጠበቅ አይደለም። ከኢየሱስ ጋር ያለው ሕይወት እነዚህ ትእዛዛት ከሚጠይቁት በላይ ይሄዳል። ይህ የሚቻለው መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ስለሚኖር ነው።

በውስጣቸው የሚኖረውንና የሚመራቸውን መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል።[297] ግቡ የመንፈስ መልካም ፍሬዎች እንዲታዩ ነው።[298] እነዚህ ፍሬዎች ከሁሉ በላይ እርስ በርስ በሚኖረው ግንኙነት ይታያሉ፦ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት። በአጠቃላይ ኢየሱስ የኖረው ይህ ነው። እርሱን መምሰል አዲሱ የሕይወት ግብ ነው።[299] በእርሱ ሰንታመን በሕይወታችን እንዲገኝና እንዲያድግ የሚያደርገው የእግዚአብሔር ፍሬ ነው። መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን የመከተል ኃይል ነው።[300] ይህ መንፈስ በሕይወታችን ያለው የእግዚአብሔር የግል መገኘት ነው። ይህ እጅግ

289. ማቴዎስ 28፥18-20
290. ሉቃስ 14፥26-27፣ 33፤ የሐዋርያት ሥራ 14፥21
291. ዮሐንስ 3፥30፤ ቆላስይስ 1፥10፤ 2 ተሰሎንቄ 1፥3፤ 2 ጴጥሮስ 3፥18
292. ሮሜ 6፥12-14
293. ዕብራውያን 10፥14፤ 1 ዮሐንስ 1፥5-2፥2
294. ያዕቆብ 5፥16
295. የሐዋርያት ሥራ 13፥43
296. ሮሜ 6፥14
297. ዮሐንስ 7፥39፤ 14፥17፤ 1 ቆሮንቶስ 2፥12፤ 6፥19
298. ገላትያ 5፥13-26
299. 2 ቆሮንቶስ 3፥18
300. የሐዋርያት ሥራ 13፥52፤ ሮሜ 8፥12-17

የሚያሰደንቅ አይደለም? መንፈሱ በአንድ ጊዜ አማካሪ፣ አስልጣኝ፣ መካሪ፣ ረዳትና መሪ ነው። ኢየሱስ እዚህ በምድር ላይ ከእኛ ጋር ቢሆን ኖሮ የሚያደርገውን በትክክል ያደርጋል።

የእግዚአብሔር መንፈስ ደቀ መዛሙርቱ እርስ በርሳቸው የሚያገለግሉባቸውን ስጦታዎች ይሰጣቸዋል።[301]

ደቀ መዝሙርነት የምችት ጉዞ አይደለም፣ የእግር ሽርሽር አይደለም፣ ወንበር ላይ ተቀምጦ የሚኖር ክርስትናም አይደለም። እንደ ኢየሱስ መኖርና ማገልገል ማለት ነው። ግዴታም የሚጥል አዲስ የሕይወት መርሕ። ለኢየሱስ ደቀ መዝሙር መንግሥቱና ጽድቁ ሁልጊዜ በመጀመሪያ ደረጃ ናቸው። ኢየሱስ እንደሚለው ስለ ሌላው ሁሉ አባታችን ይጨነቅልናል።[302]

ከኢየሱስ በቀር ማንም፦ ተከተለኝ! ለማለት ሥልጣን የለውም። እርሱ ሲጠራን እምቢ ማለት እንችላለን?

ቀላል መንገድ አይሆንም። ኢየሱስ ዋጋውን እንድናሰላ ይነግረናል፤[303] በመጀመሪያው ተቃራኒ ነፋስ የማይጠፋ ጽኑ፣ እውነተኛና የታሰበበት ውሳኔ እንድንወስን። ወደ ሕይወት የሚወስደው መንገድ ጠባብ ነው፤ ዳገትም ነው። ወደ ጥፋት የሚወስደው ሰፊ መንገድ በራሱ ይሄዳል። ሰው እንዳለ ከመቅረት በቀር ምንም ማድረግ እያስፈልገውም።[304]

የኢየሱስ ተከታዮች ሆነን ውጊያና ፈተና በሞላበት መላ ሕይወታችን ይህ ይሠራል፦ እግዚአብሔር ልጆቹን በማንኛውም ጊዜ ልጁን ስለ እነርሱ አሳልፎ በሰጠበት ቅጽበት እንደ ወደዳቸው ይወዳቸዋል።[305]

ወንጌልን ችል ማለት

ወንጌል የማሰፈራሪያ መልእክት አይደለም። የምሥራች ነው! በንስሐና በእምነት በኩል ወደ እግዚአብሔር፣ ወደ ይቅርታ፣ ወደ ነጻነት፣ ወደ ሕይወት፣ ወደ ትርጉም የሚያደርሰውን መንገድ ይከፍታል።

ነገር ግን ወንጌል ሰው እንደ ፈለገ የሚያደርገው ነገር አይደለም። ከብዙ እውነቶች አንዱ አይደለም። መልእክቱን የሚሰማ ውሳኔ እንዲያደርግ ይጠየቃል። ሰው በቸልታ ሊያየው አይገባም። ይህ መልእክት ሊያድነንና ሊጠብቀን ይፈልጋልና።

---

301. 1 ቆሮንቶስ 12፤ ሮሜ 12፥3-8
302. ማቴዎስ 6፥33
303. ሉቃስ 14፥28
304. ማቴዎስ 7፥13-14
305. ዮሐንስ 16፥27፤ 17፥23

ስለ ደን ቃጠሎ፣ ወይም ስለ አውሎ ነፋስ፣ ወይም ስለ ተበከለ የመጠጥ ውኃ፣ ወይም ስለ ግድብ መፍረስ የሚያስጠነቅቅ ዜና ያስቡ። ማስጠንቀቅ ብቻ ሳይሆን መውጫውንና መጠለያውን የሚያሳይ ዜና። ስው ይህን መልእክት ምን ያህል በቁም ነገር ሊወስደው ይገባል? ስው በስሕተት የተጋነነ ወይም ሐስት ወይም ለሌሎች ብቻ የታሰበ ነው ብሎ ቢያስብስ?

ሁሉም ወደ ብርሃን ይወጣል

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ከሙታን ለተነሣው የዓለም ጌታ በመመስከር ወንጌልን ስበኩ።[306] ስው በእርሱ ሲታመን፣ ኃጢአቱን ሲናዘዝና ሕይወቱን ሲለውጥ በእርሱ ይቅርታ እንደሚቻል አወጁ። በዚያው ጊዜ እያንዳንዱ ስው በዚህ ጌታ ፊት መልስ የሚሰጥበት ቀን እንደሚመጣና በጽኑ እንደ ተወሰነ ሁልጊዜ አጽንተው ተናገሩ። ኢየሱስ የሰዎች ሁሉ ዳኛ ነው። እያንዳንዱ በእርሱ ፊት ይቆማል። ዓይን ለዓይን። አባቱ እግዚአብሔር ፍርድን ሰጥቶታል።[307]

ስላደረግነው፣ ስለ ተናገርነውና ስላሰብነው ሁሉ መልስ እንሰጣለን። ስለዚህ ስለ ሕይወታችን እንድናስብ የሚሰጥ ማስጠንቀቂያ ነው! የምናደርገው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው እንደ ሆነ እንድናጤን። ሁሉ ነገር – ያለ ምንም ልዩነት ሁሉ ነገር – ወደ ብርሃን እንደሚወጣ ሲያስቡ ምን ይሰማዎታል? በሰውር ያሰብነውና ያደረግነው፣ በሰዎች ላይ ያደረስነውና ሳናደርግ የቀረነውም።

በውስጣችን በጥልቅ፣ በልባችንና በሳሊናችን፣ ኃጢአት እንደ ሠራን ሁላችንም እናውቃለን። እግዚአብሔር ፈጽሞ የማይፈቅደውን እናውቃለን። እሰቲ ያስቡ፦ ባለፈው ሳምንት ያሰብነውንና የተሰማንን በዚያ ሳምንት ከተገናኘናቸው ሰዎች ሁሉ ፊት በማያ ገጽ ላይ በይፋ ለማሳየት ፈቃደኞች እንሆናለን? ለራሳችን ብቻ ልንይዘው የምንመርጠው ብዙ ነገር ስለሚኖር ምናልባት እንሰማማም። ስው በሰዎች ፊት እንኳ በብዙ ነገር የሚያፍር ከሆነ በቅዱሱ አምላክ ፊትማ እንዴት ይሆናል?

በእኛ በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል ባለው ግንኙነት ውስጥ ያለው የኃጢአት ጉዳይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈጽሞ አይቃለልም። ስው እንደ ፈለገ ቢያገላብጠው፦ ዋናው ችግር ይህ ነው። ደስ የሚያሰኘው መልእክት ይህ ነው፦ በክርስቶስ ያለ ኩነኔን

306. የሐዋርያት ሥራ 4፥2፤ 8፥12፣ 25፣ 35፣ 40፤ 11፥20፤ 17፥18
307. የሐንስ 5፥22-29

መፍራት አያስፈልገውም።[308] ይቅር ከተባልን እግዚአብሔርን ለመገናኘት ከእንግዲህ መፍራት አያስፈልገንም። በክርስቶስ ልጆቹ – ወንዶች ልጆቹና ሴቶች ልጆቹ – አድርጎናል።[309] ፍጹሙ የእግዚአብሔር ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል![310]

ነገር ግን ወንጌልን ብቃወም ምን ይሆናል? እግዚአብሔር መልእክቱን በማንም ላይ በግድ አይጭንም። ውሳኔውን ለሰው ይተዋል። በዚያው ጊዜ ግን በዚህ መልእክት እርሱን ለማሳመን ሁሉን ያደርጋል። የሰዎችን ልብ ለማሳመን ይፈልጋል፤ ይታገላልም።[311]

የሕይወት አድን ቀለበት ሰለሚጣልለት እየሰመጠ ሰላለ ሰው ያሰቡ። የሚሰምጠውን ሰው እንዲድን ሊያሰገድዱት ይፈልጋሉ ብሎ የሚናገር ማንም የለም። ሰው ራሱን የጠፋ አድርጎ ካላወቀ ወንጌል ለእርሱ ምንም ትርጉም አይኖረውም። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ሰዎችን በመውቀስ በወንጌል ውሰጥ ይሠራል።[312] የእግዚአብሔር ቃል ልቦችን የመክፈት ኃይል አለው።[313]

ነገር ግን ሰው ራሱን ማታለል የለበትም፦ ያለ ወንጌል፣ ያለ ክርስቶስ ጠፍተናል፤ እሁንም ከእግዚአብሔር ቁጣ በታች ነን። ገለልተኛ ቀጠና የለም። በክርስቶስ ኩነኔ የለም – ያለ ክርስቶስ ግን በትክክል እንኮነናለን።

እምቢታው ከጸና ሰው ከመዘዙ ጋር ይኖራል። ያን ጊዜ ከኃጢአቱና ከበደሉ ጋር ብቻውን ይቀራል። ዓላማዎችን ሁሉ በሚያይ በእርሱ ፊት ሰው እንዴት ራሱን ሊከላከል ይፈልጋል ወይም ይችላል?

እግዚአብሔር ፍቅር ነው![314] እርሱ ግን ብርሃንም ነው። ፍጹም ቅዱስ።[315] መልእክቱን የሚቃወም ለእግዚአብሔር፣ ለኢየሱስና ከፍቅሩ የተነሣ ለእርሱ ላደረገው ነገር ሁሉ እምቢ ይላል። ለእያንዳንዱም በነጻ ለሚያቀርበው ሁሉ። ኢየሱስ አንድ ጊዜ እንዲህ አለ፦

ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል![316]

---

308. ሮሜ 8፥1
309. ዮሐንስ 1፥12
310. 1 ዮሐንስ 4፥16-19
311. ሉቃስ 19፥10
312. ዮሐንስ 16፥8
313. ዕብራውያን 4፥12-13
314. 1 ዮሐንስ 3፥1፤ 4፥7-8፣ 16
315. 1 ዮሐንስ 1፥5፤ ራእይ 4፥8
316. ማቴዎስ 12፥30

የእግዚአብሔር ቁጣ

የእግዚአብሔርን ቁጣ እውነታ አለመጠቆም ለተቸገረ ሰው እርዳታ እንደ መከልከል ያለ ነገር ይሆናል።[317] እግዚአብሔር ኃጢአትን ፈጽሞ እንደሚጸየፍ። ኃጢአት የውሸጥ ማንነቱን ይነካል። ሰዎቹ ያለ እግዚአብሔር ሲኖሩና ያለ እርሱ መንገዱ ወደ መከራ እንደሚያደርስ ሳያዩ ሲቀሩ ያዝናል።[318] የእግዚአብሔር ፍቅር ያለ ሰሜት ሊታሰብና ሊረዳ እንደማይችል ቁጣውም እንዲሁ ነው። ነገር ግን ይህ ቁጣም ንጹሕና ቅዱስ ነው። ድንገተኛ ንዴት አይደለም፤ ለሰዎች ኃጢአት የሚሰጥ ምክንያት የሌለውና ልክ የሌለው ምላሽም አይደለም። እግዚአብሔር ለቁጣ የዘገየ ነው![319] እንደ እኛ እንደ ሰዎች አይደለም።

የእግዚአብሔር ቁጣ ማለት እግዚአብሔር ሰውን ከኃጢአቱ መዘዝና ውጤት ጋር ለራሱ ይተወዋል ማለት ነው።[320] ብቻዬን መተው፣ ራሴ ከፈጠርኋቸው ችግሮቼ ሁሉ ጋር መጥፋት። ይህን ማንም ሊያጋጥመው አይፈልግም።

ቁጣው ማለት በፍርድ ቀን ከኃጢአቴ ጋር ሆኜ የእግዚአብሔርን የከበረ ቅድስና መገናኘት ማለት ነው። የእግዚአብሔር ቁጣ እኛ ሰዎች በሰዎችና በእርሱ ላይ ለምንፈጽመው ኃጢአት እግዚአብሔር የሚሰጠው ምላሽ ነው።

እግዚአብሔር ባይቆጣ ኖሮ እግዚአብሔር ባልሆነ ነበር። በማንኛውም መልኩ ክፋትን የማይታገሠውን ፍቅሩን በካደ ነበር። በመጨረሻ ለሁሉ ነገር «አዎን» የሚል አምላክ ማንም አይፈልግም። ሰዎች ፍትሕን ማረጋገጥ ካልቻሉ ተስፋ ልናደርግ የምንችለው በእግዚአብሔር ብቻ ነው። ይህ ግን ሌሎችን ብቻ አይመለከትም – እያንዳንዱ ስለ ራሱ መልስ ይሰጣል።

ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን የማሰታረቅ ፈቃድ ይመሰክራሉ፤[321] ራሳቸው እንዲህ አድርገው አውቀውታልና።[322] ነገር ግን የእኛን መለኪያ የሚቀበል የተገራ አምላክ አይደለም። በዓመፃችን ላይ ዝም አይልም። ወይም በቀላሉ አያልፈውም። ፍትሕ እንዲኖር ያደርጋል። ከአቅማችንና ከዛሬው አስተሳሰባችን በሚበልጥ በራሱ መንገድ።

ለእግዚአብሔርና ለምሥራቹ – ምናልባትም ብዙ ጊዜ – «አይሆንም» የሚል ራሱን ያደነድናል። በዚህ ሰው ይጠፋል።[323] የሚጠፋው እግዚአብሔር ይህን እምቢታ በከባድ

317. ዮሐንስ 3፥36፤ ሮሜ 1፥18፤ 2፥5፣ 8፤ 3፥5፤ 5፥9፤ ኤፌሶን 2፥3፤ 5፥6፤ ቆላስይስ 3፥5-6፤ ራእይ 6፥16-17፤ 11፥18
318. ማርቆስ 3፥5
319. ዘጸአት 34፥6
320. ሮሜ 1፥26
321. 2 ቆሮንቶስ 5፥19-20
322. 2 ቆሮንቶስ 5፥11
323. ሮሜ 2፥12፤ 1 ቆሮንቶስ 1፥18፤ 15፥18፤ 2 ቆሮንቶስ 2፥15፤ 4፥3፤ 2 ተሰሎንቄ 2፥10፤ 2 ጴጥሮስ 3፥9

ልብ ሰለሚቀበል ነው። መጥፋት ማለት ሰው ሊሆንበት በሚገባውና ሊሆንበት በሚችልበት ቦታ አለመሆን ማለት ነው። በቤት ሳይሆን ብቻውን ሆኖና ሥሩ ተነቅሎ። ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ተቋርጧል። ወደ ቤት ሊያመጣው እያንዳንዱን እስከ መጨረሻው ከሚከተለው አምላክ ጋር።[324]

ወንጌልን የሚቃወም እያንዳንዱ ሰው ሰለ ኃጢአቱ ትክክለኛውን ኩነኔ ይቀበላል።[325] ፍርዱ ፍጹም ትክክል ይሆናል።[326] ሰው የሚዘራውን ያጭዳል፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትምና።[327] ለእውነትና ለወንጌል ያልታዘዘ፣ በግትርነት የተቃወመ ቁጣን፣ መዓትን፣ መከራንና ጭንቀትን ያገኛል።[328] አንዳንድ ጊዜ በዚህ ሕይወትም፣ ከሞት በኋላ ግን በእርግጥ። ያልተሰረየለትን ኃጢአቱን ዓይን ለዓይን ማየትና የራሱን ኃጢአት እንደገና መገናኘት እንዲህ ይሰማዋል። በዚህ ጊዜ በእግዚአብሔር ዓይን። ግፍ በዋለባቸው ሰዎች ዓይንም።

የዘላለም ሕይወትና ገሃነም

ኢየሱስ በክብር ሰላለው የዘላለም ሕይወት[329] እንዲሁም ሰለ ዘላለም እሳትና ሰለ ዘላለም ቅጣት ይናገራል።[330] ለወንጌል የማይታዘዙት ሰለሚገኙበት በውጭ ሰላለው ጨለማ ይናገራል።[331] ሰለ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት።[332]

ሰለ ገሃነም ብዙ ጊዜ የሚናገረው በእርግጥ ኢየሱስ ነው። ራሱ ፍቅር የሆነው እርሱ ከሁሉ ይበልጥ ሰለ እርሱ ተናገረ።[333]

በአዲስ ኪዳን የመጀመሪያ ቋንቋ በግሪክ ለገሃነም የሚውለው ቃል Gehenna ነው። ያን ጊዜ ይህ እውነተኛ ሰፍራ ነበር፤ በኢየሩሳሌም አጠገብ ያለ ሸለቆ። በኢየሱስ ዘመን እሳት ዘወትር የሚነድበት የቆሻሻ መጣያ። ኢየሱስ ያንኑ ሸለቆ የሄኖም ልጅ ሸለቆ (ቤን ሂኖም) ብሎ የሚጠራውን ነቢዩ ኤርምያስንም ይጠቅሳል።[334] ይህ ሰፍራ ልጆችም ጭምር

---

324. ሉቃስ 15፥4፣ 24፤ ዮሐንስ 3፥16፤ 2 ጴጥሮስ 3፥9
325. 2 ቆሮንቶስ 5፥10
326. ራእይ 20፥11-15፤ 21፥8
327. ገላትያ 6፥7-8፤ ዘኁልቁ 32፥23
328. ሮሜ 2፥5-11
329. ዮሐንስ 3፥36፤ 5፥24፤ 6፥47፣ 51፤ 10፥28፤ 11፥26፤ ሮሜ 5፥21፤ 6፥23፤ 1 ዮሐንስ 2፥25፤ 5፥11፣ 13
330. ማቴዎስ 25፥34፣ 41፣ 46
331. ማቴዎስ 8፥12፤ 22፥13፤ 25፥30፤ ዮሐንስ 8፥12፤ 12፥46
332. ማቴዎስ 8፥12፤ 13፥42፣ 50፤ 22፥13፤ 24፥51፤ 25፥30፤ ሉቃስ 13፥28
333. ማቴዎስ 5፥22-30፤ 10፥28፤ 18፥9፤ 23፥33
334. ኤርምያስ 7፥31፤ 19፥2-7፤ 32፥35፤ ኢሳይያስ 66፥24

በሚሠዉበት የጣዖት አምልኮው የታወቀ ነበር። ስለዚህ የኀፍረትና የኃጢአት መገለጫ ነበር። ስለዚህም የፍርድና የጥፋት። የመጥፋትና የሞት።

እንደ ቀድሞው መኖር የሚፈልግ፣ በኃጢአቱ ውስጥ መቀጠል የሚፈልግ በዚህ ሕይወትን ይቃወማል። ከዘላለም ሕይወት ክብር ውጭ ሆኖ ይቀራል። ይህ በእግዚአብሔር አዲስ ዓለም ውስጥ የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ ሕይወትና የወደፊት ዕድል ነው።[335]

ገሃነም እንደ ማስጠንቀቂያ በከባድ ምሳሌዎች ተገልጿል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ዝም አይልም። በተቃራኒው፦ እጥብቆ ያስጠነቅቃል። ለ«ታላላቅ ኃጢአተኞች» ብቻ አይደለም። እንደ ሂትለር (Hitler)፣ ስታሊን (Stalin) ወይም ማኦ (Mao) ያሉ የጅምላ ገዳዮችን ብቻ አናስብ። ጨካኞችን ወይም ሕፃናትን የሚደፍሩትን ብቻ አይደለም። እግዚአብሔር ፍርዳቸውን የሚወስነው በእኛ መለኪያ ምንም ወይም ጥቂት ጥፋት እንደሌለበት ሰው ፍርድ እኩል በትክክል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል፦ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርንም ክብር አይመጥኑም።[336]

ገሃነም ለሰዎች በዝርዝር ምን ማለት እንደ ሆነ ኢየሱስና መጽሐፍ ቅዱስ ዝም ይላሉ። ስለዚህ ምናብ እዚህ ቦታ የለውም። የኢየሱስ ቃላት በቂ ማስጠንቀቂያ ናቸው።

ስለ ገሃነም ልዩ ልዩ አስተያየቶችን ይሰማሉ። አንዳንዶች የለም ይላሉ። ሌሎች የጠፉት ሰዎች በዚያ ለመጨረሻ ጊዜ ይጠፋሉ ብለው ያስባሉ። አንዳንዶች ደግሞ ሰዎች በዚያ የሚቆዩት ለመንጻት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው፤ ከዚያም በኋላ ወደ ዘላለም ሕይወት ይገባሉ ይላሉ። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ያንብቡ፤ በግርጌ ማስታወሻዎቹ ያሉትን ክፍሎችም አውጥተው ይመልከቱ። ከከፋው፣ ከከፋው ሁኔታ ይነሡ። በመራራ ሁኔታ ተሰፋ ከመቁረጥ ይልቅ በመልካም መደነቅ ይሻላል።

እግዚአብሔር የሰዎችን እምቢታ ያከብራል። ቢያመውም፣ ኢየሱስም በኢየሩሳሌም ላይ እንዳዘነ ቢያዝንም።[337] ከእግዚአብሔር ተለይተው የእምቢታቸውንና የኃጢአታቸውን መዘዝ ይሸከማሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ሁለተኛው ሞት ብሎ ይጠራዋል።[338] ያለ እግዚአብሔር መኖር ፈልገው ነበር፤ አሁንም ለዘላለም እንዲሁ ይኖራሉ። «በገሃነም

335. ራእይ 21፥8፣ 27፤ 22፥15
336. ሮሜ 3፥23
337. ማቴዎስ 23፥37
338. ራእይ 2፥11፤ 20፥6፣ 14፤ 21፥8

የሚኖሩት በፈቃዳቸው የገቡ ብቻ ናቸው» የሚለው አባባል እውነት ነው።[339] ሰው ሞትን ወይም ሕይወትን የመምረጥ ምርጫ ፊት ቆሟል።[340]

ዛሬ የመዳን ቀን ነው – ነገ አይደለም!

ሌላው ወንጌል

ወንጌል የእውነት ቃል ነው።[341] የእግዚአብሔር እውነት። ወንጌል በተሰፋፋ ቁጥር ከመጀመሪያው ጋር የማይሰማሙ ቅጂዎች እየበዙ መጡ። በዘመናችን አቆጣጠር በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን እነኳ ኢየሱስ እንዲሰብኩ የላካቸው ሐዋርያት የተበረዘ ወንጌልን እንዲጠነቀቁ ያሰጠነቅቃሉ።[342] ከመጀመሪያው ጋር ይመሳሰላሉ፤ በሚያታልል ሁኔታ እውነተኛ ሊመስሉ ይችላሉ።

እንዲሁም ዋና ነገርን የሚያሰቀሩ ወይም የሚጨምሩ ያጠሩ ቅጂዎች አሉ። ሐሰተኛና አሳሳች ቅጂዎች አሉ። ለመንገድ መሪነት እነዚህ ምሳሌዎች።

ወንጌል ራሳችንን ማዳን እንደማንችል ያለማወላወል ያሳያል። ራሳችንን ለማሻሻል የምናደርገው ሙከራ ሁሉ ተሰፋ የለውም። የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅና በመልካም ሥራ በእግዚአብሔር ተቀባይነት ለማግኘት የሚደረገው ሙከራ ይከሽፋል።[343]

እንዲሁም ጥቂት የእግዚአብሔርን ጸጋ ወስዶ መልካም ሥራዎቻችንን እንደ አሰፈላጊ ተጨማሪ መጨመርም አይሠራም። የጸጋና በሥራ የሚገኝ ጽድቅ መደባለቅ ወይም መደጋገፍ። አንድ ነገር ልናተርፍ መፈለጋችን በሆነ መንገድ የሰው ተፈጥሮአችን አካል ነው። ጸጋን መቀበል ይከብዳል። ነገር ግን ወንጌል በትክክል ይህ ነው!

በሌላ በኩል ደግሞ ይህን የእግዚአብሔር ጸጋ ዋጋ ማሳጣትና ርካሽ ማድረግ ይቻላል። ወንጌልን የሚቀበል ነገር ግን ሕይወቱን የማይለውጥ – መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ንሰሐና መመለስ ይለዋል – በተሳሳተ መንገድ ተረድቶታል። ወንጌል በራስ ወዳድነትና በኃጢአተኛ ራስን የማሟላት ፍላጎት ለሚኖር ሕይወት ነጻ የጉዞ ፈቃድ አይደለም።[344] ሕያው እምነት ሁልጊዜ ወደ ጥልቅ የሕይወት ለውጥ ያደርሳል።[345] ክርስቶስ ጌታና ገዢ ወደ ሆነበት

339. ሐሳቡ ከሲ. ኤስ. ሉዊስ (C. S. Lewis) የመጣ ነው፦ የገሃነም በሮች ከውስጥ የተቆለፉ ናቸው («Über den Schmerz» (The Problem of Pain))።
340. ዘዳግም 30፥15-19
341. ገላትያ 2፥5፣ 14፤ ኤፌሶን 1፥13፤ ቆላስይስ 1፥5፤ 1 ጢሞቴዎስ 2፥4
342. 2 ቆሮንቶስ 11፥1-4፤ ገላትያ 1፥6-9
343. ሮሜ 3፥20፣ 28፤ ገላትያ 2፥16፤ 3፥10
344. ሮሜ 6፥1፤ 2 ጴጥሮስ 1፥9-11
345. ያዕቆብ 2፥18-26

አዲሰ ሕይወት ያደርሳል።[346] አዲሱ ሕይወት ኃጢአት የሌለበት አይደለም። በምድራዊ አካል ፈጽሞ እንዲህ አይሆንም። ነገር ግን ግልጽ የሆነ «በፊት» እና «በኋላ» አለ፤ በትንሽም በትልቅም ሥራና ቃል የሚታይ ለውጥ። መልካም ሥራዎች እንደ እምነት ራሱ የክርሰቲያን ሕይወት አካል ናቸው። ያለ መልካም ሥራ እምነት የሞተ ነው። እውነተኛ እምነት ባለበት ቦታ በመልካም ሥራ ይታያል። ይህ በሥራ የሚገኝ ጽድቅ አይደለም። መልካም ሥራዎች የአዲሱ ሕይወት ማሰረጃዎች ናቸው።

እውነተኛው ወንጌል ተጨማሪ ነገር አያሰፈልገውም። ኢየሱሰ፤ ከእርሱ በቀር ምንም – መልእክቱ ይህ ነው።

ሰለዚህ አዲሰ ኪዳን እንደሚገልጸው ወንጌልን ልንጠብቅ ይገባናል።[347] የተበረዘ ወንጌል አያድንም!

ወንጌል ያልሆነው

ወንጌል ለአንድ ቤተ ክርሰቲያን ወይም ለአንድ ቤተ እምነት የሚደረግ ማሰታወቂያ አይደለም። ቤተ ክርሰቲያን ሚና የላትም ማለት አይደለም። የሁሉም ቤተ እምነቶች ክርሰቲያኖች ወንጌልን በብዛትም ይሁን በትንሹ ያሰተላልፋሉ። አብያተ ክርሰቲያናት ወደ እምነት ለሚመጡ ሁሉ ቤትና መኖሪያ ናቸው።

ወንጌል በብዙ ቦታዎች ለዓለም መሻሻል በብዙ የሚያበረክት ቢሆንም በመጀመሪያ ደረጃ ራሱን ዓለምን የማሻሻያ ፕሮግራም አድርጎ አያይም። ይልቁንም ልብን የመለወጫ ፕሮግራም ነው። በብዙ የኢየሱሰ ደቀ መዛሙርት የባልንጀራ ፍቅር ብዙዎች ይረዳሉ። ሆሰፒታሎች፣ የሕፃናት ማሳደጊያዎች፣ የባርነት መሻር በሰዎች ውሰጥ መልክ የሚይዘው የእግዚአብሔር ፍቅር ማሰረጃዎች ናቸው። ክርሰቲያኖች እንደ ጨው ሊሠሩ ይገባል።[348] ግፍን – ዓለም አቀፉንም – በሰሙ መጥራትና ለፍትሕ መቆም።

በክርሰቶሰ መሰቀል በኩል የእንድ ሰው መዳን ኅብረተሰብን የሚነካ አብዮታዊ ኃይል ይለቃል። የመሰቀሉ መልእክት ዓለምን ወደ መልካም ሊለውጥ የሚችል ብቸኛው ኃይል ነው። ይህን ማድረግ እንደሚችልም ያረጋገጠ ብቸኛው ኃይል። የክርሰቶሰ መሰቀል እንደገና በታላቅ ድምፅና በግልጽ የሚሰበክበት ጊዜ ደርሷል።

346. 2 ጴጥሮሰ 2፥1፤ ይሁዳ 1፥4
347. ይሁዳ 1፥3
348. ማቴዎሰ 5፥13

በተግባር ወንጌል የሚታየው ኢየሱስ እንዳደረገው በማድረግ ነው። ለመሰጠት፣ ለመርዳት፣ ለመጠበቅ፣ ነጻ ለማውጣት፣ ለመመስከር ዝግጁ መሆን። ለመውደድ! በብዙ ቦታዎች አንድ ነገር ወደ መልካም ይለወጣል። ወንጌል በለወጣቸው ሰዎች በኩል። እግዚአብሔር በሰዎቹ በኩል በዓለም ይሠራል፤ አንድ ቀንም ሁሉን አዲስ ያደርጋል። ዓለምን መለወጥ፣ ማሸጋገርና ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና የገንዘብ ችግሮቿን መፍታት በደቀ መዛሙርቱ ትከሻ ላይ የተጫነ አይደለም። ኢየሱስ በአደራ የሰጠን ተግባርና ተልእኮ ይህ አይደለም።

በመንግሥቱ ደቀ መዛሙርት ውስጥ፣ በኅብረታቸው ውስጥ፣ የእግዚአብሔር አዲስ ዓለም አስቀድሞ ጀምሯል። የመንግሥቱን ወንጌል ይሰብካሉ፤ ሰዎችንም ደቀ መዛሙርት ያደርጋሉ። ይህ በሚኖሩበት ኅብረተሰብ ላይ ያላቸው እጅግ ውጤታማው ተጽእኖ ነው።

ወንጌል የግል ሕይወትን የማሻሻያ ፕሮግራምም አይደለም። ወይም የመበልጸጊያ። ራስን የማሳደጊያ ዘዴም አይደለም። እግዚአብሔር እኛ ልናደርገው ያልቻልነውን ነገር እንዳደረገና እንደ ፈጸመ የሚናገር መልእክት ነው። በዚህ ዓለት ላይ ሕይወታችንን እንገነባለን። መዳናችን ኢየሱስ በመሰቀል ላይ በጮኸው ቃል ላይ ያርፋል፦ ተፈጸመ! ለዚህ «አዎን» እንላለን፤ በምስጋናም እንቀበለዋለን።

ብልጽግና ወይም ሀብት ግን ፈጽሞ የወንጌል የተሰፋ ቃል አይደሉም። በመገለልና በሰደት ምክንያት ክርስቲያኖች እንዳንድ ጊዜ ከጎረቤቶቻቸው ይልቅ የከፋ ኑሮ ይኖራሉ። ነገር ግን ሁልጊዜ ከእነርሱ ጋር እንደሚሆንና እንደሚያሟላላቸው ቃል በገባው አምላክ ሊታመኑ ይችላሉ።

በመጨረሻም

ይህ በዓለም ሰላለው እጅግ መልካም መልእክት አጠቃላይ ቅኝት ብቻ ነበር። የሚያነሣ መልእክት። ይቅርታንና ተቀባይነትን የሚሰጥ። በኢየሱስ በኩል ነጻ የሚያወጣና የሚያበረታታ።

ይህ መልእክት ለእርስዎ በግል ምን ይላል? ለልብዎ? ምናልባት እንደ አሁኑ ቀርበው አያውቁም ይሆናል። ዛሬ የመዳን ቀን ነው – ነገ አይደለም፤ ያን ጊዜ ሊረፍድ ይችላል።

ወንጌል በሳንቲሞችና በትንንሽ ኖቶች ተመንዝሮ እንደሚከፈል ትልቅ የብር ኖት ነው። የዚህን መልእክት ይዘት ይበልጥ እየተረዱና እየጠለቁበት መሄድ ጊዜ ይወሰዳል። ይህ በትንንሽ፣ አንዳንድ ጊዜም በትልልቅ እርምጃዎች ይሆናል። ኢየሱስን ስንከተል። በዕለት

ተዕለት ኑሮ። እውነተኛ እውቀት የሚያድገው በእያንዳንዱ የእምነትና የመታዘዝ እርምጃ ብቻ ነው። ማለትም ኢየሱስ የሚለውን ስናደርግ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ወደ መዳን ታሪክ በለወጠው የዓለም ታሪክ ማዕከል ላይ ወንጌል ይቆማል።

ጳውሎስ በሮም ላሉ አማኞች ወንጌልን ሊሰብክ ፈለገ፤[349] ምንም እንኳ ለረጅም ጊዜ በእምነት የኖሩ ቢሆኑም። ታላቅነቱን፣ ስፋቱንና ለምድራዊ ሕይወታችንና ለዘላለም ያለውን ውጤት ሊያሳይ ፈለገ። ጻፈውም፦ ወደ ሮሜ ሰዎች የተጻፈውን መልእክት። የወንጌል ሐውልት።

ይህን መልእክት ያንብቡ!

ከዚህስ በኋላ?

ስለ እርስዎና በቀጥታ ለእርስዎ ስለ ተናገረው መልካም ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ።

ጥያቄ ካለዎት ይጻፉልኝ፦ hj-ronsdorf@t-online.de

ሌሎች መጻሕፍትን፣ ጽሑፎችንና ስብከቶችን በድረ ገጼ ያገኛሉ፦ www.hans-joerg-ronsdorf.de



ጥቂት ጠቃሚ ምክሮች እነሆ፦

- መጽሐፍ ቅዱስን ያንብቡ። ቢቻል አዘውትረው።
- መጽሐፍ ቅዱስን ከሌሎች ሰዎች ጋር አብረው ያንብቡ – ስለ እርሱም ይወያዩ።
- እግዚአብሔር ቃሉን ሕያው እንዲያደርግልዎ ይጸልዩ – በቀጥታ ለእርስዎ እንደሚናገር አድርጎ።

349. ሮሜ 1፥1-5፣ 9፣ 15-17

- ክፍሉን ያንብቡ፤ ቢቻል ጮክ ብለውና ብዙ ጊዜ።

ስለ ክፍሉ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ፦

- ለዚህ ክፍል ምን ርዕሰ ይሰጡታል?
- ክፍሉ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ኢየሱስ ምን ይላል?
- ክፍሉ ስለ ሰዎች ምን ይላል?
- ከክፍሉ ምን እንማራለን?
- ምን ማድረግ አለብን?
- ቃሉ እንዴት ያበረታታናል?

በእንድነት ይጸልዩ። እንደገና ሲገናኙ ስላጋጠመዎትና ስለ ተለማመዱት ነገር ይነጋገሩ።

ኢየሱስ ክርስቶስን ከሚወዱና ከሚያከብሩ፣ መጽሐፍ ቅዱስንም ከሚያከብሩ፣ ከሚያነቡና በቁም ነገር ከሚወስዱ ክርስቲያኖች ጋር ግንኙነትና ኅብረት ይፈልጉ።

የኢየሱስ ወንጌል የምሥራች ነው? ለመሆኑ ለምን?

ጥቂት ጊዜ ይውሰዱና የወንጌልን ልዩነት ከተለያዩ አቅጣጫዎች ይመልከቱ።

በቀላልና በሚገባ መንገድ እዚህ ስለ ሙሉው ሥዕል ይነገራል።